


t.me/OLDBOOKSPDF

የአያሌዎቹን ሕይወት የለወጠ መጽሐፍ

# ምስጢሩ......

# (THE SECRET)

የአማርኛ ትርጉም
ጋሻው አባተ

t.me/OLDBOOKSPDF

# የእንከን-የለሽ ህይወት ምስጢሩ........

# (THE SECRET)


**በሮዳን ቢይርን ተፅፎ**

የአማርኛ ትርጉም ፡ በጋሻው አባተ
የአማርኛ ትርጉም ሥራ አስተባባሪ፡ ዶ/ር በዕውቀቱ ታደሰ



አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ዋና አከፋፋይ ሱፐርስታር መፀሐፍት መደብር
911-122835/911637928


t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት መረጃዎች በሙሉ ለማስተማሪያነት እንጂ ለህክምና፣ ለምርመራ፣ ለመድሃኒት ማዘዣ፣ ወይም ምንም አይነት የጤና መዛባትን ለማከም የታሰቡ አይደሉም:: ይህ መጽሐፍ የህክምና ባለሙያን መተካት የለበትም:: የዚህ መጽሐፍ ይዘት በህክምና ባለሙያ ሲታዘዝ እንደ አጋር የጤና ፕሮግራም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል:: የዚህ መፍሐፍ ደራሲ፣ አሳታሚ ተርጓሚና አስተርጓሚ የመጽሐፉን ክፍል ካለአግባብ በመጠቀም ለሚከተል ማንኛውም ጉዳት ምንም አይነት ኃላፊነት አይኖርባቸውም::

t.me/OLDBOOKSPDF

# ለአንባቢው ማስታወሻ

ምስጢሩ (The Secret) ለዘለአለሙ ፍቅርና ደስታን ያምጣልህ:: ለአንተና ለቀሪው አለም ይህ ነው ምኞታችን::

t.me/OLDBOOKSPDF

መቅድም ........................................ i

ምስጋና ........................................ iv

የተከሰተው ምስጢር ........................................ 1

ምስጢሩ ሲቃለል ........................................ 19

የምስጢሩ ጥቅም ........................................ 32

ኃያሉ ሂደት ........................................ 51

የገንዘብ ምስጢር ........................................ 68

የግንኙነት ምስጢር ........................................ 80

የጤና ምስጢር ........................................ 88

የአለም ምስጢር ........................................ 99

የአንተ ምስጢር ........................................ 109

የህይወት ምስጢር ........................................ 122

የህይወት ታሪኮች ........................................ 128

t.me/OLDBOOKSPDF

# መቅድም

ከአንድ አመት በፊት እስኪደክመኝ በመስራቴ ህይወቴ በአደጋ ላይ ወድቆ ነበር፡፡ አባቴም ሳይታሰብ ሞተ፡፡ በመሆኑም ከሥራ ባልደረቦቼና ከምወዳቸው ጋር የነበረኝ ግንኙነት የተበጠበጠ ሆነ፡፡ በወቅቱ ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ከትልቁ ጭንቀቴ እጅግ ታላቅ ስጦታ ሊከተል ኖሯል፡፡ የትልቅ ምስጢር ጨረፍታ፡፡ ለህይወት የሚበጅ ምስጢር፡፡ ምስጢሩ ከአንድ መቶ አመት ከሞላው መጽሐፍ ነበር የተገኘው፡፡ መጽሐፉን የሰጠችኝ ሃይሊይ ብዬ የምጠራት ልጄ ነበረች፡፡ ታሪክን መሠረት አድርጌ ምስጢሩን ወደኋላ ተመልሼ መመርመር ጀመርኩ፡፡ ይህን የሚያውቁትን ሁሉንም ሰዎች ማመን አቃተኝ፡፡ ለካስ በታሪክ የላቁ (ፕላቶ፣ ሼክስፒር፣ ኒውተን፣ ሁጎ፣ ቤትሆቨን፣ ሊንከን፣ ኤመርሰን፣ ኤዲሰን፣ አንስታይን) ሰዎች ኖረዋል፡፡

በመገረም «ሁሉም ሰው ለምን ይህን አያውቅም?» ብዬ ጠየቅሁ፡፡ ምስጢሩን ከቀረው አለም ጋር የመጋራት የጋለ ፍላጎቴ ዋጠኝና በአሁኑ ወቅት በህይወት ያሉና ምስጢሩን የሚያውቁ ሰዎችን ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ አንድ በአንድ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ማፈላለግ ስጀምር ልክ እንደማግኔት ሆንኩና አንዱ ህያው አሲታ ሌላውን እየተከተለ ወደ እኔ ይጎርፉ ጀመር፡፡ አንዱን መምህር ሳገኝ ይኸው መምህር በተስተካከለ ሰንሰለት ከሚቀጥለው ሌላ መምህር ጋር አገናኘኝ፡፡ የተሳሳተ መንገድ የተከተልኩ እንደሆን የሆነ ነገር ግንዛቤዬን ይይዘውና አቅጣጫ በመቀየር ቀጣዩ አብይ መምህር ይከሰትልኛል፡፡ በአጋጣሚና በስህተት ኢንተርኔት ከነካካሁ ወሳኝነት ያለው መረጃ አገኛለሁ፡፡ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ነው ከአመታት በኋላ ሄጄ ምስጢሩን ያገኘሁት፡፡ የዘመናችን የምስጢሩን ተግባሪዎችም አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ምስጢሩን በፊልም ወደቀረው አለም የማዳረስ ራዕይ በአይምሮዬ ተቀረፀ፡፡ በሁለት ወራት ውስጥ የፊልምና የቴሌቪዥን ቡድን ሠራተኞቼ ምስጢሩን ተማሩት/ አወቁት፡፡ መማራቸው እጅግ ጠቃሚ ነገር ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለምስጢሩ ምንም እውቀት ሳይኖር ምንም ነገር ለመሞከር ያዳግተን ነበርና::

ፊልም የሚያስተምረን እንድም መምህር አልነበረንም:: ነገር ግን፣ ምስጢሩን እናውቀው ነበርና በጠንካራ እምነት ታጅቤ ከአውስትራሊያ አብዛኞቹ አስተማሪዎች ወደሚገኙባት አሜሪካ በረርኩ:: ከሰባት ወራት በኋላ የምስጢሩ ቡድን በመላ አሜሪካ የሚገኙ ታላላቅ የሚባሉ ሃምሳ አምስት መምህራንን እንድመቶ ሃያ ሰዓት በፊጆ ፊልም ውስጥ አካትቷል:: በእያንዳንዱ እርምጃና በእያንዳንዱ ጥልቀት ምስጢሩ ምስጢሩን እንዲፈጥርልን ተጠቅመንበታል:: በቀላሉ አነጋገር እያንዳንዱን ነገርና ሰው እንደማግኔት ሆነን ስበነዋል:: ከስምንት ወራት በኋላ ምስጢሩ የተባለው ፊልም ለዕይታ በቃ::

ፊልሙ አለምን ባዳረሰ ቁጥር ታምራታዊ ትረካዎች ይጎርፉ ጀመር:: ሰዎች ከነባር ህመም ስለመፈወሳቸው፣ ስለጭንቀት፣ ህመም፣ የመኪና አደጋ ከደረሰ በኋላ ቀጥ ብሎ ለመራመድ ስለመቻል፣ በእስከሬን አልጋ ላይ የነበረ በድን ህያው ሆኖ እንደገና ስለመንቃት ጻፉ:: ምስጢሩ ከፍተኛ ገንዘብና በየመልክት ሳጥኑ ቼኮች ያስገኘ ስለመሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ መረጃዎችን አግኝተናል:: ሰዎች ምስጢሩን የተስተካከለ መኖርያቸውን፣ የህይወት አጋሮቻቸውን፣ መኪኖቻቸውን፣ ሥራዎቻቸውን ለማሳየት ተጠቅመውበት በአጭር ጊዜ ውስጥ የተዋጣለት የንግድ ሥራ ሰርተውበታል:: በጭንቀት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ህፃናት ወደሰላማቸው የተመለሱ መሆናቸውን የሚናገሩ ልብን ደስ የሚያሰኙ ታሪኮችም አሉ::

እስከአሁን ካገኘናቸው አስደናቂ ታሪኮች ውስጥ ህፃናት በምስጢሩ የፈለጉትን ነገር፣ ከፍተኛ የትምህርት ውጤትንና ጥሩ ጓደኛን ጨምሮ ለማግኘት እየተጠቀሙበት መሆኑ ይገኝበታል:: ምስጢሩ የህክምና ባለሙያዎች እውቀትን ከህመምተኞቻቸው ጋር፣ ዩኒቨርሲቲዎች ከተማሪዎቻቸው ጋር፣ የጤና ክበቦች ከደንበኞቻቸው ጋር፣ ቤተ-ክርስቲያናትና የእምነት ተቋማት ከምዕመናኖቻቸው ጋር ይጋሩ ዘንድ ገፋፍቷቸዋል:: ምስጢሩ ማንኛውንም ነገር ለመሳብ አገልግሏል::

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሁሉ የሆነው ምስጢሩ የሚለው ፊልም ከተለቀቀ ከጥቂት ወራት በኋላ ነው::

ምስጢሩ የሚለውን ለመፍጠር ያነሳሳኝ በአለማችን በሚገኙ በቢሊዮን ለሚቆጠሩት ሀሴትን ያመጣል በሚል ነው:: የተነሳሳንበትን በጕ ስሜት የምስጢሩ ፊልም ቡድን በጕነቱን ለማወቅ የቻለው ከተለያዩ የአለም ክፍሎች በተለያዩ የዕድሜ ክልል የሚገኙና የሁሉም ብሔር ሰዎች ምስጢሩን በመመልከት ያገኙትን ደስታ በመግለፅ የፃፏቸውን ደብዳቤዎች በማግኘቱ ነው:: በዚህ እውቀት ለማድረግ የማትችለው ምንም ነገር የለም:: ምስጢሩ የምትፈለገውን ማንኛውንም ነገር ያስገኝልሃል ማንም ሁን የትም ሁን::

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ 24 አስደናቂ መምህራን ተገልፀዋል:: ቃሎቻቸው በመላ አሜሪካ በተለያዩ ጊዜአት ፊልም ተነስተዋል:: እንደ አንድ ድምፅ ሆነው ይናገራሉ:: ድምፃቸውም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካትቷል:: የምስጢሩ ታምራዊ ታሪኮችም እንዲሁ ተካትተዋል:: ያለማችሁትን ህይወት እንድትኖሩ ከሚል የተማርኳቸውን የተመቻቹና አቋራጭ ጕዳናዎች አመላክቻለሁ::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማየት እንደሚቻለው ሁሉ በአንዳንድ ቦታ ላይ «አንተ» የሚለውን ቃል አግዝፌዋለሁ:: ይህም የሆነበት ምክንያት አንባቢው ይህን መጽሐፍ የፈጠርኩለት መሆኑን እንዲሰማውና እንዲያውቀው ነው:: አንተ ስል ለአንተ በአካል መናገሬ ነው:: ፍላጎቴ ከመጽሐፉ ገፆች ጋር በእውን ግንኙነት እንዲኖርህ ለማድረግ ነው:: ምክንያቱም ምስጢሩ የተሠራው ለአንተ ነውና::

ገፆችን እያለፍክ በሄድክና ምስጢሩን በተማርክ ቁጥር እንዴት ለማግኘት፣ ለመሆን ወይም አንድ የምትፈልገውን ነገር ለማድረግ እንደምትችል እያወቅህ ትመጣለህ:: እውነተኛ ማንነትህን ለማወቅ ትችላለህ:: ከፊትለፊት የሚጠብቅህን እውነተኛ ታላቅነት ለማወቅ ትችላለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምስጋና

ከእኔ ጋር በመገኘት እንድነሳሳ፣ ስሜት እንዲያድርብኝ፣ ብርሃን እንዳገኝ፣ ገዞዬ የተሳካ እንዲሆንና ይህን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ የላቀ ትብብር ላደረጉልኝ ለሚከተሉት ሰዎች ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ::

ጥበባቸውን፣ ፍቅራቸውንና መለኮታዊነታቸውን ሳይሳሱ ስለአካፈሉኝ ለተባባሪ ደራሲያን ለጆን አስራፍ፣ ሚሼል በርናርድ ቤክዊዝ ፣ ሊ ብሮወር፣ ጃክ ካንፊልድ ፣ ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ፣ ሜሪ ዳያመንድ፣ ማይክ ዱሊይ፣ ቦብ ዶይሉ ፣ ሃል ድወስኪን፣ ሞሪስጉድማን ፣ ዶ/ር ጆን ግሬይ፣ ዶ/ር ጆን ሃገሊን፣ ቢል ሃሪስ፣ ዶ/ር ቤን ጆንሰን፣ ሎራል ላንግማየር፣ ሊዛ ኒኮልስ፣ ቦብ ፕሮክተር፣ ጀምስ ሬይ፣ ዳቪድ ሺርመር፣ ማርሲ ሺሞፍ፣ ዶ/ር ጆ ቫይታል፣ ዶ/ር ዴኒስ ዋይትሊይ፣ ኒል ዶናልድ ቫልሽ እና ዶ/ር ፍሬድ አላን ወልፍ ::

ለምስጢሩ ዝግጅት ቡድን አስደናቂ ስብዕናዎች ፖል ሃሪንግተን፣ ግሌንዳ ቤል፣ ስካይ ባይርን እና ኒክ ጆርጅ::

ለድሬው ሃሪዮት፣ ዳኒኤል ኬር፣ ዳሚያን ኮርቦይ እና ምስጢሩ የሚለውን ፊልም ለማዘጋጀት አብረውን ለተጓዙት ሁሉ፣

ለተደናቂ ንድፍ አጣጣል /ግራፊክስ/ እና ምስጢሩ ከሚያጭረው ስሜት ጋር በማጣመራቸው ለጉዘር ሚዲያዎቹ ጀምስ አርምስትሮንግ፣ ሻሙስ ሆር እና አንዲ ልዊስ፣

ለምስጢሩ ዋና የሥራ አስፈፃሚ መኮንንና ከገነት የተሰጠን ቦብ ራይኖንን፣

ለሚካኤል ጋርዲነርና ከአውስትራሊያ እስከ አሜሪካ የህግ አማካሪ ቡድን ለነበረው ለምስጢሩ የድረ-ገፅ ቡድን::

በልቤ ውስጥ የሚንቦገቦግ ስሜት በውስጤ ለጫሩብኝ ጥንታውያን ሊቃውንት ::



t.me/OLDBOOKSPDF

ልባቸውን ከፍተው ምስጢሩን ለተቀበሉት የቢዮንድ ወርድስ አሳታሚዎች ሪቻርድ ኮህንና ሲንዚያን ብላክ፣ ሄንርይ ከቪና ጁሊ ሽታይገርዋልድት ፡፡

ለካቲ ጉድማን፣ ሱዛን ስሎትና ኮሊን ሃልም፣ የቤሊዝ የተፈጥሮ ኃይል ዲሬክተር ሱዛን ሞሪስ፣ ጀኒ ማክኪይ እና ጆ ሹጋርማ፣ የሚያውቋቸውን ታሪኮች ስላካፈሉን፡፡

ለ ዶ/ር ሮበርት አንቶኒ፣ ዶሪ እና ኤስዜር ሂክስ፣ አብርሃም፣ ዴቪድ ካሜሮን ጊካንዲ፣ ጆን ሃርቸራን፣ ካትራይን ፖንደር፣ ጌይ እና ካቲ ሄንድሪክስ፣ ስቴፈን ኤም አር ኮቢ ፣ አርካት ቶልና ደቢ ፎርድ፣ ስለአነሳሽ አስተምሯቸው ፡፡

ለ ክህራስና ጃኔት አትውድ፣ ማርሲያ ማርቲን፣ የሽግግር መሪዎች ጉባዔ አባላት፣ የመንፈሳዊ ሲኒማ ክበብ፣ የአጋፔ መንፈሳዊ ማዕከል ሠራተኞችና በምስጢሩ የተሳተፉ መምህራን ያላሰለሰ ድጋፍ በማድረጋቸው፡፡

ለተወዳጆቹ ጓደኞቼ ለፍቅራቸውና ያላሰለሰ ድጋፋቸው፡፡
ለአስደናቂው ቤተሰቤና እህቶቼ ወደር የማይገኝለት ድጋፋቸው፡፡

ሴት ልጆቼ ውድ የህይወቴ ፈርጦች ናቸውና በመኖራቸው ብቻ እያንዳንዱን እስትንፋሴን ብርሃንማ ያደርጉታል፡፡ ሃይሌይ የህይወቴ ጅማሮና የእውነተኛ ጉዞው ሃላፊ ስትሆን ስኬይ ኮቴዬን በመከተል ይህን መጽሐፍ በመፍጠርና በብቃት ኤዲት በማድረግ ቃላቶቼን ወደ መጽሐፍ ያወራረሰች ናት፡፡ በመጨረሻም ምስጋናዬ ለነዚህ ሴት ልጆቼ ይድረሳቸው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# የተከሰተው ምስጢር

## ቦብ ፕሮክቶር

(ፈላስፋ፣ ደራሲና የግል አሰልጣኝ)

*ምስጢሩ የፈለከውን ይሰጥሃል፤ ደስታ፣ ጤናና ብልፅግናን ያመጣልሃል::*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

(ኢዛቲታዊ ፈላስፋ፣ የግብይት ባለሙያና ደራሲ)

*የፈለከው ይኖርሃል፣ የፈለከውን ታደርጋለህ ወይም ትሆናለህ::*

## ጆህን አሳራፍ

(ኢንተርፕሬነርና የገቢ አሰባሳቢ ባለሙያ)

*ማንኛውም የመረጥነው ነገር ሊኖረን ይችላል:: ስለግዝፈቱ ግድ የለኝም::*

## ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ

*(ፈላስፋ፣ ወጌሻ፣ ፈዋሽና የግላዊ መለወጥ ስፔሺያሊስት)*

*ይህ ነው የህይወት ታላቁ ምስጢር::*

## ዶ/ር ጆህን ዌትሌይ

(የስነ-ልቦና ባለሙያና በአይምሮ እምቅ ችሎታ መስክ አሰልጣኝ)

*ቀደም ብለው የነበሩት መሪዎች የነበራቸውን የምስጢሩን ኃይል ለማኖር እንጂ ሊያጋሩት አልፈለጉም:: ሰዎች ምስጢሩን እንዳያውቁት አድርገዋል:: ሰዎች ወደስራ በመሄዱ፣ ስራቸውን በመስራት ያለምንም አቅም በአሰልቺ የዕለት ተዕለት ሥራ ተጠምደው ነበር የሚውሉት:: ምክንያቱም ምስጢሩ በጥቂት ሰዎች ተይዞ ስለነበር ነው:: በየታሪክ ዘመኑ የምስጢሩን እውቀት የተመኙ*



t.me/OLDBOOKSPDF

ለያሉ ሰዎች ነበሩ:: ይህን እውቀት ለእለሰም ለማስራጨት መንገድ ያገኙ ሌሎች ብዙዎችም ነበሩ::

**ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ**

(ባለራዕይና የአጋፔ መንፈሳዊ ማዕከል መስራች)

በሰዎች ህይወት ውስጥ ብዙ ታምራትን አይቻለሁ:: ገንዘብነክ ታዕምር፣ የመፈወስ ታዕምር፣ የአእምሮ ህመም የመዳን ታዕምር፣ የግንኙነት መሻሻል ታምርን የመሳሰሉ::

**ጃክ ካንፊልድ**

(ደራሲ፣ መምህር፣ የህይወት አሰልጣኝና ቀስቃሽ ተናጋሪ፣)

ይህ ሁሉ የሆነው ምስጢሩን በጥቅም ላይ ማዋልን በማወቅ ነው::

## ምስጢሩ ምንድን ነው?

**ቦብ ፕሮክቶር**

ምናልባት እዛ ቁጭ ያልከው እየተገረምክ ይሆናል:: ምስጢሩ ምንድን ነው? እኔ እንዴት ልረዳው እንደቻልኩ እነግርሃለሁ::

ሁላችንም የምንሰራው በአንድ ህልቆ መሳፍርት በሌለው ኃይል አማካይነት ነው:: ሁላችንም እራሳችንን የምንመራው ልክ ይህን በሚመስሉ ህጎች ነው:: የአለማችን የተፈጥሮ ህጎች እጅግ እንቅጩን የሚያሳዩ በመሆናቸው መንኮራኩሮችን ስንሰራ፣ ሰዎች ወደ ጨረቃ ስንልክና ለአንድ እንኳን ሳይሳሳት ወደ መሬት የመመለሻቸውን ጊዜ ስንወስን ምንም ችግር የለብንም::

የትም ሁን፣ ህንድ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ፣ ስቶክሆልም፣ ለንደን፣ ቶሮንቶ፣ ሞንትሪያል፣ ወይም ኒው ዮርክ ሁላችንም የምንሰራው በአንድ ኃይል ነው:: በአንድ ህግ ነው:: በመስህብ:: ምስጢሩም የስበት ህግ ነው::

ወደ ህይወትህ የሚመጣ ማንኛውም ነገር ወደ ህይወትህ እንተው የሳብከው ነው:: ወደ አንተ የተሳበውም በአይምሮህ ውስጥ ስለህ

t.me/OLDBOOKSPDF

*በያዝካቸው ምስሎች አማካይነት ነው:: እያሰብከው ያለኸው ነገር ነው:: በአእምሮህ እያውጠነጠንከው ያለው ማንኛውም ነገር ወደ አንተ እየሳብከው ያለኸውን ነው::*

«ማንኛውም አሳቤ እውን የሆነ ነገር ነው»::

ፕሬንቲስ ሙልፎርድ (1834-1891)

የስበት ህግ የአለማችን እጅግ ኃይለኛው ህግ መሆኑን በህይወት የነበሩ እጅግ ታላላቆቹ መምህራን ነግረውናል:: እንደ ዊልያም ሼክስፒር፣ ሮበርት ብራውኒግ እና ዊሊያም ብላክ የመሳሰሉት ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ብለውታል:: እንደ ሉድዊግ ቫን፣ ቤቶቨን የመሳሰሉት ሙዚቀኞች በዘፈናቸው ገልፀውታል:: እንደ ሊወናርዶ ዳቬንቺ የመሳሰሉት ሰአሊያን በስእሎቻቸው አመላክተውታል:: ሶቅራጠስን፣ ፕላቶን፣ ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰንን፣ ፓይታጉረስን፣ ሰር ፍራንሲስ ቤከንን፣ ሰር አይሳክ ኒውተንን፣ ጆን ወልፍጋንግ ፎን ጉይተንና ቪክተር ሁጉን የመሳሰሉት ፈላስፎች በጽሑፎቻቸውና አስተምሮዎቻቸው አዳርሰውታል:: የሁሉም ስሞች ህያው ናቸው:: በታሪክም እንደተዘከሩ ይኖራሉ::

እንደ ሂንዱይዝም፣ የሄርሜቲክ ልማዶች፣ የቡድሃ እምነት፣ የአይሁድ እምነት፣ ክርስትናና እስልምናን የመሳሰሉት ሃይማኖቶችና የባቢሎኖችንና ግብፆችን የመሳሰሉት ስልጣኔዎች በፅሑፎቻቸውና ታሪኮቻቸው ገልፀውታል:: በተለያዩት ቅርፆቹ በሁሉም ዘመናት እንደተዘገበው የስበት ህግ በሁሉም ምዕተ አመታት በጥናታውያን ጽሑፎች ውስጥ ይገኛል:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3000 በድንጋይ ላይ ተፅፎ ተገኝቷል:: ምንም እንኳን ይህን እውቀት ቢመኙትም፣ በእርግጥም ተመኝተውታል፣ ማንም ሊያገኘው በሚችልበት መልኩ ሁልጊዜም እዛው የሚገኝ ነበር::

ህጉ ከጊዜ ጋር የጀመረ ነው:: ሁልጊዜም እዛው የነበረና ሁልጊዜም የሚኖር ነው:: የአለምን ስርአት የህይወት ተሞክሮህን የሚወስን ህግ ነው:: የትም ሁን ማን የስበት ህግ የህይወትህን ተሞክሮ የሚሰራው እርሱ ነው:: ይህ ኃያል ህግ ያን ሁሉ የሚያደረገው በአሳቢዎችህ

t.me/OLDBOOKSPDF

አማካይነት ነው:: የስበት ህግ ወደ ተግባር እንዲመጣ የምትጠራው አንተ ነህ:: ይህን የምታደርገው በአሳቤዎችህ አማካይነት ነው::

ቻርለስ ሃኔል በ1921 የስበት ህግን «እጅግ ታላቁና የማያብል ጠቅላላውን የፍጥረት ስርዓትን የሚወስን ህግ ነው» ሲሉ ገልፀውታል::

## ቦብ ፕሮክቶር

*ጥበበኞች ይህን ሁልጊዜም ያውቁታል:: ወደኋላ መለስ ብለህ ወደባቢሎኖች መሄድ ትችላለህ:: ይህን ሁሉም ያውቁት ነበር:: የሚያውቀው ግን የተወሰኑ የጥቂት ሰዎች ቡድን ነበር:: ጥንታውያን ባቢሎኖችና ታላቁ ብልፅግናቸው በምሁራን ደህና ሁኖ ተዘግበላቸዋል:: ባቢሎናውያን ከሰባቱ የአለም አስደናቂ ነገሮች አንድ የሆነውን የተንጠለጠለ የአበድ ቦታ በመስራታቸውም ይታወቃሉ:: የአለምን ህግ በማወቃቸውና በአግባቡ በጥቅም ላይ በማዋላቸው በታሪክ እጅግ ባለፀጋ ዘሮች ለመሆን ቻሉ::*

## ቦብ ፕሮክቶር

*አንድ በመቶ የሚሆነው የህዝብ ክፍል ወደ 96 በመቶ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን ያገኛል ብለህ ለምንድን ነው የምትገምተው? ይህ አጋጣሚ ይመስልሃል? እንደዚያ እንዲሆን የተነደፈ ነው:: የሆነ ነገር ይገባቸዋል:: ምስጢሩ ገብቷቸዋል:: እናም አንተም አሁን ምስጢሩ ማለት ምን እንደሆነ እንዲገባህ እየተደረገ ነው::*

በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሀብትን በህይወታቸው ያከማቹ ሰዎች ምስጢሩን የተጠቀሙ ናቸው:: ስለመትረፍረፍና ብልፅግና አሳቤዎች እያወጠነጠኑ የዚህ ተቃራኒ ሃሳብ በአእምሮአቸው ሥር እንዲሰድ ሳይፈቅዱ ነው እንዲያ መሆን የቻሉት:: ትልቁ ሃሳባቸው ሀብትን የሚመለከት ነው:: በአእምሮአቸው የሚያውቁት ነገር ሀብት ብቻ ነው:: ሌላ ምንም ነገር በአእምሮአቸው ውስጥ አይኖርም:: ተገነዘቡትም አልተገነዘቡትም ብቸኛው አሳቢአቸው የብልፅግና አሳቤአቸው ነው:: ሀብትን የሚያመጣላቸው የስበት ህግ በተግባር ሲሰራ ማለት ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

ምስጢሩንና የስበት ህግን ለማስረጃነት ትክክለኛው ምሳሌ ይህ ነው። ሀብት ያገኙ መልሰው ያጡና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደገና ያገኙ ሰዎችን ታውቅ ይሆናል። ምንድን ነው እዚህ ላይ የሆነው አወቁትም አላወቁት የእንዲህ አይነት ሰዎች ዋናው ሃሳብ በሀብት ላይ ነው። ለዚህም ነው በመጀመሪያ ባለፀጋ የሆኑት። አከታትለውም ሀብቴ ሁሉ ቢጠፋስ የሚል የፍራቻ ስሜት ማሳደር ይጀምሩና ይኸው እሳቤ ዋናው ጭንቀታቸው እየሆነ ይመጣል። ስለ ብልፅግና የነበራቸውን ሃሳብ ወደማጣት ሃሳብ ይለውጡትና ያገኙትን ሁሉ ያጡታል። ካማጣት በኋላ የአጣለሁ ፍርሃት አብሮ ይወገድና እየቆየም ስለብልፅግና ማሰብ ይጀመራሉ። ብልፅግናም ይመለሳል። ምንም ይሁን ምን ህጉ የአስተሳሰቦችህ አፀፋዊ መልስ ነው።

## ማንኛውም ነገር አምሳያውን ይስባል

### ጆህን አሳራፍ

*የስበት ህግን ለማየት ለእኔ ቀላሉ መንገድ እራሴን እንደማግኔት ማየት ስችልና ማግኔት ወደ እራሱ የሚስብ መሆኑን ሳውቅ ነው። በአለም አንተን የሚያክል ሃይለኛ ማግኔት የለም። በውስጥህ በአለም ከማንኛውም ነገር የበለጠ ኃይል ያለው ማግኔታዊ ኃይል አለ። ይህ ቅፅበታዊ ማግኔታዊ ኃይል የሚመነጨው በእሳቤዎችህ አማካይነት ነው።*

### ቦብ ዶይል

(ደራሲና የስበት ህግ ልዩ ባለሙያ)

*በትክክል ሲቀመጥ የስበት ህግ ማንኛውም ነገር አምሳያውን ይስባል ይላል። እናም ባሰብክ ቁጥር ተመሳሳይ አሳቦችን እየሳብክ ነው።*

በአንድ ያላስደሰተህ ጉዳይ ላይ ማሰብ ጀምረህ ታውቃለህ? ስለዚሁ ጉዳይ የበለጠ እያሰብክ በሄድክ ቁጥርስ ነገሩ የባሰ አስቀያሚ ይመስልሃል? ይህ የሚሆነው አንድን ነገር በቋሚነት ባሰብከው ቁጥር የስበት ህግ ተጨማሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

አምሳያ አሳቤዎችን ያመጣብሃልና ነው:: በደቂቃዎች ውስጥ አያ የማያስደስቱ አምሳያ ሃሳቦች ይከተላሉና ሁኔታው ሁሉ የበለጠ መባ ይሆናል:: የበለጠ እያስብክበት በሄድክ ቁጥር የበለጠ እየተበሳጨ ትሄዳለህ::

የሃሳብ አምሳያን የመሳብ ተሞክሮ አንድን ዘፈን እንደሰማህ አጋጥሞ ሊሆን ይችላል:: ያን ዘፈን ከሰማህ በኋላ ዘፈኑ ከአይምሮህ አልወ ይልሃል:: እየደጋገምክ በውስጥህ ታዜመዋለህ:: ስታዜመ ባይታወቅህም የማሰብ አትኩሮትህን በሙሉ ከዘፈኑ ላይ ታደርጋለህ: እንዲህ በማድረግህ የዚያን ዘፈን አምሳያ አሳቤዎችን እየሳብክ ነው: በመሆኑም የስበት ህግ ወደ ተግባር ይሸጋገርና የዛን ዘፈን አምሳ ሃሳቦች አሁንም አሁንም ያስከትላል ማለት ነው::

## ጆህን አሳራፍ

እንደ ሰው ሥራችን የሚሆነው የምንፈልጋቸውን ሃሳቦች ይዞ መገ ት ነው:: በአይምሯችንም ውስጥ የምንፈልገውን ነገር በግልፅ ማስቀመጥም ይኖርብናል::

ይህንም በማድረጋችን እጅግ ታላላቅ ከሆኑት ህግጋት ውስጥ አንዱ የሆነውን የስበት ህግ እንዲኖረን እናደርጋለን:: እናም በእጅጉ ያስብክባቸውን ነገሮች ትሆናለህ:: ነገር ግን እጅግ ያስብክባቸው ነገሮችንም ትስባቸዋለህ:: የአሁኑ ህይወትህ ያለፉ ሃሳቦችህ ነፀብራቅ ነው:: በዚህ ውስጥ እጅግ ታላላቅና አርባና-ቢስ ያልካቸው ነገሮች ይካተታሉ:: በከፍተኛ ሁኔታ ያስብክባቸውን ነገሮች ስለምትስብ ህይወትህን በሚመለከት በእያንዳንዱ ነገር ላይ ያለህን አብይ ሃሳብ ለመገንዘብ ትችላለህ:: ምክንያቱም በተሞክሮህ ውስጥ አልፈዋልና ነው:: እስከአሁንም ድረስ ምስጢሩን እየተማርከው ነው:: በምታገኘው እውቀትም ማንኛውንም ነገር ለመለወጥ ትችላለህ::

## ቦብ ፕሮክቶር

*በአይምሮህ ውስጥ የሚታይህ ከሆነ በእጅህ ውስጥ ማስገባትም ትችላለህ:: በአይምሮህ ውስጥ ስለምትፈልገው ነገር ማሰብ*

t.me/OLDBOOKSPDF

*የምትችልና ዋናው ሃሳብህም ይኸው ከሆነ ወደእውነተኛው ህይወትህ እንዲመጣ ታደርገዋለህ::*

## ማይክ ዱሌይ

(ደራሲና የአለም አቀፍ ተናጋሪ)
*ያ መርህ በሶስት ቀላል ቃላት ሊጠቃለል ይችላል:: ሃሳቦች ቁሳዊ ነገሮች ሆኑ:: በዚህ እጅግ ከባድ በሆነው ህግ አማካይነት ሃሳቦችህ የህይወትህ ቁሳቁሶች/ነገሮች ይሆናሉ:: ሃሳቦች ቁሳዊ ነገሮች ሆኑ የሚለውን ለእራስህ ደጋግመውና በንቃተ ህሊና ግንዛቤህ ውስጥ አርፎ እንዲቀመጥ አድርግ::*
ሃሳቦችህ ቁሳዊ ነገሮች ሆኑ::

## ጆህን አሳራፍ

*ብዙ ሰዎች የማይረዱት ነገር ቢኖር ሃሳብ ተደጋጋሚ መሆኑን ነው:: ሃሳብን መለካት እንችላለን:: እናም አሁንም አሁንም የሆነ አዲስ ሞዴል መኪና አለኝ ፣ የምፈልገውን ያህል ገንዘብ አለኝ፣ እንዲህ አይነት ኩባንያ እየከፈትኩ ነው፣ የሚስማማኝ አይነት ጓደኛ አግኝቻለሁ፣ ወዘተ ብለህ እያሰብክ ከሆነ ያን ድግግሞሽ ያለማቋረጥ እየረጨህ ነው ማለት ነው::*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

ሃሳቦች ያን ሁሉ ማግኔታዊ ንዝረት ይልኩና አቻ ሃሳብን ወደ አንተ መልሰው ያመጣሉ::

> «ዋናው ሃሳብ ወይም የአእምሮ አዝማሚያ ማግኔቱ ነው:: ህጉም አምሳያ አምሳያውን ይስባል የሚለው ነው:: በመሆኑም የአእምሮ አዝማሚያ ለእራሱ ተፈጥሮ በግልባጩ ተመጣጣኝ የሆኑ ሁኔታዎችን ይስባል»::
>
> ቻርለስ ሃኔል (1866-1949)

t.me/OLDBOOKSPDF

ሃሳቦች ማግኔታዊ ናቸው:: የመደጋገም ባህሪም አላቸው:: ስታስ
እነዚያ ሃሳቦች ወደ ውጨው አለም ይላኩና በማግኔታዊ ቅጽበ
አምሳያቸው የሆኑ ነገሮችን ሁሉ መሳብ ይጀምራሉ:: ነገሮቹ
በተመሳሳይ የድግግሞሽ ፍጥነት ላይ የሚገኙ ናቸው:: ወደ ውጭ
የተላከ ነገር ሁሉ ወደ ምንጩ ይመለሳል:: ምንጩም አንተው ነህ::

በዚህ መንገድ አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ ስርጭቱን የሚያደርገ
በድግግሞሽ አማካይነት ነው:: ይህም ስርጭት በቤት ውስጥ በሚገ
ቴሌቪዥን ላይ ወደ ምስሎች ይለወጣል:: አብዛኞቻችን እንዴት እንደዚ
እንደሚሆን ላናውቅ እንችላለን:: ነገር ግን እያንዳንዱ ቻናል ፍሪኩንሲ
ያለው መሆኑን እናውቃለን:: ፍሪኩንሲውን ስናስተካክልም ምስሎቹ
በቴሌቪዥኑ ላይ ለማየት እንችላለን:: ፍሪኩንሲውን የምንመርጠው
ቻናሉን በመምረጥ ነው:: በመሆኑም ለቻናሉ የተላኩ ምስሎችን እናገኛ
ለን:: በቴሌቪዥናችን የተለያዩ ምስሎች ማየት ከፈለግን ቻናሉን
እንቀይርና ወደ አዲስ ፍሪኩንሲ እንዞራለን/እናስተካክላለን::

ሰብአዊ የማሰራጫ ጣቢያ ነህ:: የምታስተላልፍበት ፍሪኩንሲ ከተሞችን፣
አገሮችን አለምን አልፎ ይደርሳል:: በመላው አለምም ያስተጋባል:: ያን
ፍሪኩንሲም በሃሳቦችህ አማካይነት እያስተላለፍክ ነው:: በማስተላለፍ
የምታገኛቸው ምስሎች እንደ ቴሌቪዥኑ ምስሎች የሚታዩ አይደሉም::
የህይወት ስዕሎች ናቸው እንጂ:: ሃሳቦችህ ፍሪኩንሲውን ሰሩ:: አምሳያ
ነገሮችንም ወደ ፍሪኩንሲው ሳቡ:: ተመልሰውም የህይወትህ ምስሎች
ሆነው ወደ አንተው ተመለሱ::

> «የአእምሮ ኃይል ንዝረቶች እጅግ የተጣሩ በመሆናቸው
> ኑሮአቸውም እንዲሁ እጅግ ከባድ ነው»
>
> ቻርለስ ሃኔል

## ቦብ ፕሮክቶር

*የተትረፈረፈ ህይወት እየኖርክ ለእራስህ ከታየህ ይህን ኑሮ
ትስበዋለህ:: ሁልጊዜና ለማንም ሰው ይህ ይሰራል የተትረፈረፈ
ህይወት እየኖርክ ባሰብክ ቁጥር:: ነገር ግን ሁሉም ሰው ያለመው*

t.me/OLDBOOKSPDF

*አይነት ህይወት የማይኖረው ለምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም::*

## ከማይረባው ይልቅ መልካሙን ሳብ

### ጆህን አሳራፍ

*እዚሀ ላይ ነው ችግሩ:: አያሌዎች ስለማይፈልጉት ነገር ያስባሉ:: ለምን አሁንም አሁንም ብቅ ጥልቅ እንደሚልባቸውም ይደነቃሉ:: ሰዎች የፈለጉት ነገር የማይኖራቸው ምክንያት ከሚፈልጓቸው ነገሮች ይልቅ ስለማያስፈልጓቸው ነገሮች ስለሚያውጠነጥኑ ነው:: ሃሳቦችህን አዳምጣቸውና የምትናገራቸውን ቃላትም አዳምጥ:: አምሳያነት አላቸው:: ህጉ ፍፁማዊ ነው:: ስህተቶችም አይገኙም::*

የሰው ልጅ በህይወቱ አይቶት የማያውቅ በሽታ ለአመታት ሰውን ሲያወድም ኖሯል:: የማይፈለግ በሽታ ነበር:: ሰዎች ይህን በሽታ ያመጡት በአብዛኛው ስለማያስፈልጋቸው ነገር በማሰብ፣ በማውራትና በማተኮራቸው ነው:: ይህ ትውልድ ግን ታሪክን የሚለውጥ ነው:: ምክንያቱም ከዚህ አይነት በሽታ ነፃ የሚያደርግ እውቀት እያገኘ ነውና:: በአንተ ይጀመራል:: ስለምትፈልገው ነገር ብቻ የምታስብና የምታወራ ሆነህ የዚህ አዲስ ግንዛቤ ጀማሪ ልትሆን ትችላለህ::

### ቦብ ዶይል

*አንድ ጥሩ ይሆናል የምትለውን ነገር በአእምሮህ አውጠንጠንክ አላውጠነጠንክ የስበት ህግ ደንታ አይደለም ወይም የሆነ ነገር ፈለክ አልፈለክ የህጉ ጉዳይ አይደለም:: ለአሰብከው አፀፋ መስጠት ብቻ ነው ደንታው:: ስለሆነም የእዳ ክምር እየታየህ በዚህ ሳቢያ ውጥረት ውስጥ ከገባህ ለቀረው የውጪ አለም ይኸኑ እያስተላለፍክ ስመሆኑ ምልክት ነው ማለት ነው:: «ብተጫነኝ እዳ ሳቢያ መልካም ነገር አይሰማኝ» ስትል ለእራስህ ማረጋገጥህ ነው:: በተለያዩ የስብዕና*

t.me/OLDBOOKSPDF

ደረጃዎችህ ስሜቱ ይኖራል። አሁስህ የምታገኘውም ነገር ቢኖ ይህኑ ስሜት ነው።

የስበት ህግ የተፈጥሮ ህግ ነው። ህያው ባለመሆኑ መጥፎና ጥሩ ነገሮች አይታዩትም። ከእራስህ ሃሳቦች በመነሳት እነዚህኑ ሃሳቦች የህይወትህ ተሞክሮ አድርጎ መልሶ ወዳንተው ያንሀባርቃቸዋል። የስበት ህግ የሚሰጥህ ነገር ቢኖር የምታስባቸውን ነገሮች ብቻ ነው።

## ሊዛ ኒኮልስ

(ደራሲና እራስ የማስቻል ወኪል)

*የስበት ህግ ታዛዥ ነው። ስለምትፈልጋቸው ነገሮች ስታስብና ሙሉ በሙሉ አትኩሮት ስታደርግባቸው የስበት ህግ ልክ እንደፈለከው በፈለከው ጊዜ ይሰጥሃል። በሚያስፈልጉህ ነገሮች ላይ ካተኮርከም የስበት ህግ የማትፈልግ መሆንህን አያዳምጥም። የምታስባቸውን ነገሮች ያሳይሃል። አሁንም አሁንም ብቅ ያደርጋቸዋል። የስበት ህግ በመፈለግና ባለመፈለግ መካከል አይለይም አያደርግም። የፈለገውን ይሁን በአንድ ነገር ላይ ካተኮርክ ያ ነገር እንዲከሰት ጥሪ ማድረግህ ነው።*

አትኩሮትህን በአንድ በሆነ የምትፈልገው ነገር ላይ ስታደርግና ያን አትኩሮትም ሙጥኝ ብለህ በትይዝ በዚያ ወትት የምትፈልገውን ነገር ከኃያል ኃይል ጋር እየጠራህ ነው። የስበት ህግ አታድርግ፣ የለም፣ አይደለም ወይም ምንም አይነት የአሉታ ቀመር አይነድፍም። የአወንታና አሉታ ቃላትን ስትናገር ለስበት ህግ የሚደርሰው ይኸው ነው።

«በዚህ ቀዳዳ በኩል ምንም ነገር መድፋት የለብኝም»።
«በዚህ ቀዳዳ በኩል የሆነ ነገር መድፋት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ነገሮችን መድፋት እፈልጋለሁ»።

«ፀጉሬን መጥፎ አድርጌ መቆረጥ አልፈለግም»።
«መጥፎ የፀጉር አቆራረጥ እፈልጋለሁ»።

t.me/OLDBOOKSPDF

«መዘግየት አልፈለግም»::
«መዘግየት እፈልጋለሁ»::

«ያ ሰው ባለጌ እንዲሆንብኝ አልፈልግም»::
«ያ ሰውዬና ሌሎች ሰዎችም ባለጌ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ»::

«የምግብ ቤቱ ጠረጴዛችን ለሌላ እንዲሰጥብን አልፈልግም»::
«የምግብ ቤቱ ጠረጴዛችን እንዲሰጥ እፈልጋለሁ»::

«እነዚህ ጫማዎች እንዲጉዱኝ አልፈልግም»::
«ጫማ እንዲጉዳኝ እፈልጋለሁ»::

«ይህን ሁሉ ለመስራት አልችልም»::
«ከምችለው በላይ ሥራ እንድሰራ እፈልጋለሁ»::

«ጉንፋን እንዲይዘኝ አልፈልግም»::
«ጉንፋንና ሌሎች ነገሮችም እንዲይዙኝ እፈልጋለሁ»::

«መከራከር አልፈልግም»::
«የበለጠ መከራከር እፈልጋለሁ»::

«እንደዚያ ብለህ አትናገረኝ»::
«አንተም ሆንክ ሌሎች እንዲያ ብላችሁ እንድትናገሩኝ እፈልጋለሁ»::

የስበት ህግ የሚሰጥህ የምታስበውን ነገር ነው:: በቃ!

## ቦብ ፕሮክቶር

*አመንክም አላመንክም፣ ገባህም አልገባህ የስበት ህግ ሁሌጊዜም ይሰራል:: የስበት ህግ የአፈጣጠር ህግ ነው:: የኳንተም ፊዚክስ ምሁራን አለም በነቂስ ከሃሳብ የመጣች ናት ይሉናል:: ህይወትህን በአሳቤዎችህና በስበት ህግ አማካይነት ትፈጥራለህ:: እያንዳንዱ ሰው በእራሱ እንደዚሁ ያደርጋል:: ስለዚህ ማወቅህ ብቻ ምንም አይሰራም:: በህይወትህና በሌሎች ህይወትም በማንኛውም የታሪክ*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ወትት እየሰራ ያለ ነው:: ስለዚህ ግዙፍ ሳታውቅ የቱን ያህ*
*የምትደንቅ ኃየል እንደሆንክ ታውቃለህ::*

## ሲዛ ኒኮልስ

*የሰበት ህግ ማሰብ እስካላቆምክ ድረስ መስራቱን አያቆምም:: በማን*
*ውም ሃሳብህ መፍሰሱን ባላቆመበት ጊዜ ሁሉ የስበት ህግ እየሰራ*
*ነው:: ስለአለፈው ስታስብ የስበት ህግ እየሰራ ነው:: ስለ አሁኑ*
*ወደፊቱም ስታስብ ህጉ በመስራት ላይ ነው:: የማያቋርጥ ሂደት*
*ነው:: ተግ በል፣ አቁም የሚል ቁልፍ አትጫንም:: ማሰ*
*እንደማያቋርጥ ሁሉ ሁልጊዜም በመተግበር ላይ ነው::*

ይታወቀንም አይታወቀን አብዛኛውን ጊዜ እናስባለን:: ለአንድ ሰው
እያወራህም ይሁን ያን ሰው እያዳመጥከው ባለበት ወቅት እያሰብ
ነው:: ጋዜጣ እያነበብክም ይሁን ቴሌቪዥን እያየህ ታስባለህ:: ያለ
ትውስታዎችህን ስትቀሰቅስም ታስባለህ:: እንዲህ ይሆናል ብለ
የወደፊቱን ስታስታውስ ታስባለህ:: መኪና እያሽከረከርክ ታስባለህ
በጧት ከመኝታህ ተነስተህ ለሥራ ስትዘጋጅ እያሰብክ ነው
ለአብዛኞቻችን የማናስብበት ወቅት በእንቅልፍ ላይ ስንሆን ነው
ተኝተንም ቢሆን ግን የስበት ኃይሎች ቀደም ተብሎ በታሰቡ ጉዳዮች ላይ
መሥራታቸውን አያቆሙም:: ይልቅየስ ከመኝታህ ቀደም ብለው
የነበሩትን ሃሳቦች መልካም ሃሳቦች አድርጋቸው::

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ሁልጊዜም መፍጠር አለ:: አንድ ግለሰብ ምንጊዜም ያስባል ወይም*
*እሳቤዎች አሉት:: ከእነዚህ ሃሳቦች የሆነ ነገር ይከሰታል:: አሁን*
*የምታስበው የወደፊት ህይወትክን ይፈጥራል:: ህይወትህን*
*የምትሰራው በሃሳቦችህ ነው:: ማሰብ ስለማታቆም ሁልጊዜ*
*ትፈጥራለህ:: በአብዛኛው ያሰብከው ወይ ያተኮርክበት ነገር ህይወትህ*
*ሆኖ የሚከሰተውን ነው::*

እንደማንኛውም የተፈጥሮ ህግ በዚህኛውም ህግ ፍፁምነት አለ
ህይወትህን ትፈጥራለህ:: የዘራኸውን ታጭዳለህና ሃሳቦችህ አዝርዕት

t.me/OLDBOOKSPDF

ናቸው፣ የምትሰበስበው መኸርም በተከልካቸው አዝርዕት ላይ ጥገኛ ነው።

እያጉረመረምክ ከሆነ የስበት ህግ እንድታጉረመርም የሚያደርጉ አያሌ ሁኔታዎችን ያመጣብሃል። ሌላ ሰው እያጉረመረመ እና በዛም ላይ ተጠምዶ ሳለ እያደመጥክ፣ ስሜቱንም እየተጋራሁና ተስማምተህ ከሆነ በእዛው ወቅት እራስህን እንድታጉረመርም የሚያደርጉ ብዙት ያላቸው ሁኔታዎችን ትጠራለህ/ትስባለህ።

ህጉ እያደረገ ያለው በሃሳብህ አትኩሮት ያደረክበትን ነገር በማንፀባረቅ መልሶ ለአንተው መስጠትን ነው። የዚህን ህግ እንዲህ ማድረግ በማወቅ የህይወትህን ማንኛውንም ሁኔታና አጋጣሚ መለወጥ ትችላለህ። የአስተሳሰብህን ጉዳና በመለወጥ ማለት ነው።

## ቢል ሃሪስ

(መምህርና የሴንተርፖይንት የምርምር ተቋም መስራች)

*ሮበርት የሚባል በኢንተርኔት የማስተምረው ተማሪ ነበረኝ። አልፎ አልፎ በኤሌክትሮኒክ የመልዕክት መስመሬ ,የገኘኝ የነበረው ሮበርት ግብረ-ሰዶም የሚፈፅም ሰው ነበር። አንድ ጊዜ አሳዛኝ ህይወቱን ዘርዝሮ በኢ-ሜል ላከልኝ። የስራ ባልደረቦቹ አደሙበት። እጅግ ጠምደውት ስለነበር ጭንቀት አመጣበት። ቁልቁል ወርዶ በሚሄድበት ወቅት ሰው የሚጠሉ ሰዎች በመንገድ አጋጠሙትና የሆነ ችግር ሊፈጥሩበት ሆነ። ኮሜዲያን ለመሆን ፈልጎ አንድ የሚያስቅ ድራማ ይዞ ብቅ ሲል ግብረሰዶም የሚፈፅም መሆኑን የሚያውቁ ሰዎች ተተናኮሉት። ጠቅላላ ህይወቱ ደስታ-ቢስ ነበር። ይህ የሆነበትም ዋናው አትኩሮት ግብረ-ሰዶም የሚፈፅም በመሆኑ ነበር።*

*ሮበርት አትኩሮት ያደረገው በማይፈልገው ጉዳይ ላይ መሆኑን ማስተማር ጀመርኩ። የላከልኝን ኢ-ሜል አሳየሁትና ደግሞ እንዲያነበው ጠየኩት። «ተመልከት የላክልኝ የማትፈልገውን ነገር*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ሁሉ ነው» አልኩት:: «ስሜታዊ ነህ» አልኩት :: «አንድን ነገር በተመሰጦ ስሜት ካየኸው እንዲያውም ፈጥኖ ይደርስብሃል» አልኩት:: ሰማኝ:: በልቡ ወደሚፈልገው ነገር ማተኮርን መለማመድ ጀመረ:: ከስድስትና ስምንት ሳምንት በኋላ ታምር ታዬ:: ይጠሉት የነበሩት የስራ ባልደረባዎቹ አንድም ወደተለያዩ ቦታዎች ተቀየሩለት ካለዚያም እርግፍ አድርገው ተውት:: ስራውን መውደድ ጀመረ:: በመንገድ የሚያስቃየው አንድም ሰው ጠፋ:: የሚያስቅ ድራማውንም ሲያሳይ በሚተናኮሉት ፋንታ አድናቂዎቹ ተበራከቱ::*

ህይወቱ እንዲህ የተለወጠው በማይፈልገው ጉዳይ ላይ ከማተኮር ይልቅ በሚፈልገው ላይ በማተኮሩ ነው:: የሮበርት ህይወት የተለወጠው አስተሳሰቡን ስለለወጠ ነው:: ወደ አለም ለየት ያለ ፍሪኩንሲ ስለረጨ ነው:: ሁኔታው የቱንም ያህል የማይሆን ቢመስልም አለም የአዲሱን ፍሪኩንሲ ምስሉች መስጠት ነበረባት:: የሮበርት አዲስ ሃሳቦች አዲስ ፍሪኩንሲዎች ሆኑና የህይወቱ ጠቅላላ ሥዕል ተቀየረ::

ህይወትህ በእጅህ ነው:: በአሁኑ ሰአት የትም ሁን በህይወትህ ምንም ነገር ይከተል አስተሳሰብህን ነቅተህ መምረጥ ትችላለህ:: እናም ህይወትህን ትለውጣለህ:: ተስፋ የሚያስቆርጥ ምንም ሁኔታ የለም:: እያንዳንዱ የህይወትህ ጉዳይ ይለወጣል::

## የአይምሮህ አቅም /ኃይል/

### ሚካኤል በርናርድ በክዊዝ

*በንቃተ-ህሊናህ የያዝካቸውን ዋና ዋና ሃሳቦች ወደ እራስህ ትስባቸዋለህ:: ሃሳቦችህን ቀደም አድርገህ አወካቸውም አላወካቸው አሁን ግን እየተገነዘብካቸው ነው:: አሁን ስለምስጢሩ ስታውቅ ጭልጥ አድርጐ ወስዶህ ከነበረው እንቅልፍ እየነቃህና እየተገነዘብክ ነው:: ስለማወቅህ፣ ስለህጉና በሃሳቦችህ አማካይነት ስለአለህ አቅም ሁሉ ትረዳለህ::*

t.me/OLDBOOKSPDF

## ዶ/ር ጆህን ደማርቲኒ

*ምስጢሩን በሚመለከትና የአይምሯችንና የፍላጐታችንን ኃይል ጠንቅቀህ ብታይ ሁሉም ከእኛው ጋር ሆነው ታገኛቸዋለሁ:: አይናችንን መክፈትና ማየት ብቻን ነው ማድረግ ያለብን::*

## ሊዛ ኒኮልስ

*የስበት ህግን የትም ታየዋለሁ:: ማንኛውንም ነገር ወደ እራስህ አቅርብ:: ሰዎችን፣ ሥራን፣ አካባቢን፣ ጤናን፣ ሀብትን፣ እዳን፣ ደስታን፣ የምትነዳውን መኪና፣ የምትኖርበትን መንደር እነዚህን ሁሉ ወደ እራስህ አምጣቸው:: ሁሉንም እንደማግኔት ትስባቸዋልሁ:: ያሰብከበትን ነገር ሁሉ ታገኘዋለሁ:: ጠቅላላው ህይወትህ በጭንቅላትህ ውስጥ የሚውጠነጠኑት ሃሳቦች መከሰቻ ነው::*

ይህ አለም የሁሉም እንጂ የተወሰኑት ብቻ አይደለም:: የስበት ህግ የማይመለከተው ምንም ነገር የለም:: ህይወትህ ወሳኝ የሆኑ ሃሳቦችህ መስታወት ነው:: ህያው የሆኑ ነገሮች ሁሉ የሚሰሩት በስበት ህግ አማካይነት ነው:: ሰው የሚለየው የሚረዳ አይምሮ ስለአለው ነው:: ነፃ ፍላጐቱንና ሃሳቦቹን ለመምረጥ ይጠቀምበታል:: ሆን ብሎ ያስባል:: ጠቅላላ ህይወቱንም በአይምሮው ውስጥ መፍጠር ይችላል::

## ዶ/ር ፍሬድ አለን ወልፍ

(የኳንታም ፊዚክስ ባለሙያ፣ ሌክቸረርና ተሸላሚ ደራሲ)
የምነግራችሁ ከገማች ቀውስነት ተነስቼ አይደለም:: ጥልቀት ካለው መሠረታዊ መገንዘብ ተነስቼ እንጂ:: ኳንታም ፊዚክስ ይህን በማመላከት ይጀምራል:: አይምሮ ያልታከለበት አለም ሊኖር አይችልም ይላል:: ቀጥሎም አይምሮ የተመለከተውን ነገር ሁሉ ቅርፅ ያሲዛል ይላል::

በአለም እጅግ ኃይለኛ የማሰራጫ ጣቢያ ነህ ተብሎ ቢታሰብ ከዶ/ር ወልፍ ጋር የተስማማ ሃሳብ እንዳለህ ለማየት ትችላለህ:: አይምሮህ ያስባል:: የሃሳብ ምስሎቹም የህይወትህ ተሞክሮ ሆነው ተመልሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

ያስተላልፋሉ:: ህይወትህን በሃሳቦችህ መፍጠርህ ብቻ አይደለም ሃሳቦችህ አለምን ለመፍጠር ጠንካራ አቅምም ይጨምራሉ:: «በዚህ አለም ምንም ማድረግ የማልችል ኢምንት ነኝ» ብለህ አስበህ ከሆነ እንደገና መልሰህ አስብ:: አይምሮህ በእርግጥ በዙሪያህ የሚገኘውን አለም ቅርፅ ያሲዛል::

ባለፉት ስምንት አመታት የታዩት የኳንታም ፊዚክስ አስደናቂ ስራና ግኝቶች የሰው ልጅ አይምሮ ከፍተኛ የመፍጠር ኃይል ያለው መሆኑን እንድንረዳ አግዘውናል:: ሥራዎቹ ናርነጂ፣ ኤመርሰን፣ ሼክስፒር፣ ባኮን፣ ክሪሽናሙርቲ እና ቡደሃ ካሉት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው::

## ቦብ ፕሮክቶር

*ህጉን አልተረዳኸውም ማለት አልቀበልም አልክ ማለት አይደለም:: ስለኮረንቲ ምንም ላታውቅ ትችላለህ:: ኮረንቲ የሚሰጣቸውን ጥቅሞች ከአገልግሎት ላይ ለማዋል ግን የሚከለክልህ የለም:: ስለኮረንቲ አሰራር አላውቅም ነገር ግን ኮረንቲን በመጠቀም የአንድን ሰው እራት ማዘጋጀት እንደሚቻል አውቃለሁ::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ስለታላቁ ሚስጥር መረዳት ሲጀምሩ አብረዋቸው ያሉት አሉታዊ አስተሳሰቦች ያስፈሯቸዋል:: አንድ አውንታዊ ሃሳብ ከመቶ በላይ አንድን አሉታዊ ሃሳብ የሚበልጥ መሆኑ መረጋገጡን መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: ይህ ግንዛቤ የተወሰነ ጭንቀትን እዛው ላይ ለማስወገድ ይረዳል::*

የሆነ አሉታዊ ነገር ወደ ህይወትህ ለማምጣት አያሌ አሉታዊ ሃሳቦችንና የማያቋርጥ አሉታዊ አስተሳሰብን የግድ ይላል:: ነገር ግን አሉታዊ አስተሳሰብን ላልተቋረጠ ጊዜ ከቀጠልክበት በህይወትህ ውስጥ መከሰት ይጀምራል:: ለምን አሉታዊ ሃሳብ ገጠመኝ ብለህ የምትጨነቅ ከሆነ የበለጠ ጭንቀት ይከተልሃል:: መልካም መልካሙን ነው የማሰብ ብለህ ከአሁኑ ወስን:: በተጨማሪም መልካም አስተሳሰቦችህ ጠንካራና አሉታዊ አስተሳሰቦች ግን ደካማ መሆናቸውን ለቀሪው አለም አውጅ::

t.me/OLDBOOKSPDF

## ሊዛ ኒኮልስ

*እግዚአብሄር የተመሰገነ ይሁንና ሁሉም ነገር በታሰበበት ወቅት ሳይሆን ዘግይቶ የሚሆን ነው:: የታሰበው ሁሉ ያኔውኑ እውን አይሆንም:: እንዲያ ቢሆን ኖሮ ችግር ይገጥመን ነበር:: መዘግየት የሚጠቅምበት ጊዜ አለ:: እንደገና እንድትፈትሽ፣ እንድታስብና የምትፈልገውን እንድታይና አዲስ ምርጫ እንድታደርግ ያስችልሃል::*

ህይወትህን የምትፈጥርበት ሁሉም አቅምህ የሚገኘው አሁን ነው:: ምክንያቱም እያሰብክ ያለኸው አሁን ነውና:: የማይጠቅም ሃሳብ ተከስቶብህ ከሆነ አሁኑኑ አስተሳሰብህን ለውጥ:: ቀዳሚ ሃሳብህን ሰርዘህ በአውንታዊ አዲስ ሃሳብ ለመተካት ትችላለህ:: አዲስ አስተሳሰብ በማፍለቅ አዲስ ፍሪኩንሲ መርጨት አሁን ስለምትችል ጊዜ ይጠቅምሃል::

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*የህይወትህ የበላይ ኃላፊ አንተው ስለሆንክ ሃሳቦችህን ለመገንዘብና ተጠንቅቀህ መርጠህ ለመዝናናት ትሻለህ:: የህይወትህ ሚካኤል አንጀሎ አንተው ነህ:: የዳዊትን ቅርፅ የምትቀርፀው አንተ ነህ::*

በአይምሮህ ላይ የበላይነት ለማሳደር አንደኛው መንገድ አይምሮን መተው ነው:: ያለምንም ልዩነት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ መምህራን ተመስጦን እንደየዕለት ተዕለት ተግባር ይሰሩታል:: ምስጢሩን ከተረዳሁ በኋላ ነበር ተመስጦ ያን ያህል ኃይል ያለው መሆኑን ያጤንኩት:: ተመስጦ ከአይምሮህ ይለይሃል:: ሃሳብህን እንድትቆጣጠር ያደርጋል:: ሰውነትህንም እንደገና ያበረታዋል:: ትልቁ ነገር ለመመስጥ ረጅም ሰአት መመደብ የሌለብህ መሆኑ ነው:: በመጀመሪያ ጊዜ ከሶስት እስከ አስር ደቂቃ በቀን የሚበቃ ሲሆን ይህም ሃሳብህን ለመቆጣጠር ያስችላል::
ስለሃሳቦችህ ግንዛቤ እንዲኖርህ «እኔ የአስተሳሰቦቼ የበላይ አለቃ ነኝ» የሚል ስሜት ማጫር ትችላለህ:: ሁልጊዜ ተናገረው:: ተመስጥበት:: ያን

t.me/OLDBOOKSPDF

ስሜት ሙጭጭ አድርገህ ስትይዝ በስበት ህግ አማካይነት ስሜትህን ትሆናለህ።

አሁን ወሳኝነት ያለውን የራስህን አምሳያ ለመፍጠር የሚያስችልህ እውቀት እያገኘህ ነው። ወሳኝነት ባለው አምሳያህ ፍሪኩንሲ ላይ አምሳያህን የመሆን እድል እንዳለ ተረዳ። ምን መሆን፣ ለመሆን፣ ለማድረግና እንዲኖርህ እንደምትፈልግ ወስን። ፍሪኩንሲውንም እርጨው። ራዕይህ ህይወትህ ይሆናል።

## ማጠቃለያዎች

- የህይወት ትልቁ ምስጢር የስበት ህግ ነው
- የስበት ህግ አምሳያ አምሳያውን ይስባል ይላል። ስለሆነም አንድ ነገር ስታስብ አምሳያ አስተሳሰብን እየሳብክ ነው።
- አስተሳሰቦች ማግኔታዊ ናቸው። ፍሪኩንሲም አላቸው። ስታስብ አስተሳሰቦችህ ወደ አለም ይላኩና በተመሳሳይ ፍሪኩንሲ ላይ የሚገኙ ተመሳሳይ አስተሳሰቦችን እንደማግኔት ይስባሉ። ወደ ውጭ የተላከ ማንኛውም ነገር ወደ ምንጩ፣ ወደ አንተ ይመለሳል።
- አንተ የማሰራጫ ጣቢያ አይነት ነህ ፍሪኩንሲ ከአስተሳሰቦችህ ጋር የምታሰራጭ። በህይወትህ ማንኛውንም ነገር ለመለወጥ ከፈለክ አስተሳሰብህን በመለወጥ ፍሪኩንሲውን ለውጥ።
- የአሁን አስተሳሰቦችህ የወደፊት ህይወትህን ይፈጥራሉ። እጅግ አዘውትረህ የምትስበው ወይም የምታተኩርበት በአብዛኛው ህይወትህ ሆኖ ይከሰታል።
- አስተሳሰቦችህ ቁሳዊ ነገሮች ይሆናሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምስጢሩ ቀላል ተደረገ

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ልክ እንደ ግራቪቲ ህግ የመሳሰሉ ህግጋት ባሉበት አለም ውስጥ እንኖራለን። ከአንድ ህንፃ ላይ ብትወረወር ደግ ሰው ሆንክ አልሆንክ ወደ መሬቱ ወድቀህ መከስከስህ አይቀርም። የስበት ህግ የተፈጥሮ ህግ ነው። እንደግራቪቲ ህግ ከሰው ሰው የማይለይና የማያዳላ ነው። ግልፅና እርግጠኛ ነው።*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*በህይወትህ አሁን ከቦህ የሚገኝ ነገር ሁሉ የምትነጫነጭበትንም ጨምሮ የሳብከው ነው። ይሰማኛል መጀመሪያ ስትሰማው እንደሚያስጠላህ። «መቼም የመኪና አደጋ እንዲደርስብኝ አልጠራም » ትላለህ። ወዲያው «እንዲህ የሚነዛነዝ ደንበኛ አልስብም» ትላለህ ። «ብድር እንዲኖርብኝ ፈልጌ አልጠራም» ልትል ትችላለህ። እራስህ የጠራሃቸው ናቸው እልሃለሁ። ይህ ነው አንደኛው እጅግ አስቸጋሪው ፅንሰ ሃሳብ። ከተቀበልከው በኋላ ግን ህይወትን የሚቀይር መሳሪያ ነው።*

ምስጢሩን የሚመለከተውን ይህን አይነት ክፍል ሰዎች ሲሰሙ በዚህ ውስጥ ህይወታቸው ያለፉ አያሌ ሰዎችን ያስታውሳሉ። እነዚያ ሁሉ ሰዎች የህይወታቸው መጥፎያዎችን ሳቡ ብሎ ለማመን ይቸገራሉ። ሰዎቹን ፣ ህይወት ያጠፉትን ነገሮች እራሳቸውን በምናባቸው ላይቀርጿቸው ይችላሉ። ነገር ግን የአስተሳሰቦቻቸው ፍሪኩንሲ ከሆነው አጋጣሚ ጋር ተዛምዷል። ሰዎች ባልሆነ ስአት ካልሆነ ቦታ እውላለሁ ብለው ካመኑና ሁኔታዎቹን ለመቆጣጠር ካልቻሉ የፍርሃት፣ የመነጠልና የአቅመ-ቢስነት አስተሳሰባቸው ካላቋረጠ ባልሆነ ጊዜና ቦታ መሆንን ይስባሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁኑኑ መወሰን ትችላለህ:: በማንኛውም ወቅት መጥፎ ነገር ቢያጋጥምህ እድልህ ሆኖ ይመስልሃል? ባልሆነ ጊዜና ቦታ ላይ እሆናለሁ ብለህ ለማመን ትፈልጋለህ? ሁኔታዎቹን ለመቆጣጠር አትችልም? ወይስ የህይወት ተሞክሮህ በእጅህ ውስጥ መሆኑን ማመንና ማወቅ ትፈልጋለህ? የምታስበው እንዲያ በመሆኑ በህይወትህ የሚያጋጥምህ ደጋደጉ ነገር መሆኑስ? ምርጫው የአንተ ነው:: እንዲሆን የፈለከው ሁሉ የህይወትህ ተሞክሮ ይሆናል:: አንተው በማያቋርጥ ሃሳብ ካልጠራኸው በስተቀር ምንም ነገር በእውኑ ህይወትህ አይመጣም::

## ቦብ ዶይል

*አንዳንዶቻችን የምንስበው በስህተት ነው:: ለመቆጣጠር ያልቻልን ይመስለናል:: አስተሳሰቦቻችንና ስሜቶቻችን እየተሽከረከሩ በመሆኑ ሁሉም ነገር በስህተት ወደኛ ይመጣል:: አንድን የማይፈለግ ነገር ማንም ሰው ይሁን ብሎ ወደራሱ አይስብም:: ስለምስጢሩ እውቀት ከሌለህ በህይወትህና በሌሎች ህይወት ላይ የማይፈለጉ ነገሮች እንዴት ሊከሰቱ እንደቻሉ ለማየት ሊቀልህ ይችላል:: እንዲህ አይነት አስተሳሰብ የሚመጣው የአስተሳሰባችን ታላቅ የመፍጠር ችሎታን ለመረዳት ካለመቻል ነው::*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ስለዚህ ለመስማት የመጀመሪያህ ከሆነ አሁን እየተሰማህ ያለው «አስተሳሰቤን መቆጣጠር አለብኝ» የሚል ስሜት ነው:: የመጀመሪያው እንዲያ ሊሆን ይችላል:: ጨዋታው የሚጀመረውም ያን ጊዜ ነው:: ጨዋታው ወደ ሚስጥሩ የሚወስዱ አያሌ አቋራጮች መኖራቸው ነው:: የውጤታማዎች ውጤታማ የሆነውን አቋራጭ መምረጥ አለብህ:: ንባብህን ቀጥልና ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ታያለህ::*

## ማርሲ ሺሞፍ

(ደራሲ፣ አለማቀፋዊ ተናጋሪና የለውጥ መሪ)

*እያንዳንዱን አስተሳሰብ መቆጣጠር አይቻልም:: በቀን ጠዐ ... ሺህ የሚደርሱ ሃሳቦች እንደሉ ...*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ሁለት ሃሳቦች ብትቆጣጠር የቱን ,የሀል ድክም እንደምትል ለመገመት ትችላለህ? እንደመልካም አጋጣሚ ሆኖ ቀላል መንገድ አለ:: ስሜቶቻችን ምን እንደምናስብ እንድናውቅ ያደርጋሉ::*

የስሜት ጥቅም አንስ የሚታይ አይደለም:: ስሜቶችህ ህይወትህን እንድትጋፈጥ የሚረዱህ ወሳኝ መሳሪያዎች ናቸው:: አስተሳሰቦችህ የማንኛውም ነገር ቀዳሚ ሳቢያዎች ናቸው:: በዚህ አለም የምታየውና የምትሞክረው ማንኛውም ነገር ውጤት ነው:: ይህም ስሜቶችህን ይጨምራል:: የዚህ ውጤት ሳቢያ/ምክንያት ምንጊዜም አስተሳሰቦችህ ናቸው::

## ቦብ ዶይል

*ስሜታዊነት የምናስበውን እንድናውቅ የሚያደርግ አስገራሚ ስጦታ ነው::*

ስሜቶችህ ፈጥነው ምን እያሰብክ እንደሆነ ይነግሩሃል:: የሆነ መጥፎ መጥፎ ወሬ እንደሰማህ የተሰማህ ስሜት ወዲያው ሲሰወር አስብ:: ያ በሆድህ የነበረው ስሜት ቅጽበታዊ ነበር:: በመሆኑም ነው ስሜቶችህ ምን እያሰብክ እንደሆነ የሚያሳውቁህ ቀዳሚ ምልክቶች ናቸው የሚባለው:: ምን እየተሰማህ እንደሆነ ለመረዳትና ከሚሰማህ ጋር እራስህን ለማጣጣም ትፈልጋለህ:: ምክንያቱም ምን እያሰብክ እንደሆነ ለማወቅ እጅግ ቀልጣፋው መንገድ ስሜትህ ስለሆነ ነው::

## ሊዛ ኒኮልስ

*ሁለት አይነት ስሜቶች አሉህ:: አንደኛው የጥሩና ሌላኛው ደግሞ የመጥፎ ስሜቶችህ ስለሆኑ ሁለቱንም ታውቃቸዋለህ:: መጥፎ ስሜቶች የሚባሉት ድብርት፣ ቁጣ፣ ተቃውሞ፣ ፀፀት፣ ወዘተ ናቸው::*

በማንኛውም ወቅት የሚሰማህን የምታውቀው አንተው በመሆንህ ማንም ጥሩ ወይም መጥፎ ተሰማህ ብሎ ሊነግርህ አይችልም:: ምን እየተሰማህ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆነ በእርግጠኝነት ለማወቅ ከተቸገርክ እራስህን ጠይቅ:: «ም
እየተሰማኝ ነው?» በል:: ቀን ላይ ቆም ብለህ ይህን ጥያቄ ጠይቅ
እንዲያ ስትጠይቅ ምን እየተሰማህ እንደሆነ ትገነዘባለህ::

ማወቅ የሚገባህ ነገር ቢኖር መጥፎ ስሜት እያለህ በዚያው ላይ ተደር
መልካም አስተሳሰብ ሊኖር የማይችል መሆኑን ነው:: ይህማ ህግ
የሚጥስ ይሆናል:: ምክንያቱም የስሜቶችህ ሳቢያ/ምክንያ
አስተሳሰቦችህ ናቸውና ነው:: መጥፎ እየተሰማህ ከሆነ መጥፎ ስሜት
እንዲያድርብህ የሚያደርጉ አስተሳሰቦችን እያውጠነጠንክ ነው::

አስተሳሰቦችህ ፍሪኩንሲህን ይወስናሉ:: ስሜቶችህ ወዲያው ምን
አይነት ፍሪኩንሲ ላይ እንዳለህ ይነግሩሃል:: መጥፎ እየተሰማህ ከሆነ
ተጨማሪ መጥፎ ነገሮችን በሚጋብዝ ፍሪኩንሲ ላይ ነህ:: የስበት ህግም
የመጥፎ ምስሎችንና መጥፎ ስሜት የሚያጭሩብህን ነገሮች መልሶ
ወደአንተ በመላክ አፀፋ ማድረግ ይኖርበታል::

መጥፎ እየተሰማህና አስተሳሰብህን ቀይረህ የተሻለ ስሜት እንዲያድርብህ
ማድረግ አልችል ባልክ ቁጥር «የበለጠ የከፋ ስሜት የሚያጭሩብኝ
ተጨማሪ ሁኔታዎችን ስጠኝ » እያልክ ነው:: «አምጣው! » እያልክ
ነው::

## ሊዛ ኒኮልስ

*የሃኛው ግልባጭ ደግሞ መልካም ስሜታዊነትና ስሜቶች አለህ የሚለው ነው:: መቼ እንደመጡ ታውቃለህ:: ጥሩ እንዲሰማህ ያደረጉ በመሆናቸው:: በእያንዳንዱ ቀን ፊንጠዝያ፣ ደስታ ፣ ፍሰሃ፣ ፍቅር ቢሰማን ብለህ ገምት:: መልካም ስሜቶችህን በምታንቆለጳጵስበት ወቅት ተጨማሪ መልካም ስሜቶች ወደ አንተ ይመጣሉ:: ጥሩ ስሜት የሚያመጡልህ ነገሮችም እንዲሁ::*

## ቦብ ዶይል

*እጅግ ቀላል ነው:: «በዚህች ሰአት ምን እያሰብክ ነው?» መልካም፣ እንዴት ነህ? «ደህና ነኝ» ጥሩ፣ ቀጥል::*

t.me/OLDBOOKSPDF

በአንድ ጊዜ ጥሩ ስሜት ለማሳደርና አሉታዊ አስተሳሰቦች፣ ለማግኘት አይቻልም። ጥሩ እየተሰማህ ከሆነ መልካም አስተሳሰቦችህን እያውጠነጠንክ ነው። ይታይሃል፣ በህይወትህ ማንኛውም ነገር ሊኖርህ ይችላል። ወሰን የለውም። አንድ ነገር ግን መያዝ አለብህ። መልካም ሊሰማህ ይገባል። ስታስተውለው ትፈልገው የነበረው ነገር ይህን አልነበረምን? ህጉ በእርግጥ የማያብል ነው።

## ማርሲ ሺሞፍ

*ጥሩ እየተሰማህ ከሆነ ምኞትህን የያዘ መጪ ዘመንን እየፈጠርክ ነው። መጥፎ ከተመኘህ ከምኞትህ ያፈነገጠ መፃኢ ዘመን እየፈጠርክ ነው። እያንዳንዱን ቀን ስታሳልፍ የስበት ህግ በየሴኮንዷ እየሰራ ነው። የምናስበውና የሚሰማን ነገር ሁሉ መፃኢ ዘመናችንን ይፈጥራል። ተጨንቀህ ወይም ፈርተህ ከዋልክ ቀኑን ሙሉ የበለጠ ስትጨነቅና ስትፈራ እንደዋልክ እወቅ።*

ጥሩ እየተሰማህ ከሆነ መልካም አስተሳሰቦችን እያውጠነጠንክ መሆን አለበት። እናም ተጨማሪ መልካም ነገሮችን መልሶ የሚያመጣልህ ኃይለኛ ፍሪኩንሲ እየረጨህ ነው። እነዚህ መልካም ነገሮች በተራቸው ጥሩ ስሜት ያመጡልሃል። ጥሩ ስሜት የተሰማህበትን ወቅት አትልቀቀው። አስበው። ጥሩ በተሰማህ ቁጥር ጠንክረህ መልካም ነገሮችን ወደራስህ እየሳብክ መሆኑን ተገንዘብ።

አንድ እርምጃ ወደፊት እንሂድና ስሜቶችህ ምን እያሰብክ እንደሆነ እንድታውቅ ከአለም የተላኩ መልዕክቶች ቢሆኑስ?

## ጃክ ካንፊልድ

*ስሜቶቻችን በጉዳዩ ፣ በጉዳናው ላይ መሆን አለመሆናችንን የሚጠቁሙን መረጃ መጋቢ መሳሪያዎች ናቸው።*

አስተሳሰቦችህ የማንኛውም ነገር ቀዳሚ መንስኤ መሆናቸውን አስታውስ። እናም ሳታቋርጥ ስታስብ ወደያውኑ ወደ ውጪ አለም

t.me/OLDBOOKSPDF

ይላካል:: ያ አስተሳሰብ ከሚመጥነው ፊሪኩንሲ ጋር ማግኔታዊ መስጠፍን ያመጣል:: ወደያውኑ የዚያን ፍሪኩንሲ ንባብ ወደ ስሜቶችህ መልሶ ይልካቸዋል:: በሌላ አባባል ስሜቶችህ ከውጭው አለም የተላኩልህ መልዕክቶች ናቸው:: አሁን ያለህበትን ፍሪኩንሲም ይነግሩሃል:: ስሜቶችህ የፍሪኩንሲን መረጃ ማግኛ መንገድ ናቸው::

ጥሩ ስሜት እየተሰማህ ከሆነ «መልካም አስተሳሰቦችን እያውጠነጠንክ ነው» የሚል መልዕክት ከአለም መጣልህ ማለት ነው:: እንደዚሁም መጥፎ ከተሰማህ «መጥፎ ሃሳቦች እያውጠነጠንክ ነው» የሚል መልዕክት ከአለም ተላከልህ ማለት ነው::

በመሆኑም መጥፎ ሲሰማህ «ማስጠንቀቂያ! አሁን ማሰብ አቁም:: አሉታዊ ፍሪኩንሲ መዘገብህን አቁም:: ፍሪኩንሲ ቀይር:: ክስተቶችን ቀንስ:: ማስጠንቀቂያ! » የሚል መልዕክት ከውጪው አለም ይላክልሃል::

በሚቀጥለው ጊዜ መጥፎ ከተሰማህ ወይም አሉታዊ ስሜታዊነት ካደረብህ ከውጪው አለም የሚላክልህን መልዕክት አዳምጠው:: በዛ ወቅት በአሉታዊ ፍሪኩንሲ ላይ በመሆንህ የሚከለክልህን መልካም ነገር ሁሉ ገድበህ አታስደርስም:: አስተሳሰብህን ቀይር:: ስለጥሩ ነገር አስብ:: ጥሩ ስሜቶችህ ሲያንሰራሩ እራስህን ወደ አዲስ ፍሪኩንሲ መቀየርህ ይታወቅሃል:: አለምም በተሻሉ ስሜቶች ይህኑ ታረጋግጣለች::

## ቦብ ዶይል

*ከምታስበው ይልቅ የሚሰማህን ነው የምታገኘው:: ለዚህም ነው ሰዎች ከመኝታቸው እንደተነሱ አውራ ጣታቸውን በመውጋት መጥመዝመዝ የሚጀምራቸው:: ቀኑን ሙሉ እንዲሁ ያሳልፉታል:: ስሜታዊነታቸውን ትንሽ ለጠጥ ቢያደርጉት ቀኑን በሙላ መቀየር እንደሚችሉ የሚያሳያቸው ምንም ምልክት የላቸውም::*

*ቀኑን ስትጀምር በደስታ ከሆነና ስሜትህን የሚለውጥ ምንም ነገር ካላጋጠመህ በስበት ህግ መሠረት የደስታ ስሜትህን እንደነበረ የሚያስቀጥሉ ተጨማሪ ሁኔታዎችንና ሰዎች መሳብህን ትቀጥላለህ::*

t.me/OLDBOOKSPDF

*አንድ መጥፎ አጋጣሚ በሌላ የተተካበት ብዙ አጋጣሚዎችን አይተናል:: አውቀኸውም ይሁን ሳታውቅ ሰንሰለቱ የጀመረው በአንድ ሃሳብ ነው:: አንዱ መጥፎ ሃሳብ ሌሎች መጥፎ ሃሳቦችን ሲጉትት ፍሪኩንሲው የዚጋና የተሳሳተ ነገር ይከተላል:: ለዚያ የተሳሳተ ነገር አፀፋ ስትመልስ ሌሎች ስህተቶችን ትስባለህ:: ሆን ብለህ አስተሳሰብህን በመለወጥ ከዚያ ፍሪኩንሲ ወጥተህ መሄድ ካልቻልክ ሰንሰለቱ አይበጠስም:: ይቀጥላል::*

አስተሳሰብህን ወደምትፈልገው ለመለወጥ ትችላለህ:: ፍሪኩንሲህን ለመለወጥህ በስሜቶችህ ታረጋግጣለህ:: የስበት ህግም አዲሱን ፍሪኩንሲ መጥኖ በመያዙ የህይወትህን አዲስ ምስሎች ወደ አንተው መልሶ ይልክልሃል:: እዚህ ላይ ነው ስሜቶችህን ከጥቅም ላይ በማዋል በህይወትህ የምትፈልገውን ለማግኘት እቅም መስጫ አድርገህ የምትጠቀምበት::

ስሜቶችህን እንዲያውም ከፍ ያለ ፍሪኩንሲ ለማስተላለፍ ትጠቀምባቸዋለህ:: ይህም የሚሆነው በምትፈልገው ላይ ስሜትን በማከል ነው::

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*የጤናማነት ስሜት አሁኑኑ መሰማት ሊጀምርህ ይችላል:: የባለፀጋነት ስሜትም እንዲሁ:: እንደተመኘኸው አይነት ስሜት አልሰማህ ካለ ስሜቶችህን በማዳመጥ ላይ አተኩርና ወደ ጠቃሚነት ከፍ አድርጋቸው:: እራስህን ከፍ ለማድረግ በማለት አጠንክረህ በስሜቶችህ ላይ ስታተኩር ስሜቶችህን ራሳቸውን ከፍ ታደርጋቸዋለህ:: እንደዚህ ለማድረግ አንደኛው መንገድ አይንህን በመዝጋት ከሚያሳስቱ እይታዎች መቆጠብና በሚሰማህ ላይ በማተኮር ነው:: ለደቂቃም ቢሆን ፈገግታ ይኑርህ::*

## ሊዛ ኒኮልስ

አስተሳሰቦችህና ስሜቶችህ ህይወትህን ይፈጥራሉ:: ሁሌም እንዲሁ ነው:: የተረጋገጠ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ እንደግራቪቲ ህግ በመሳሳቱና በዚያን ቀን የግራቢቨቲ ህ
እንዳይሰራ በመርዳቱ ምክንያት አሳሞች ክንፍ አውጥተው ሲ
አታይም:: በተመሳሳይ የስበት ህግም ምንም ልዩነት አያደርግም:: አ
ነገር ወደ አንተ ከመጣ አንተ ነህ ያመጣኸው በተራዘመ ማሰብ:: የስ
ህግ ግልፅ ያለ ነው::

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

ለመዋጥ ሊያስቸግር ይችላል:: ነገር ግን፣ እራሳችንን አዘጋጅተ
ለነገሩ ክፍት ስንሆን ውጤቱ እጅግ አስደንጋጭ ይሆናል:: ይህ አን
በህይወትህ ቦታ የነበረው አስተሳሰብ የግንዛቤ ለውጥ ስታደር
እንዳልነበረ ይሆናል እንደማለት ያለ ነው::

ማንኛውንም ነገር የመለወጥ አቅም አለህ:: ምክንያቱም ሃሳቦችህ
መምረጥ የምትችለውና ስሜቶችህን ለይተህ የምታውቅ አንተ
ስለሆንክ ነው::

«እየኖርክ የራስህን አለም ትፈጥራለህ»
ዊንስተን ቸርች

## ዶ/ር ጆ/ቫይታል

*ጥሩ ከተሰማህ በእርግጥ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ይህ ጥሩ
ስሜት ነው ወደ ውጭው ሄዶ ቅስቀሳ በማድረግ መሰል ተጨማሪ
ነገሮችን ወደ አንተ የሚያመጣልህ:: ስለሆነም የበለጠ ጥሩ ሊሰማህ
ከቻለ ተጨማሪ መልካም ስሜት እንዲኖርህ የሚረዱ ነገሮችን
ትስባለህ:: እራስህንም ከፍ ከፍ ታደርጋለህ::*

## ቦብ ፕሮክቶር

*ክርስስ ስትል ወዲያውኑ መመለስ የምትችል መሆኑን ታውቅ ነበር?
ቆንጆ ሙዚቃ አዳምጥ ወይም ማንጐራጐር ጀምር:: ስሜታዊነትህን
ይለውጠዋል:: ወይም ስለአንድ ቆንጆ ነገር አስብ፤ ስለ አንድ
የምትወደው ህፃን ወይም የምትመካበትን ሰው ማንሰላሰል ጀምር::*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ዖን ሃሳብ በውስጥህ አቆየው፡፡ ሁሉንም ነገር ዝጋና ይህን ሃሳብ ብቻ ያዝ፡፡ ጥሩ ስሜት ሲሰማህ እንደሚጀምር ላረጋግጥልህ እችላለሁ፡፡*

እድኒዎችህን የሚሰበስቡልህ የምስጢር ቀናፊዎች ዝርዝር አዘጋጅ፡፡ ስሜትህን ወዲያውኑ የሚያስለውጡ ነገሮችን ማስቴ ነው፡፡ ቆንጆ ትውስታዎች፣ መፃኢ-ክንቶች፣ አስቂኝ ወቅቶች፣ ተፈጥሮ፣ የምትወደው ሰው፣ የምታደንቀው ሙዚቃ ፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተናደድክ ወይም ጥሩ ባልተሰማህ ጊዜ ወደዚህ ዝርዝር መለስ በልና ባንዱ ላይ አትኩሮትህን አድርግ፡፡ የተለያዩ ነገሮች ወደተለያዩ በተለያዩ ጊዜአት ይለዋወጡሃል፡፡ አንደኛው ካልሠራ ወደ ሌላኛው ዙር፡፡ እራስህንና ፍሪኩንሲህን ለመቀየር የሚወስድብህ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ብቻ ነው፡፡

# ፍቅር የስሜቶች ሁሉ ስሜት

## ጀምስ ሬይ

(ፈላስፋ፣ ሌክቸረር፣ ደራሲና የብልፅግናና የሰው እምቅ ኃይል ፕሮግራም መስራች)

*እንደምሳሌ ብንወስደው ጥሩ መስማት ለቤት እንስሳቶችህም ይሰራል፡፡ እንስሳት በሚገርም የስሜት ሁኔታ ላይ ስለሚከቱህ እጅግ የሚገርሙ ናቸው፡፡ ለእንስሳቱ ፍቅር ስታሳያቸው ፍቅሩ ለአንተም ህይወት መልካሙን ሁሉ ያስገኝለታል፡፡ የሚገርም ስጦታ ነው፡፡*

> «የአስተሳሰብና ፍቅር ቅይጥ ነው ማንም የማይገድበውን የስበት ህግ ሃይል የሚሰራው»
>
> ቻርለስ ሀቨል

ከፍቅር የበለጠ ኃያል በምድር ላይ አይገኝም፡፡ የፍቅር ስሜት ለመርጨት የምትችለው እጅግ ከፍተኛው ፍሪኩንሲ ነው፡፡ ሁሉን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሃሳብህን በፍቅር ብታደርገው፣ ሁሉንም ሰውና ነገር ማፍቀር ብትጎ ህይወትህ ይለወጣል::

ለነገሩ አንዳንድ ቀደምት ተመራማሪዎች የስበትን ህግ የመውደድ ሲሉ ገልፀውታል:: ተመራመርና ለምን እንዳሉ ትደርስበታለህ:: ስለአን ሰው ደግ ነገር ካላሰብክ ያን ደግ ያልሆነ አስተሳሰብህን ታገኘዋለ ባለማሰብህ እራስህን እንጂ ማንንም አትጐዳም:: መውደድን ብታስ ማን ተጠቃሚ እንደሚሆን ገምት:: አንተው ነህ:: እናም ዋናው ሁኔታ የማያፈቅር ከሆነ የስበት ህግ ወይም ህገ-መውደድ አጠንክሮ መል ይሰጥሃል:: ምክንያቱም እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍሪኮንሲ ላይ ስለሆነ ነው:: ከፍተኛ የፍቅር ስሜት ባደረብህና በረጨህ ቁጥር የበለጠ አቅ ታገኛለህ::

> «የስበት ህግ ሌላው ሰው ህገ-ፍቅር የሆነው ሃሳብ ከአንፀባረቀ ነገር ጋር የመዛመዱን መርህ ስለሆነም እያንዳንዱን የሰ ተሞክሮ የሚያዘው መሆኑን ያሳየናል:: ይህ ሁሉንም ነገ የሚመለከት ዘለዓለማዊና መሠረታዊ መርህ ነው:: በሁሉም ፍልስፍና፣ ሃይማኖትና ሳይንስ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው ከዚህ ፍቅረ-ህግ ማፈግፈግ አይቻልም:: ለአስተሳሰብ ብርታት የሚሰጥ ስሜት ነው:: ስሜት ፍላጐት ሲሆን ፍላጐትም ፍቅ ነው:: አስተሳሰብ በፍቅር ሲጠረዝ የማይደፈር ይሆናል::»
>
> ቻርለስ ሀኔል

## ማርሲ ሺሞፍ

*አስተሳሰብህንና ስሜቶችህን በትክክል መቆጣጠር ስትጀምር የራስህ እውነተኛ አለም መፍጠር ጀመርክ ማለት ነው:: ነገነትህም ያለው እዚህ ነው:: አቅምህ ሁሉ ያለውም እዚህ ነው::*

*ማርሲ ሺሞፍ የታላቁን አልበርታነስታይን አባባል ይጋራል:: «የሰው ልጅ ሁሉ እራሱን መጠየቅ ያለበት ይህች አለም ተስማሚ ናትን ብሎ ነው::»*

የስበት ህግን ካወቅን የምንሰጠው መልስ «አዎ ይህች አለም ተስማሚ ናት» የሚል ይሆናል:: ለምን? ምክንያቱም በስበት ህግ መሠረት እንዲህ ብለህ ስታስብ ተስማሚነቷ ያጋጥምሃልና ነው:: አልበርታነስታይን እንዲህ አይነት ጥያቄ ያነሳው ሚስጥሩን ስለሚያውቀው ነው:: ጥያቄውን በመጠየቅ እንድናስብና ውሳኔ እንድናሳልፍ እንደሚገፋፋን ያውቅ ነበር:: ጥያቄውን በማንሳቱ ብቻ ትልቅ እድል ሰጥቶናል::

የአልበርታንስታይንን ፍላጐት የበለጠ በማስፋት ይህች አለም ገናና ናት ብለህ ማረጋገጥና፣ ማወጅ ትችላለህ:: ይህች አለም ታላቅ ናት:: መልካሙን ነገር ሁሉም ታመጣልኛለች፣ አለም በማንኛውም ጉዳይ ታብርልኛለች፣ በማንኛውም ነገር ትደግፈኛለች፣ ፍላጐቴንም ፈጥና ታሟላልኛለች በማለት አረጋግጥ :: ይህች አለም ወዳጅህ መሆኗን እወቅ::

## ጃክ ካንፊልድ

*ስለምስጢሩ ከተማርኩና ለህይወቴ ጥቅም ማዋል ከጀመርኩበት እንስቶ ህይወቴ በእውነት ታምራዊ መሆን ጀምሯል:: ሁሉም ሰው ለመኖር የሚመኘው ህይወት እኔ በየቀኑ የምኖረውን አይነት ነው ብዬ አስባለሁ:: የምኖረው 4.5 ሚሊዮን ዶላር በሚገመት መኖሪያ ውስጥ ነው:: የምሞትላት ሚስት አለችኝ:: በአለም ውስጥ በሚገኙ አስገራሚ ቦታዎች የእመት እረፍቴን አደርጋለሁ:: ተራራዎችን ወጥቻለሁ:: ሳፋሪዎችን ጎብኝቻለሁ:: ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ስለሚስጥሩ በማወቄ ነው::*

## ቦብ ፕሮክቶር

*ህይወት ፍፁም ክስተታዊ መሆን ይችላል:: መሆንም አለበት:: ይሆናልም:: ይህ የሚሆነውም ሚስጥሩን መጠቀም ስትጀምር ነው::*

ህይወትህ ይህ ነው እስከምትረዳው ድረስ ይጠባበቅህ የነበረው:: እስካሁን ህይወት አስቸጋሪና ትግል እንደሆነ አድርገህ አስበህ ይሆናል:: በስበት ህግ መሠረትም ያሰብከውን አይነት ህይወት ልትኖር ትችላለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁኑኑ ለእለም «ህይወት እጅግ ቀላል ነው:: ህይወት እጅግ ጥሩ ነው:: ጥሩ ነገሮች ሁሉ ያጋጥሙኛል» ብለህ በጩኸት አሰማ::

በውስጥህ እንድታገኘው እየጠበቀ ያለ አንድ እውነት አለ:: ይህም እውነት «ህይወት መስጠት ያለባትን ጥሩ ነገር ሁሉ ታገኛለህ» የሚል ነው:: ይህን ጉዳይ ሲጀመርም ታውቀዋለህ:: ምክንያቱም መልካም ነገር ሳያጋጥምህ ሲቀር የሚሰማህን አለመመቸት ታውቀዋለህና ነው:: ጥሩ ነገሮች የተፈጥሮ መብቶችህ ናቸው:: አንተ የራስህ ፈጣሪ ነህ:: የስበት ህግ በህይወትህ የምትፈልገውን ለማግኘት የሚረዳህ መሳሪያ ነው:: ወደህይወት ሚስጥርና ወደ ራስህ ለአሳዊነት እንኳን ደህና መጣህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- የስበት ህግ የተፈጥሮ ህግ ሲሆን ልክ እንደ ግራቪቲ ህግ ለማንም አይወግንም፡፡
- እራስህ ጉትተህ ካልሳብከው በስተቀር ምንም ነገር ወደ ተሞክሮህ አይመጣም
- ስለምታስበው ነገር ለማወቅ ምን እየተሰማህ እንደሆነ ተመራመር፡፡ ስሜታዊነቶች ጠቃሚ መሳሪያ ናቸው፡፡ ምን እያሰብን እንደሆነ ቀድመው ስለሚነግሩን፡፡
- መጥፎ እየተሰማን መልካም አስተሳሰብ ሊኖረን አይችልም፡፡
- አስተሳሰብህ ፍሪኩንሲህን ይወስናል፡፡ የሚሰሙህ ስሜቶችም በፍጥነት በየትኛው ፍሪኩንሲ ላይ እንደሆንክ ይነግሩሃል፡፡ መጥፎ ሲሰማህ የበለጠ መጥፎ ነገሮች በሚስብ ፍሪኩንሲ ላይ ነህ፡፡ ጥሩ ሲሰማህ የበለጠ መልካም ነገሮችህን ሞጥረህ እያስጠጋህ ነው፡፡
- አስደሳች ትዝታን፣ ተፈጥሮን ወይም የምትወደው ሙዚቃን የመሳሰሉ የምስጢሩ መዘወሮች የስሜቶችህን ፍሪኩንሲ በቅፅበት ሊለውጡ ይችላሉ፡፡
- የፍቅር ስሜት ለማሰራጨት የምትችለው እጅግ ከፍተኛው ፍሪኩንሲ ነው፡፡ የላቀ ፍቅር እየተሰማህና እያሰራጨህ ከሆነ ከፍ ያለ አቅም/ ኃይል እየተጠቀምክ ነው ማለት ነው፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ አጠቃቀም

ሂደት ቀላል ሂደት ነው። ልጅ … 

ፈጣሪ ነህ። የስበት ህግን በመጠቀም የመፍጠር ቀላል ሂደት አለ። እጅግ ታላላቆቹ መምህራን በአስገራሚው ሥራዎቻቸው አማካይነት ለፈጠራ ሂደቱ አስተዋፅኦ አድርገዋል። አንዳንዶቹ አለም እንዴት እንደሆነች የሚያሳይ ትረካዎችን ፈጥረዋል። በትረካዎቻቸው ውስጥ የሚገኘው ጥበብ ከትውልድ ወደ ትውልድ ወርዶ ታሪክ ሆኗል። በአሁኑ ወቅት ህያው የሆኑ ብዙ ሰዎች የነዚህ ትረካዎች ይዘት የህይወት ጭብጥ መሆኑን ይረዱታል።

## ጀምስ ሬይ

ስለ አላዲንና ፋኑሱ ስታስብ አላዲን ፋኑሱን አነሳ፣ አጠፋና ሰይጣኑን አባረረ። ሰይጣኑ ሁሌም የሚለው ነገር አለ።

«ፍላጎትህ የኔ ትዕዛዝ ነው»።

*ታሪኩ እንደሚለው ሶስት አይነት ፍላጎቶች አሉ። ነገር ግን ታሪኩን እራሱ ወደ ኋላ ሄደህ ብትመረምረው የምኞት ምንም ገደብ የለውም።*

*ስለዚህም አስብ።*

*ይህን አባባል ወስደን በህይወት ላይ እናውለው ። አስታውስ አላዲን የሚፈልገውን ሁሉም የሚጠይቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሰይጣን የተመሰለችው አለም አለች። በዘልማድ ብዙ ብዙ ተብላ ትጠራለች። ምንም ትባል ምን ለአንተ ፍላጎት የሚመችውን ትመርጣለህ። ነገር ግን ሁሉም ዘልማድ ከእኛ የበለጠ አንድ ነገር እንዳለ ነግረውናል። የአላዲን ሰይጣን ሁልጊዜ የሚለው ነገር አለ።*

«ፍላጎትህ የእኔ ትዕዛዝ ነው»።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ አስደናቂ ተረት ህይወትህና በውስጡ የሚገኙት ነገሮች ሁሉ በእራስ የተፈጠሩ መሆናቸውን ያሳያል። ሰይጣኑ ለእያንዳንዱ ትዕዛዝህ መልስ ብቻ ነው የሰጠው። ሰይጣኑ የሰበት ህግ ነው። ሁልጊዜ የምትለውንና የምታስበውን ያደምጣል። የሚገምተው የምታስበው የምትፈልገውን ነው፣ የምትናገረው የምትፈልገውን ነው፣ የምትሰራው የምትፈልገውን ነው ብሎ ነው። አንተን የአለም አለቃና ሰይጣኑም አገልጋይህ እንደሆነ ነው የሚያስበው። ሰይጣኑ ትዕዛዝህን አንገራግሮ አያውቅም። አንተ ታስበዋለህ። ሰይጣኑ ወዲያውኑ አለምን በሰዎች፣ ሁኔታዎችና ኩነቶች አማካይነት ምኞትህ ይፈፀም ዘንድ ማገዝ ይጀምራል።

## የፈጠራው ሂደት

በምስጢሩ ላይ ከጥቅም ላይ የዋለው የፈጠራው ሂደት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን የተወሰደ ሲሆን ለፈጠራህ ቀላሉ መመሪያና በሶስት ቀላል ደረጃዎች የሚከፈል ነው።

### ደረጃ 1፡- ጠይቅ

#### ሊዛ ኒኮልስ

*የመጀመሪያው ደረጃ መጠየቅ ነው። ለአለምህ ትዕዛዝ ስጣት። የምትሻውን ትወቅ። እርሷም ላሰብከው ምላሽ ትሰጥሃለች።*

#### ቦብ ፕሮክቶር

*በእርግጠኝነት የምትፈልገው ምንድን ነው? ቁጭ በልና በብጣሽ ወረቀት ፃፈው። በአሁን ጊዜ ፃፈው። «አሁን እጅግ ደስተኛና የረካሁ ነኝና..... » ብለህ ለመጀመር ትችላለህ። ቀጥለህም ህይወትህ በማንኛውም መስክ ምን ሊሆንልህ እንደምትፈልግ አብራራ።*

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትፈልገውን መምረጥ ይኖርብሃል:: ነገር ግን ፍላጎትህን ለይተህ ማወቅ ይኖርብሃል:: ይህ የአንተ ሥራ ነው:: ግልፅ ፍላጎት ከሌለህ የስበት ህግ የምትፈልገውን ነገር ሊያመጣልህ አይችልም:: የተደበላለቀ ፍሪክዌንሲ በመላክ ተመሳሳይ ውጤቶችን ታስከትላለህ:: ምናልባት በህይወትህ ለመጀመሪያ ጊዜ በእርግጥ የምትፈልገው ነገር ምን እንደሆነ ለይተህ አውጣ:: አሁን እንዲኖርህና እንድትሆን ወይም እንድታደርገው የምትፈልገውን ታውቀዋለህ:: ገደብ የለውምና ምን ትፈልጋለህ?

በፈጠራ ሂደት መጠየቅ የመጀመሪያው ደረጃ ነው:: ስለሆነም መጠየቅ ልምድህ ይሁን:: መምረጥ ኖሮብህ ነገር ግን እንዴት መመረጥ እንዳለብህ ግራ ከተጋባህ ጠይቅ:: በህይወትህ በምንም ነገር ላይ አትዘጋ:: ዝም ብለህ ጠይቅ::

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ይህ በእውነት የሚያዝናና ነው:: ይህችን አለም ልክ እንደ ማውጫ አድርጎ መያዝ ነው:: በውስጧ ምጠቅና «እንዲህ አይነት ተሞክሮ፣ ምርትና የዚህ አይነት ሰው እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ» በል:: አንተ ነህ ለአለም ፍላጎትህን እያቀረብክ ያለኸው:: ያን ያህል ቀላል ነው::*

*አሁንም አሁንም መጠየቅ አይኖርብህም:: አንዴ ጠይቅ:: አንድን ነገር ከካታሎግ ላይ አይቶ ይሁንልኝ እንደማለት ያለ ነው:: ጥያቄህን ካቀረብክ በኋላ እንደገና ጥያቄዬ አልደረሰ ይሆናል በማለት መጠራጠርና ደጋግሞ ጥያቄ ማቅረብ አይኖርብህም:: አንዴ ብቻ የምታደርገውን ጠይቅ:: በፈጠራ ሂደትም እንዲሁ ነው:: የመጀመሪያ መነሻ ፍላጎትህን ለይቶ ማወቅ ነው:: ፍላጎትህን ለይተህ ስታውቅ ጥያቄህን አቅርበሃል ማለት ነው::*

### ደረጃ 2:- እመን

## ሊዛ ኒኮልስ

*ደረጃ ሁለት ማመን ነው:: አንዴ ያንተ መሆኑን እመን:: የማይዋዥቅ ብዬ ለመጥራት የምወደው እምነት ይኑርህ::*

t.me/OLDBOOKSPDF

በማይታየው ማመንን:: ደርሶኛል በልና እመን:: የምትፈልገው ነገር እንዲሆንልህ በጠየቅከበት ጊዜ ያንተው እንደሆነ እወቅ:: የተሟላና የጠነከረ እምነት ሊኖርህ ይገባል:: ከካታሎግ አይተህ የመረጥከውን ነገር ጠይቀህ ከሆነ ተዝናና:: ምክንያቱም በጥያቄህ መሠረት ስለምታገኝ ነው:: በህይወትህም በዚሁ መልክ ቀጥል::

> «የምትፈልጋቸውን ነገሮች የአንተ እንደሆኑ አድርገህ ተመልከት:: እንደፈለካቸው እንደሚገኙ እወቅ:: እናም ተዋቸው ይምጡ:: ስለነሱ አትጨነቅ:: አታስብ:: ስላጣሃቸውም አታስብ:: የራስህ እንደሆኑ ብቻ ይሰማህ::»
>
> ሮበርት ኮሊየር (1885-1950)

ስትጠይቅና በማይታው በኩል የተሰጠህ መሆኑን ስታምንና ስታውቅ አለም ትቀየርና ወደሚታየው አለም የጠየቅከው ሁሉ ይመጣ ዘንድ ትጠመዘዛለች:: አሁኑኑ እያገኘህ እንደሆነ ምሰል፣ ተናገርና አስብ:: ለምን? አለም መስታወት ናትና አሳብህን ወደአንተው መልሳ ስለምታንፀባረቅ ነው:: ታዲያ የጠየቅከውን ሁሉ እያገኘህ ቢመስልህ ስሜት አይሰጥም? እስከአሁን ያገኘሁት ነገር የለም የሚል አስተሳሰብ ካለህ እስከአሁን አልደረሰኝም የሚለውን መሳብህን ትቀጥላለህ:: ደርሶኛ ል ብለህ ማመን ይኖርብሃል:: አግኝቼዋለሁ ብለህ ማመን ይኖርብሃል:: የዚህኑ ፍሪኩንሲ መላክ አሰብህ:: እናም የነዚህን ምስሎች መልሰህ ታገኛ ለህ:: እንዲያ ስታደርግ የስበት ህግ ሁሉንም ሁኔታዎች፣ ሰዎችና ኩነቶች በርትቶ በመሳብ እንዲደርሱህ ያደርጋል::

የእመት እረፍት ለመውሰድ፣ አዲስ መኪና ወይም ቤት ለመግዛት ስትጠይቅ ሁሉም የአንተው መሆናቸውን እወቅ:: ሌላ ጥያቄ ሌላ ቦታ ሄደህ አታቀርብም:: ሎተሪ ቢደርስህ ወይም ውርስ ብታገኝ ጥሬ ሃብቱን ገና ሳትረከብ የአንተ መሆኑን ታውቃለህ:: ይህም ያንተ መሆኑን ማመን ነው:: ደርሶኛል ብሎ የማመን ስሜት ያ ነው:: የምትፈልጋቸውን ነገሮች በስሜትህ የባለቤትነት ጥያቄ አንሳባቸውና ያንተ መሆናቸውን እመን:: እንደዚያ ስታደርግ የስበት ህግ የፈለከውን ሁኔታ፣ ሰውና ኩነት ጉትቶ ያመጣልሃል::

t.me/OLDBOOKSPDF

እራስህ ወደማመን እንዴት ትመጣለህ? እምነት መስራት ጀምር:: ልክ እንደ ህግን ሁነና እምነት ሥራ:: እምነት አሁንም ያለህ እንደሆነ ሁነህ ታይ:: ማመን ስትሰራ ደርሶኛል ብለህ ማመን ትጀምራለህ::

ጅኒው ሁልጊዜም ለጥና ዋና አስተሳሰቦችህ መልስ ይሰጣል:: በጠየቅክበት ጊዜ ብቻ አይደለም:: ለዚህም ነው ከጠየቅክ በኋላ ማመንና ማወቅ አለማቋረጥ ያለብህ:: ታመን:: የአለኝታና የታማኒነት እምነት እጅግ ታላቁ ኃይልህ ነው::

> «የፈለከው ይኖርሃል:: የውስጥህን የፈጠራ ሂደት እንዴት መጠቀም እንዳለብህ ከተማርክ የማይፈታ ህልም የለም:: ለአንዱ የሚሰራ ዘዴ ለሁሉም ይሰራል:: ወደ ስልጣን ለመምጣት ቁልፉ ያለህን መጠቀም ነው:: እናም የበለጠ የመፍጠር ሂደት በውስጥህ እንዲፈስ ለፋፊ ቧንቧዎችን ክፍት ማድረግ የግድ ይላል»
>
> ሮበርት ኮሊየር

**ዶ/ር ጆ ቫይታል**

*ነገሮች ሁሉ ይላኩልህ ዘንድ አለም እራሷን እንደገና ታዘጋጃለች::*

**ጃክ ካንፊልድ**

*አብዛኞቻችን በእውነት የምንፈልገውን ነገር እንድንመኝ ለእራሳችን አንፈቅድም:: ምክንያቱም ውጤቱን ቀድመን ለማየት ስለማንችል ነው::*

**ቦብ ፕሮክቶር**

*ትንሽ ምርምር ብታደርግ ማንም የተሳካለት እንዴት ለስኬት እንደበቃ አያውቅ እንደነበር ለማረጋገጥ ትችላለህ:: አንድ ነገር ለማድረግ እንደሚጀምር ብቻ ነው የሚያውቀው::*

**ዶ/ር ጆ ቫይታል**

t.me/OLDBOOKSPDF

*እንዴት ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አያስፈልግህም:: አለም እራሷን እንዴት አድርጋ እንደገና እንደምታዋቅር ማወቅ አያስፈልግህም::*

እንዴት ሊሆን እንደሚችል፣ አለም እንዴት ወደ አንተ እንደምትመጣ የአንተ ጭንቀት ወይም ሥራ አይደለም:: አለም ለአንተ ይህን እንድታደርግልህ ፍቀድላት:: እንዴት ሊሆን ይችላል ስትል እምነት የጐደለው ፍሪኩንሲ እየረጨህ ነው:: አሁንም የያዝከው ስለመሆኑ እምነት የለህም:: ማድረግ ያለብህ ስለመሆኑ ታስባለህ:: ይህች አለም ልታደርግልህ መቻሏን ግን አታምንም:: እንዴት ሆኖ የሚለው በፈጠራ ሂደቱ ውስጥ የአንተ ድርሻ አይደለም::

## ቦብ ፕሮክቶር

*እንዴት እንደሆነ አንተ አታውቅም:: እንዲታይህ ይደረጋል:: መንገዱ ይከሰትልሃል::*

## ሊዛ ኒኮልስ

*እንዲሆኑልን የፈለግናቸው ነገሮች ሳይሆኑ ሲቀር ያነጫንጨናል:: ተስፋም እንቆርጣለን:: እናም ተጠራጣሪዎች መሆን እንጀምራለን:: ጥርጣሬው የተስፋ መቁረጥን ስሜት ይወልዳል:: ጥርጣሬውን ውሰድና ቀይረው:: ያን ስሜት አስታውስና በማይታጠፍ ታማኒነት ተካው::*

## ደረጃ 3:- አግኝ

## ሊዛ ኒኮልስ

*ሶስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ማግኘት ነው:: ልታደንቀው ይዳዳህ:: ሲደርስ እንደሚሰማህ አይነት ስሜት ይሰማህ:: አሁኑኑ ይሰማህ::*

t.me/OLDBOOKSPDF

## ማርሲ ሺሞፍ

*እናም በሂደቱ የመልካምና የደስታ ስሜት መኖር እጅግ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ጥሩ ሲሰማህ እራስህን በምትፈልገው ነገር ፍሪኩንሲ ላይ ታስቀምጣለህና::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ይህች አለም ስሜታም አለም ናት:: ስለአንድ ነገር ግን በዚህ ስር ተመጣጣኝ ስሜት ባይኖርህ በህይወትህ የምትፈልገውን እውን ለማድረግ* በቂ አቅም ሳይኖርህ ይችላል:: ስሜት ሊኖርህ ይገባል::

አንዴ ጠይቅ፣ ያገኘህ መሆኑን እመን እናም ታገኝ ዘንድ ማድረግ ያለብህ ቢኖር ጥሩ ስሜት እንዲኖርህ ነው:: ጥሩ ሲሰማህ በማግኘት ፍሪኩንሲ ላይ ትሆናለህ:: ወደ አንተ እየመጡ ባሉ ጥሩ ነገሮች ፍሪኩንሲ ላይ ነህና እንዲሆንልህ የጠየከውን ታገኛለህ:: ስታገኘው የማያስደስትህን ነገር እንዲኖርህ አትፈልግም:: ትፈልጋለህ? ስለዚህ እራስህን በጥሩ ስሜት ፍሪኩንሲ ላይ አድርግና አግኝ::

በዛ ፍሪኩንሲ ላይ እራስህን ለማግኘት አጭሩ መንገድ « እያገኘሁ ነው:: አሁን ለህይወቴ የሚጠቅመውን መልካሙን ሁሉ እያገኘሁ ነው:: አሁን እያገኘሁ ነው» ማለት ነው:: ስሜቱም ይደርብህ:: ልክ እንደአገኘህ አይነት ይሰማህ::
ውዷ ጓደኛዬ ማርሲ ከአየኋቸው ሁሉ እጅግ ታላቅ መከሰቻ ናት:: ማንኛ ውም ነገር ስሜት ይሰጣታል:: የፈለገችን ማግኘት የሚያስከትለው ስሜት ይሰማታል:: ማንኛውም ነገር እየኖረ ይሰማታል:: በእንዴት፣ መቼ ወይም የት የተተበተበች አይደለችም:: ስሜት ያድርባታል:: እናም ይሆንላታል::

ስለዚህ ጥሩ ይሰማህ አሁን::

t.me/OLDBOOKSPDF

**ቦብ ፕሮክቶር**
*ያን ተምኔት ወደ እውነት ስትቀይረው እጅግ የላቁ ተምኔቶች በመገንባት አቅጣጫ ላይ ትሆናለህ:: ያ ነው እንግዲህ የመፍጠር ሂደት የኒ ወዳጅ::*

«በፀሎት ፣ በእምነት ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም መልስ ያገኛል»
ማቴዎስ 21/22

«የተመኘኸውን ሁሉ ከፀለይክ ካመንክ ታገኘዋለህ:: ያንተም ይሆናል»::

ማርቆስ 11/24

**ቦብ ዶይል**
*የሰበት ህግ የህጉ ጥናትና ትግበራ አሁን አለኝ የሚለውን ስሜት እንዴት ማዳበር እንደሚቻል መልክ ያስይዛል:: ያን መኪና ነድተህ ሞክረው:: ለዛ ቤት ከሱቅ እቃ ግዛለት:: ወደ ቤት ግባ:: አሁን አለኝ የሚለውን ስሜት ለማዳበር ማንኛውንም ነገር አድርግ:: ያደረካቸውንም ነገሮች አትርሳቸው:: ያን ለማግኘት ማድረግ የምትችለው ማንኛውንም ነገር ለመሳብ ይረዳሃል::*

ልክ አሁን በእጅህ እንዳለህ ሲሰማህ ስሜቱ እውነተኛ በመሆኑ በቃ ያለህ አይነት ይሆናል:: አግኝቻለሁ ብለህ እያመንክ ነው:: ታገኘዋለህም::

**ቦብ ዶይል**
*አንተው ከተኛህበት ነቅተህ ልትሆን ትችላለህ:: ተከስቷል:: ወይም አንድ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያነሳሳ ሃሳብ ኖሮህ ሊሆን ይችላል:: «መልካም በዚህ መንገድ ላደርገው እችል ነበር:: ነገር ግን መንገዱን እጠላዋለሁ» ማለት የለብህም:: እንደዚያ ከሆነ በመልካሙ ጉዳና ላይ አይደለህም:: እንቅስቃሴ አንዳንዴ ላያስፈልግ ይችላል:: ነገር ግን እንቅስቃሴው አለም ልታመጣልህ ከምትሞክረው ጋር*

t.me/OLDBOOKSPDF

*አጣጥመህ እያደረከው ከሆነ አስደሳች ይሆናል:: ሀያው*
*ይሰማሃል:: ጊዜ ይቆማል:: በብርሃን ልታደርገው ትችላለህ::*

እንቅስቃሴ ለአንዳንድ ሰዎች ሥራ የሚለውን ትርጉም የያዘ ቃል ነው
የተነሳሳ እንቅስቃሴ ግን በምንም አይነት ሥራ የሚፈጥረውን አይነ
ስሜት አያመጣም:: የተነሳሳ እንቅስቃሴና የእንቅስቃሴ ልዩነት ይ
ነው::

የተነሳሳ እንቅስቀሴ ማለት የሆነ ነገር አገኛለሁ ብለህ የምታደርገ
ነው:: ለመሞከርና አንድ ነገር እንዲሆን የምታደርገው እንቅስቃሴ
አስገራሚ ነው:: ምክንያቱም በማግኘት ፍሪኩንሲ ላይ ስለሆንክ ነው::
የኋልዮሽ ይጥልሃል:: የተነሳሳ እንቅስቀሴ ጥረት አይፈልግም:: ስሜቱም

ህይወትን በፍጥነት እንደሚፈስ ወንዝ ውሰዳት:: አንድ ነገር እንዲሆን
ስትንቀሳቀስ በወንዝ ፍጥነት ተቀራኒ እየሄድክ እንደሆን አይነት ስሜት
ይኖራል:: ስሜቱ ከባድና እንደ ትግል አይነት ነው:: ከአለም አንድ ነገር
ለማግኘት ስትንቀሳቀስ በወንዙ ፍጥነት ተቃራኒ እየሄድክ እንደሆነ
አይነት ስሜት ይኖራል:: ስሜቱ ከባድና እንደ ትግል አይነት ነው::
ከአለም አንድ ነገር ለማግኘት ስትንቀሳቀስ በወንዙ ፍጥነትና አቅጣጫ
አብረህ እንደምትጓዝ ይሰማሃል:: ድካም አልባነት ይሰማል:: የተነሳሳ
እንቅስቃሴ ስሜት ይህ ነው:: ይህ ነው በአለማችንና ህይወት አቅጣጫ
በህብር የመጓዝ ስሜት:: አንዳንድ ጊዜ የፈለከውን እስከምታገኝ ድረስ
እንቅስቃሴ እንዳደረክ ልትገነዘበው ትችላለህ:: ምክንያቱም እንቅስቃሴ
ማድረጉ ጥሩ ስሜት ነበረውና ነው:: ወደ ኋላ መለስ ብለህ ትመለከትና
አለም እንዴት አድርጋ ወደምትፈልገው ያመጣችህበትን ታምርና
ዝንቅንቅ ታያለህ:: የምትፈልገውን ያመጣችልህ መሆኑንም እንዲሁ::

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*አለም ፍጥነት ትፈልጋለች:: አትዘግይ:: ግምትን አትደግፍ::*
*አትጠራጠር:: አጋጣሚው ሲገኝ፣ ሲነዝርህና የመገፋፋት ስሜት*
*ከውስጥህ ሲመጣ ተንቀሳቀስ:: ያንተ ሥራ ያ ነው:: ማድረግ*
*ያለብህ ያን ነው::*

ደመነብስህን እመን:: ደመነብስ አለም እያነሳሳችህ ማለት ነው:: አለም
በማግኘት ፍሪኩንሲ ላይ ሆና እያነጋገረችህ ነው:: ደመነብሳዊ ስሜት

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለህ ተከተሰው:: አለም የጠየከውን ለማግኘት ማግኔታዊ ማንቀሳቀስ እያደረገችብህ መሆኑን ትረዳለህ::

## ቦብ ፕሮክቶር

*የምትፈልገውን ሁሉ ታመጣዋለህ:: ገንዘብ ከሆነ የምትፈልገው ታመጣዋለህ:: ሰውም ከሆነ እንዲሁ:: የሆነ መጽሐፍንም እንዲሁ ታመጣዋለህ:: ቀልብህ ያረፈበትን ነገር ጠንቅቀህ መገንዘብ ይኖርብሃል:: ምክንያቱም የምትፈልጋቸውን ነገሮች ምስሎች በአግባቡ በምናብህ ስትስላቸው እነሱም ወደ አንተ ይሳባሉ:: አንተም በተመሳሳይ ወደነሱ ትሳባለህ ነው:: በአንተ አማካይነት ወደ ተጨባጭ እውነትነት ይለወጣሉ:: እንደዚያ የሚሆነውም ‵በህግ ነው::*

እራስህን እንደ ማግኔት አድርገህና ሁሉንም ነገር እየሳብክ አስታውስ:: ስለምትፈልገው ነገር በአይምሮህ ግልፅ ከሆንክ የምትፈልገውን ያን ነገር ወደራስህ ለመሳብ የምትችል ማግኔት ሆነሃል:: ተፈላጊው ነገርም በበኩሉ የማግኔት ኃይል ያገኛል:: የስበት ህግ እያሉ ነገሮች እያመጣልህ በሄደ ቁጥር አንተም የበለጠ ማግኔታዊ ትሆናለህ:: ምክንያቱም ተጨማሪ የተማሪነት፣ የእምነትና የእውቀት ኃይል ስለሚኖርህ ነው::

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ያለምንም ነገር ልትጀምር ትችላለህ:: ያለምንም ነገርና መንገድ ይሰራል::*

የሚያስፈልግህ ነገር ቢኖር አንተና እንዲሆኑ የሚታሰቡ ነገሮችን የማሰብ አቅምህ ብቻ ናችሁ:: በሰው ልጅ ታሪክ የተፈለሰፈና የተሰራ ማንኛውም ነገር የተፀነሰው በአንድ ሃሳብ ነው:: ከዚያ አንድ አሳብ ተነስቶ መንገዱ ደራ:: ያም መንገድ ከማይታይነት ወደክስተትነት ተለወጠ::

t.me/OLDBOOKSPDF

## ጃክ ካንፊልድ

በጨለማ የሚነዳ አንድ መኪናን አስብ:: የፊት መብራቶቹ ከአንድ እስከ ሁለት መቶ ጫማ ብቻ የሚያሳዩ ናቸው:: ከካሊፎርኒያ እስከ ኒው ዮርክ በጨለማ እየነዳህ ይህን መብራት መጠቀም ትችላለህ:: ምክንያቱም ብርሃኑ የሚያስፈልግህ ለተከታታይ ሁለት መቶ ጫማዎች እርቀት ብቻ ነውና:: የሀይወት ጉዳናም እንዲሁ ነው:: በየሁለት መቶ ጫማው ሌላ ሁለት መቶ ጫማ የሚከተል ከሆነ ህይወትም እንዲሁ በተከታታይ እየተለወጠ የሚሄድ ይሆናል:: እንዲያ እያለም በእውነት ወደምትፈልገው ያደርስሃል:: ምክንያቱም እዛ መድረስ ትፈልጋለህና ነው::

ይህችን አለም እመናት:: ተማመን፣ እመንና ታማኒነት ይኑርህ:: ምስጢሩ የሚለውን ፊልም የማሳየት ምንም አሳብ አልነበረኝም:: የራዕዬን ውጤት ብቻ አጥብቄ ይዤ ነበር:: ውጤቱም በልቤ ቁልጭ ብሎ ታይቶኝ ነበር:: በሙሉ አቅሜ ተሰምቶኝ ነበር:: እናም የሚስጥሩን ፊልም ለመድረስ የሚያስፈልገው ማንኛውም ነገር መጣልን::

> «የመጀመሪያው መነሻህ ታማኒነት ይሁን:: የደረጃውን መጨረሻ አጠቃለህ ማየት አያስፈልግህም:: ዝምብለህ ወደ መጀመሪያው ደረጃ ውጣ»::
>
> ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁ አር (1929 - 1968)

## ምስጢሩና አካልህ

የፊጠራ ሂደትን ክብደታቸውን ለመቀነስ ከሚፈልጉ ወፍራሞች አንፃር እንየው:: መታወቅ ያለበት የመጀመሪያው ነገር ለመቀነስ ስትፈልግ የበለጠ መቀነስን መልሰህ ትስባለህ:: በምግብ መቀነስ የማይቻለው ለዚህ ነው:: ምክንያቱም አትኩሮትህ ክብደት መቀነስ ነውና:: ያለማቋረጥ መልሰህ የምትስበው ክብደት መቀነስ ያለብህ መሆኑን ነው::

ቀጥሎ መታወቅ ያለበት የውፍረት ሁኔታው የተፈጠረው በአስተሳሰብህ አማካይነት መሆኑ ነው:: በተለመደ አነጋገር አንድ ሰው ከሚገባው በላይ ከወፈረ ውፍረቱ የመጣው ከወፍራም አስተሳሰቦች ማሰብ ነው:: ይህን ያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ሲያውቀውም ሳያውቀውም ይችላል። አንድ ሰው ቀጭን እስተሳሰብ ይዞ ወፍራም አይሆንም። የሰበትን ህግ ጨርሶ ነው የሚያስተባብለው። እንዲያ ከሆነ ሰዎች የቱንም ያህል ዝግመታዊ፣ ታይሮይድ፣ ሜታቦሊዝም ወይም ውፍረታቸው የዘር ነው ቢባሉም ሁሉም የውፍረት አሳቤዎች ሽፋኖች ናቸው። እንደነዚህ አይነት አባባሎችን የምትቀበለው በልምድ ምክንያትና ስለአመንክ ነው። የዚህ አይነት ተሞክሮም ወፍራም መሆንን መሳብ እንድትቀጥል ያደርግሃል።

ሁለት ሴቶች ልጆች ከወለድኩ በኋላ ወፈርኩ። ውፍረቱ የመጣው ከወለዱ በኋላ ክብደት አይቀንስም አብሶም ሁለተኛ ከወለዱ በኋላ የሚታሰብ አይደለም እየተባለ እየሰማሁ ከመኖሬ መሆኑን አውቃለሁ። ከእንዲህ አይነት የውፍረት አመለካከት ጋር እራሴን አመሳሰልኩና ውፍረት ስራዬ ሆነ። በእርግጥ ደለብኩ። መድለቤን የበለጠ እየተገነዘብኩ በሄድኩ ቁጥር የበለጠ መድለብን አመጣሁ። በሌለ ቁመናዩ 143 ፓውንድ መዘንኩ። ይህ ሁሉ የሆነው ውፍረትን ስለማስብ ነበር።

አብዛኛው ሰው እኔም ጭምር የምናምነው ምግብ ክብደትን ይጨምራል የሚለውን ነው። የሚጠቅም እምነት አይደለም። አሁን ሳስበው ዝም ብሎ ቧልት ነው። ምግብ ክብደትን አያመጣም። ምግብ ያወፍራል የሚለው ያንተ አመለካከት ነው። ምግብ ክብደትን እንዲጨምር የሚያደርገው አመለካከት የነገሮች ሁሉ ቅድመ መነሻ መሆኑን አስታውስ። የተስተካከለ አመለካከት ይኑርህ። ውጤቱም የተስተካከለ ክብደት ይሆናል።

የተስተካከለ ክብደት የሚባለው ለአንተ ጥሩ የሚሰማህ ክብደት ነው። የማንም ሰው የተለየ አባባል የተለየ ትርጉም አያመጣም። የሚመችህ ክብደት ትክክለኛው ክብደት ነው። በቃ።

ቀጭን ሆኖ እንደፈረስ የሚበላ ሰው ልታውቅ ትችላለህ። እንደዚህ አይነት ሰዎች «ያገኘሁትን ሁሉ እበላለሁ ነገር ግን ሁልጊዜም የተስተካከለ ክብደት አለኝ» በማለት ሲፎክሩ ይችላሉ። የአለማችን ጅኒም « እንዳላችሁት ይሁንላችሁ»። ይላቸዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

የተስተካከለ ክብደት እንዲኖርህ እነዚህን ደረጃዎች ተከተል::

## ደረጃ 1:- ጠይቅ

የምትፈልገውን ክብደት ለይተህ እወቅ:: ያን የተስተካከለ ክብደት ስትይዝ ምን አይነት ቁመና ይኖረኛል ብለህ የምታስበውን በምናብህ አስቀምጠው:: መልካም ክብደት ቀደም ብሎ ኖሮህ ከሆነና በዚህ ወቅት የተነሳኸው ፎቶ ካለ ሁልጊዜ ይህን ፎቶ ተመልከተው:: ፎቶው ከሌለህ መልካም ክብደትን የሚወክል ሥዕል ፈልግና እንዲሁ ሁሌ ተመልከተው::

## ደረጃ 2:- እመን

የተስተካከለ ክብደት ይኖረኛልና አሁንም አለኝ በልና እመን:: ትክክለኛ ክብደት ያንተ ስለመሆኑ አስመስል:: እምነት ፍጠር:: የተስተካከለ ክብደት እየመጣልህ መሆኑን ማየት መቻል አለብህ:: የተስተካከለ ክብደትህን ጻፍና በመመዘኛ መሳሪያህ ላይ አስቀምጠው:: አልያም አትመዘን:: እንዲሆንልህ የጠየቅከው ነገር ከአመለካከትህ፣ ከምትናገረውና ከተግባርህ ጋር መጋጨት የለበትም:: በአሁኑ ክብደትህ ወቅት ልብስ አትግዛ:: ወደፊት እገዛለሁ በምትላቸው ልብሶች ላይ እምነት ጣል:: አትኩሮትም ስጣቸው:: በካታሎግ እንደመረጥክ ሁሉ ትክክለኛውን ክብደት ምረጥ:: ጥያቄህን አቅርብ እናም ይሰጥሃል::

መልካም ክብደት ያላቸውን ሰዎች የማየት፣ የማድነቅና በውስጥህ የማሞገስ ፍላጎት ይኑር:: ፈልጋቸው:: ስታደንቃቸውና የዚህም ስሜት ሲሰማህ ለራስህ እንዲሆን ታደርገዋለህ:: ወፍራሞች ሲያጋጥሙህ አትያቸው:: ትክክለኛ ክብደት ነው ብለህ መደምደም ነው:: ዞር በልና የሰው ስሜት ይሰማህ::

## ደረጃ 3:- ተቀበል

ጥሩ ሊሰማህ ይገባል:: ስለራስህም ጥሩ ሊሰማህ ይገባል:: ይህ ወሳኙነው:: ምክንያቱም አሁን ስለአለው አካልህ ደስታ ሳይሰማ የተስተካከለ ክብደት ሊኖርህ አይችልም:: ስለራስህ መጥፎ ከተሰማህ እጅግ ኃይለኛ ስሜት ነው:: የዚህ አይነት ስሜትም አይቆምም::

t.me/OLDBOOKSPDF

አካልህን ጠልተህና እየተቸህ ለውጥ ማምጣት አትችልም። እንዲያውም የከፋ ሁኔታን ትፈጥራለህ እንጂ። እያንዳንዷን የአካልህን ነቁጥ አምላሽት። እንቅስቃሴዋት። መልካሙን ስታስብ፣ ስለራስህ ጥሩ ስሜት ሲያድርብህ በተስተካከለ የሰውነት ክብደትህ ፍሪኩንሲ ላይ ትሆናለህ። ፍፁምነትንም ትጠራለህ።

ሞላስ ዋትልስ የተባለው ፀሐፊ ስለ አመጋገብ ያለው አስደናቂ ነገር አለ። «ስትመገብ በእስተኛኘክህ ላይ አትኩሮት ያደረክ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሁንና የማኘክህን፣ የመዋጥህና ምግቡ በአፍህ ውስጥ እያለ የፈጠረብህን ስሜቶች ውደዳቸው። በሚቀጥለው ስትመገብም ይህኑ ድገመው። ስትበላ ከራስህ ጋር ከሆንክ የምግቡ ጣዕም ይታወቅሃል። እየበላህ አይምሮህ ከተሰለበ ምግቡ ጨርሶ ጣዕም ያጣል። ስንመገብ ከራሳችን ጋርና ከሚያስደስተው የመብላት ተሞክሮ ላይ ከሆነ፣ ምግቡ ወደ አካላችን ያለምንም ችግር የሚሰርፅ ስለመሆኑ አምኛለሁ»።

## ስንት ጊዜ ይወሥዳል?

### ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ሰዎች የሚጨነቁበት ሌላው ነገር እንዲሆን የተፈለገው ነገር ሁሉ በስንት ጊዜ ውስጥ ይሆናል የሚለው ነው። ይህን ያህል ጊዜ ይወስዳል የሚል ህገ-መፀሐፍ የለም። የራስህ ከሁኔታው ጋር የመዛመድ ጉዳይ ነው።*

ጊዜ መደናበር ነው። አንስታይን እንዲህ ብሎ ነው የነገረን። ይህን ስትሰማ መጀመሪያ ጊዜህ ከሆነ ጭንቅላትህን የሚያዞር ዕንሠ - ሃሳብ ይሆንብሃል። ምክንያቱም ነገሮች በጊዜ ውስጥ ተከታትለው ሲሆኑ ታያለህና ነው። የኳንተም ፊዚክስና አንስታይን ሁሉም ነገር በአንድ ወቅት የሚሆን ነው ይላሉ። ይህ የሚሆነውም ጊዜ የሚባል ነገር የለም ብለህ መረዳት ከቻልክና ዕንሠ - ሃሳቡን ከተቀበልክ ነው። እንዲህ ሲሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ ወደፊት የምትፈልገውን ነገር ሁሉ አግኝተኸዋል ማለት ነው:: ሁሉም ነገር የሚሆነው ባንድ ጊዜ ከሆነ ፍላጎትህም ሆኖ ተጠናቋል::

አሰም አንተ የምትፈልገውን ለማሳካት ምንም ጊዜ አይፈጅባትም:: የዘገየ የሚመስልህ ነገር ሁሉ ዘግይቶ አይደለም:: የራስህ ነገር የሆነ መሆኑን ለማመን፣ ለማወቅና ስሜት ለማሳደር በመዘግየትህ ነው የዘገየ የሚመስልህ:: በፍላጎትህ ፍሪኩንሲ ላይ ስመሆን በመዘግየትህ ነው:: ልክ በፍሪኩንሲው ላይ ስትሆን የምትፈልገው ነገር ይከሰታል::

**ቦብ ዶይል**

*ለአለም መጠን ምኗም አይደለም:: በሳይንስ ደረጃም ግዙፍና እጅግ የማይታይ ደቃቅ ያልናቸውን ነገሮች ለማሳብ ማስቸገር ካቆመ ቆይቷል::*

*አሰም ማንኛውንም ነገር ያለ ድካም ታደርገዋለች:: ሣር ለማደግ አይጨነቅም:: ያለድካም ያድጋል:: ሁሉም ነገር የአይምሮ ባጣ ነው:: «ይህ ትልቅ ነገር ነው፣ ያ ጊዜ ይወስዳል፣ ወዘተ» የምንለው እኛው ነን:: እናም «ይህ ትንሽ ነው፣ አንድ ሰአት እንዲፈጅ አደርገዋለሁ» የምንለው የራሳችንን ደንቦች ነው:: እንደ አለማችን ከሆነ ደንቦች የሉም:: የእንዳለ ስሜት አይነት ስሜት ስለምታሳይ ነው እንዲህ አይነት ደንቦች የሚኖሩ የመሰለህ::*

አሰም ጊዜም መጠንም የላትም:: አንድን ብር ማሳየት አንድ ሚሊዮን ብርን ከማሳየት የሚለይበት የለም:: ሂደቱ አንድ ነው:: አንዱ አጭር ጊዜ የወሰደ ሌላኛው ደግሞ የተራዘመ የሚሆነው ሚሊዮን ብር ብዙ ስለሆነና አንድ ብር ደግሞ ያን የህል ስላልሆነ ብለህ ስላሰብክ ነው::

**ቦብ ዶይል**

*ለአለም መጠን ምኗም አይደለም:: በሳይንስ ደረጃም ግዙፍና እጅግ የማይታይ ደቃቅ ያልናቸውን ነገሮች ለማንፀባር ማስቸገር ካቆመ ቆይቷል::*

t.me/OLDBOOKSPDF

አለም ማንኛውንም ነገር ያለ ድካም ታደርገዋለች። ማር ለማድግ አይጨነቅም። ያለድካም ያድጋል። ሁሉም ነገር የአይምሮ ጣጣ ነው። «ይህ ትልቅ ነገር ነው፣ ያ ጊዜ ይወስዳል፣ ወዘተ» የምንለው እኛው ነን። እናም «ይህ ትንሽ ነው፣ አንድ ሰአት እንዲፈጅ አደርገዋለሁ» የምንለው የራሳችንን ደንቦች ነው። እንደ አለማችን ከሆነ ደንቦች የሉም። የእንዳለ ስሜት አይነት ስሜት ስለምታሳይ ነው እንዲህ አይነት ደንቦች የሚኖሩ የመሰለህ።

## ቦብ ፕሮክቶር

*ለረጅም ጊዜ ለማግኘት ከማታውቀው ጓደኛህ ጋር እያወራህ አስብ። በሆነ ምክንያት ሌላ ሰው ስለዚህ ጓደኛህ እያወራልህ ነው። ከጓደኛህም የስልክ ጥሪ ወይም ደብዳቤ ይደርስሃል።*

የስበት ህግን ለመሞከር በትንሽ ነገር መጀመሩ ቀላሉ መንገድ ነው። ልክ እንደዚህ ያደረገ የአንድ ወጣት ሰውዬን ታሪክ ላካፍልህ። ምስጢሩ የሚለውን ፊልም አየና በትንሽ ነገር ለመጀመር ወሰነ።

በአይምሮው የላባ ስዕል ሳለ። ይህ ላባ አምሳያ የሌለው ነው ብሎ አረጋገጠ። በላባው ላይ የተለዩ ምልክቶች አደረገ። እናም ይህን ላባ ባየ ቁጥር የባሰ የስበት ህግን ተንተርሶ የፈጠረው ላባ መሆኑን ያለምንም ጥርጥር ያውቀዋል።

ከሁለት ቀናት በኋላ በኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ርዝመት ባለው ፎቅ ለመውጣት ተቃርቦ ነበር። ለምን እንደሆነ ባያውቅም ብቻ ከፎቁ ሆኖ ወደታች ተመለከተ። በዛ ፎቅ መግቢያ ከእግሩ ሥር ቀደም ብሎ በምናቡ የሳላትን ላባ አየ። በጭንቅላቱ ካለችው ላባ ጋር አንድ አይነት ነው። በምናባዊው ላባ ላይ ያስቀመጣቸው ልዩ ምልክቶችም አሉ። በዛን ጊዜ ያለቅንጣት መጠራጠር የስበት ህግ ከነሙሉ ክብሩ መስራቱን አወቀ። በአይምሮው ኃይል አማካይነት አንድን ነገር ወደራሱ የመሳብ አቅም ያለው መሆኑን ተገነዘበ። ምልዑነት ባልጉደለው እምነት አሁን እጅግ ላቅ ያሉ ነገሮችን ወደ መፍጠሩ ተሸጋግሯል።

t.me/OLDBOOKSPDF

**ዳቪድ ሺርመር**
(የኢንቨስትመንት አሰልጣኝ፣ የሃብት ስፔሺያሊስት)
የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን እንዴት እድርጌ እንዳስመርኳቸው ብዙዎቹን አስደንቋል። ልክ ምስጢሩ የሚለውን ፊልም እንዳየሁ ነው እንዲህ ማድረግ የጀመርኩት። የመኪና ማቆሚያ ቦታ ልክ በምፈልገው አካባቢ እንደማገኝ ታይቶኛል። 95 በመቶ እንደቱመኝ ሁት ይሆንልኛል። 5 በመቶ ትንሽ መታገስ ይኖርብኛል። ወዲያውም መኪና አቁሞ የነበረ ሰው ይለቅልኝና እኔ እገባለሁ። ሁልጊዜ እንደዚያ ነው የሚሆነው።

«ለመኪናዬ ማቆሚያ ሁልጊዜ አገኛለሁ» የሚል ሰው በእርግጥም እንደሚያገኝ አሁን ለመረዳት ትችል ይሆናል። እድለኞችና ሁልጊዜ እጣ ይወጣልናል የሚሉ ሰዎች ሁልጊዜ እጣ እንደሚወጣላቸው ምክንያቱ አሁን ሊገባህ ይችል ይሆናል። እነዚህ ሰዎች ይጠብቁታል። ትልቅ ነገርን በመመኘት ጀምር እንዲያ ስታደርግ ህይወትህን ቀድመህ ትፈጥራለህ።

## ቀንህን አስቀድመህ ፍጠር

የስበት ህግን ተጠቅመህ ሙሉ ህይወትህን አስቀድመህ መፍጠር ትችላለህ። ዛሬ ከጀመርከው እስከሚቀጥለው ነገ ድረስ። ቀንህን አስቀድሞ መገንዘብ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ፕሬንቲስ ሙልፎርድ የሚባል መምህር ብዙ ቁምነገሮችን ባካተተበት ፅሁፍ አሳይቶታል።

> «አስደሳች ጉብኝት ወይም ጉዞ ይኖረኛል ብለህ ለእራስህ ስትነግር ጉብኝትህን ወይም ጉዞህን አስደሳች የሚያደርግ መልዕክት ከአካልህ ቀድመህ ስለምትልክ ጉብኝትህና ጉዞህ በዚሁ መልክ ይስተካከሉልሃል። ከጉብኝትህ ወይም ጉዞህ በፊት መጥፎ ወሬ፣ ወይም ፍርሃት ወይም የሆነ የሚደብር ነገር ካደረብህ ጉዞህንና ጉብኝትህን አስቸጋሪ የሚያደርጉ የማይታዩ አስፈፃሚዎችን ቀድመህ መላክህ ነው። አመለካከታችን ወይም በሌላ ቋንቋ የአይምሮአችን ሁኔታ ነገሮችን መጥፎና ጥሩ ብሎ አስቀድሞ የመመደብ ሥራ ይሰራል»።
>
> ፕሬንቲስ ሙልፎርድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፕሬንቲስ ሙልፎርድ ይህን የፃፈው በ18ዎቹ ነው:: መልካም ጅማሪ ነው:: የእያንዳንዱን ቀን እያንዳንዱን ኩነት ቀድሞ መገንዘብ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ በግልፅ ማየት ትችላለህ:: እንዲህ ባታደርግ የሚሆነውን ያለ ጥርጥር ታየዋለህ:: የዚህ ወቅት ውጤት ጥድፊያና መሯሯጥ ነው::

ከተጣደፍክና ከተሯሯጥክ እነዚህ ነገሮች ከፍርሃት የመጡ መሆናቸውን ታውቃለህ:: እናም መጥፎ ነገሮችን ቀድመህ እያዘጋጀህ ነው:: በተጣደፍክ ቁጥር አንዱን አስቸጋሪ ነገር በሌላ እየተካህ ትሄዳለህ:: የስበት ህግም ተጨማሪ ጥድፊያና መሯሯጥን የሚያመጡ ነገሮችን በተጨማሪ ያዘጋጅልሃል:: ማቆምና ከዚያ ፍሪኩንሲ መውጣት ይኖርብሃል:: ትንሽ ጊዜ ውሰድና ራስህን ቀይር መጥፎ ነገርን መጋበዝ ስለሌለብህ::

ብዙ ምዕራባውያን ጊዜን ሲያሳድዱ ይውሉና «ጊዜ አጠረን» ይላሉ:: አንድ ሰው እንዳለው «በቂ ጊዜ ከሌላቸው ምክንያቱ የስበት ህግ ነው»:: ጊዜ የለኝም እያልክ ስታንሰላስል ኖረህ ከሆነ ከአሁኑ ጀምረህ «ከበቂ በላይ ጊዜ አለኝ» ብለህ አበክረህ አውጅና ህይወትህን ለውጥ::

የወደፊት ህይወትህን ለመፍጠር አብይ ጊዜን ወደመጠበቅ ልትዞር ትችላለህ:: በሚቀጥለው ጊዜ ያን ጊዜ የምትፈልገውን ለማግኘት የምትጠባበቅበት ሁኔታ ላይ ትደርሳለህ:: ይህን በማንኛውም ጊዜና`ቦታ ልታደርገው ትችላለህ:: ማንኛውንም ህይወት ነክ ሁኔታ ወደቀናነት ለውጠው::

ማንኛውንም ነገር አስቀድሞ የመወሰን ልምድ ይኑርህ:: ይህም የሚሆነው በአመለካከትህ ደረጃ ነው:: የተፈጥሮ ሃይሎችን አስቀድመህ በምታደርገውና በምትሄድበት ሁሉ የወደድከው ነገር እንዲሆን አንድታውጠነጥን እንዲያደርጉልህ አዘጋጃቸው :: እናም ህይወትህን ሆን ብለህ ትፈጥረዋለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ልክ እንደ አላዲኑ ጂኒ የስበት ህግ ማንኛውንም መመሪያ ይሰጠናል።
- የመፍጠር ሂደት የምትፈልገውን ለመፍጠር በሶስት ደረጃዎች ይረዳሃል። ማለትም ጠይቅ፣ እመንና ተቀበል በተባሉ ደረጃዎች ይረዳሃል።
- አለም የምትፈልገውን እንድታደርግልህ መጠየቅ የምትፈልገውን ለይቶ ለማወቅ እድል ይሰጥሃል። በአይምሮህ ቁልጭ አድርገህ ፍላጎትህን ካወክ ጥያቄህን አቅርበሃል ማለት ነው።
- ማመን የጠየከውን እንዳገኘህ አይነት መሆንን፣ ማውራትንና ማሰብን ይጨምራል። የፈለከትን አግኝቻለሁ የሚል ፍሪኩንሲ ስትልክ የስበት ህግ የፈለካቸውን ሰዎች፣ ኩነቶችና ሁኔታዎች ወደ አንተ ያንቀሳቅስልሃል።
- ማግኘት የፈለከውን ነገር ስታገኝ የሚሰማህን ስሜት አይነት ይይዛል። የአሁን ጥሩ መሰማት በምትፈልገው ነገር ፍሪኩንሲ ላይ እንድትሆን ያደርግሃል።
- ክብደት ለመቀነስ ክብደት በመቀነስ ላይ አታተኩር። ይልቅየው በተስተካከለው ክብደትህ ላይ አተኩር። የተስተካከለ ክብደት ስሜት ይደርብህ። ይሆንልሃልና።
- አንድ ስኒ ቡናን ወይም የመኪና ማቆሚያ ቦታን የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮችን ተንተርሰህ መጀመር የስበት ህግን በተግባር ለማየት የሚረዳ ቀላል መንገድ ነው። የሆነች ትንሽ ነገርን ለመሳብ ሞጥረህ ተመኝ። አቅሙን ስታዳብር ከፍ ያሉ ነገሮችን ለመሳብ ትችላለህ።
- እያንዳንዱ ቀን እንዴት እንዲያልፍልህ በምትፈልገው ሁኔታ አስቀድመህ በአመለካከትህ ፍጠረውና ህይወትህን ሆን ብለህ ትሰራዋለህ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ሃይለኛ ሂደት

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ብዙ ሰዎች በወቅቱ ሁኔታ ተተብትበው እየኖሩ አይነት ይሰማቸዋል:: ማንኛውም አይነት ወቅታዊ ሁኔታ ያለ እውነታ ነው:: ያለ እውነታ ደግሞ ምስጢሩ የሚለውን በአገልግሎት ላይ ማዋል ስትጀምር መለወጥ ይጀምራል::* .

ያለው እውነታህ ወይም የአሁኑ አኗኗርህ ስታውጠነጥናቸው የነበሩ አመለካከቶችህ ውጤት ነው:: አመለካከቶችህንና ስሜቶችህን መለወጥ ስትጀምር ሁሉም ተጠቃሎ ይለወጣል::

> «ሰው ራሱን መለወጥ ይችላል... እናም የእሱ ባለቤት ይሆናል የሚለው ለትክክለኛው አመለካከት በብቃት የነቃ የማንኛውም አይምሮ ማጠቃለያ ነው»::
>
> ክርስቲያን ዲ. ላሶር (1866 - 1954)

## ሊዛ ኒኮልስ

*ሁኔታዎችን ለመለወጥ ስትፈልግ መጀመሪያ የራስህን አስተሳሰብ ለውጥ:: እዳ ይመጣብኛል ብለህ ስትጠብቅ አይቀርም:: ይሆናል የምትለው ሌላ ትልቅ ነገርም አይኖርም:: የእዳ ደረሰኝ ብቻ ነው:: እናም በየቀኑ እዳን እየፈራህ ትውላለህ:: የምታስበው እዳን ነው:: የምትጠብቀውም እዳን ነው:: እዳ ይጠብቀኝ ይሆን እያልክ በተደጋጋሚ ጠይቅ:: «አዎ» ነው መልሱ:: ምክንያቱም ከመልዕክት ሳጥንህ ውስጥ ሁልጊዜ ይጠብቀኛል የምትለው ነገር እዳ ስለሆነና የስበት ህግም ለአመለካከትህ ታዛዥነቱን አይነፍግምና ነው:: እስኪ ለራስህ አስብና በዕዳ ፋንታ የገንዘብ ቼክ አገኛለሁ ብለህ አስብ::*

እንዲሆንልህ የምትፈልገው ነገር ከባድ የመሳብ ሃይል አለው:: ነገሮችን ወደአንተ ስበ ስለሚያመጣ ነው:: ቦብ ፕሮክቶር እንዳለት «ፍላጎት ከምትፈልገው ነገር ጋር ሲያገናኝህ እንዲኖረኝ የሚለው ፍላጎትህ ደግሞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩን ወደ አንተ ያመጣዋል»:: የምትፈልጋቸውን ነገሮች ይሆናሉ ብለህ ጠብቅ:: የማትፈልገውን ነገር ደግሞ አትጠብቅ:: ምን እንዲሆን ነው አሁን የምትጠብቀው?

## ጀምስ ሬይ

*ብዙ ሰዎች አሁን ያሉበትን ሁኔታ ብቻ ይገነዘቡና «እኔ እንዲህ ነኝ» ይላሉ:: እነርሱ ግን እንደዚያ ነበሩ እንጂ አሁን አይደሉም:: ለምሳሌ በባንክ ውስጥ በቂ ገንዘብ የለኝም፣ የምትሻው አይነት ግንኙነት ከማንም ጋር የለኝም፣ ወይም ጤናዬ የተሟላ አይደለም ልትል ትችላለህ:: ነገር ግን ያ አይደለም እንደዚያ የሚያስብልህ:: ያለፉት ጊዜዎች አመለካከትህና የሥራህ ቅሪቶች ናቸው:: ለዚህም ነው ህይወታችን በአለፉት ወቅቶች ቅሪተ-አመለካከትና ተግባር ላይ የተመሰረተ ነው የምንለው:: እናም የአሁኑ ማንነትህ በቅሪተ-አመለካከትህ አኳያ የምታየው ከሆነ ለወደፊቱም ምንም የተለየ ነገር እንደማይኖርህ አድርገህ እራስህን እያጨለምክ ነው::*

«የአሁኑ ማንነታችን ያለፈ አመለካከታችን ውጤት ነው»
ቡድሃ (536 ቢ.ሲ.ኢ - 483 ቢ.ሲ.ኢ)

ከታላቁ መምህር ኔቪል ጉዳርድ ያገኘሁትን ሂደት ላካፍልህ:: ይህ ሂደት በህይወቴ ላይ ሰፊ ውጤት አስከትሏል:: ኔቪል ከመተኛትህ በፊት በየቀኑ ያደረግካቸውን ነገሮች ሁሉ እንድታብሰለስላቸው ይመክራል:: አንድ ኩነት ወይም ወቅት በፈለከው መንገድ አልሄድ ካለህ እነደገና በአይምሮህ አውጠንጥነው:: እነዚያን ኩነቶች በአይምሮህ ውስጥ ደጋግመህ ደጋግመህ ስታውጠነጥናቸው ፍሪኩንሲህን ከቀኑ ታላቅቀውና ለነገ የሚሆን አዲስ ፍሪኩንሲና ምልክት ትረጫለህ:: ለወደፊትህ የሚሆኑ አዳዲስ ስዕሎች ሆን ብለህ ፈጥረሃል ማለት ነው:: አላስፈላጊ የሆኑትን ስዕሎች ለመለወጥ አሁንም ጊዜ አለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የውለታ/ምስጋና ሃያል ሂደት

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

ህይወትህን ለመለወጥ በአሁኑ ሰአት ምን ማድረግ ትችላለህ? የመጀመሪያው ነገር ምስጋና የሚያስከትሉ ነገሮችን ዝርዝር ማዘጋጀት ነው:: ይህ አቅምህን ለውጡ አመለካከትህንም ያስተካክለዋል:: ይህን ከማድረግህ በፊት ምናልባት በሌለህ ነገር ላይ አትኩረህ ይሆናል:: አሁን ግን ከዚህ በተቃራኒው ትጓዛለህ:: ደስታን ለፈጠሩልህ ነገሮች ሁሉ አመስጋኝ መሆን ትጀምራለህ::

«ምስጋና/ውለታ ጠቅላላ አይምሮህን ወደ የአለም ፈጣሪ አቅም የመጣዋል የሚለው ለአንተ እንግዳ አመለካከት ነው:: ከግምት አስገባውና እውነት መሆኑን ታያለህ»::

ዋላስ ዋልተር (1860- 1911)

## ማርሲ ሺሞፍ

ምስጋና በህይወትህ የበለጠ የሚያስገኝህ ፍፁማዊነት ያለው መንገድ ነው::

## ዶ/ር ጆን ግሬይ

(ሳይኮሎጂስት፣ ደራሲና አለም አቀፍ ተናጋሪ)
እያንዳንዱ ወንድ ሚስቱ ትንሽ ነገር እንኳን ብማድረጉ ስታመሰግነው ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል:: የበለጠና ጥሩ ነገር የማድረግ ፍላጎት ያድርበታል:: ማመስገን ነገሮችንና ድጋፍን የመሳብ አቅም አለው::

## ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ

የምናምንበትንና ምስጋናችንን የቸርነውን ማንኛውንም ነገር እናገኝ ዋለን::

t.me/OLDBOOKSPDF

## ጀምስ ሬይ

*ለእኔ ምስጋና እጅግ ሃያል ነገር ነው:: ጧት ጧት ስነሳ «አመሰግናለሁ» እላለሁ:: ጧት ጧት ገና መሬቱን ስረግጥ «አመሰግናለሁ» እላለሁ:: ጥርሴን ሳጥብና ጧት ማድረግ ያለብኝን ስሰራ ላመስገኔ ምክንያት የሆኑኝን ነገሮች አወጣ አወርዳቸዋለሁ:: እነዚህን እያውጠነጠንኩ ምንም አይነት ተራ የቀንተቀን ሥራ አልሰራም:: ጠብ እርግፍ አድርጌ ያን አይነት ሥራ እተውና ማመስገን እጀምራለሁ::*

ጀምስ ሬይ ስለምስጋና ያለውን ተሞክሮ እያካፈለን ፊልም የተነሳበትን ቀን ጨርሶ አልረሳውም:: ከዛን ጊዜ ጀምሮ የጀምስን ሂደት ህይወቱ አደረኩት:: ጧት ከመኝታዬ ስነሳ ሳላመሰግን አንድም ነገር አልጀምርም:: መሬቱንም መርገጥ ስጀምር እንዲሁ አመሰግናለሁ:: ገላዬን ስታጠብም እቀጥላለሁ:: ቀኑን ሙሉ በሙሉ ለመጀመር ስዘጋጅ ከመቶ በላይ አመሰግናለሁ:: እንዲህ በማድረጌ ቀኔን ተግቼ እየፈጠርኩት ነው:: የቀኑን ፍሪኮንሲ ወስኜዋለሁና ሆን ብዬ የምፈልገውን አይነት ቀን እያሳወቅሁ ነው:: ከአልጋዬ ተደናብሬ ወጥቼ ያ ቀን ተቆጣጥሮኝ እንዲውል አላደርግም:: እያንዳንዱን ቀን ለመጀመር ከዚህ የተሻለ ምንም አይነት መንገድ የለም:: የህይወትህ ፈጣሪ ነህና ቀንህንም ፍጠር::

ምስጋና በታሪክ ውስጥ ያለፉት የታላላቅ መምህራን የአስተምህሮ ክፍል ነው:: ዋላስ ዋትልስ በ1910 «ሃብታም የመሆን ሳይንስ» ብለው በሰየሙት መፃህፍ ውስጥ ምስጋና ረጅሙ ክፍል ነው:: ይህ መፃህፍ እጅጉን ለውጦኛል:: ሚስጥሩ በሚለው ፊልም የተወነ መምህር ሁሉ ምስጋናን የቀን ተቀን ጉዳዩ አድርጎ ተጠቅሞበታል:: አብዛኞቹ ቀኑን የሚጀምሩት የምስጋና አመለካከትና ስሜትን ይዘው ነው::

ጆ ሱጋርማን የተባሉ ግሩምና የተዋጣላቸው የንግድ ሰው ሚስጥሩ የሚለውን ፊልም ካዩ በኋላ በዚህ ፊልም ውስጥ የወደዱት ነገር ስለምስጋና የሚተርከውን ክፍል እንደሆነና ምስጋና ለህይወታቸው መሳካት ያደረገላቸውን አስተዋፅኦ ነገሩኝ:: ጆ ያጋጠማቸው የህይወት መሳካት እንደተጠበቀ ሆኖ ለትንሿ ነገር እንኳን ማመስገናቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

አለቆረጡም:: የመኪና ማቆሚያ ቦታ ሲያገኙ «አመሰግናለሁ» ይላሉ::
ያ የምስጋናን ኃያልነትና ያደረገላቸውንም ያውቁታል:: እናም ምስጋና
የለናኗራቸው ዘይቤ ሆኗል::

ምስጢሩን ተጠቅሜ ከሞከርኩትና ካነበብኩት የምስጋና ኃይል ከሁሉም
በላይ ሆና አግኝቻዋለሁ:: ሚስጥሩን በማወቅ አንድ ነገር ብቻ ማድረግ
ከቻልክ ምስጋናን ተጠቀም የህይወትህ ዘይቤ መሆን እስከሚችል ድረስ::

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

አሁን በእጅህ የያዝከውን ነገር አስመልክቶ የተለየ ስሜት እስከሚያድርብህ ድረስ ብዙ ጥሩ ነገሮችን መሳብ ትጀምራለህ:: ምስጋናን የሚያስከትሉ ብዙ ሌሎች ነገሮችን ትስባለህ:: የፈለኩት መኪና፣ ሚስት፣ ቤትና የመሳሰሉት የሉኝም ልትል ትችላለህ:: እነዚህ የማትፈልጋቸው ነገሮች ናቸው:: አሁን በእጅህ በሚገኙትና ምስጋና በሚሹ ነገሮች ላይ አተኩር:: አሁን ለያዝከው ሁሉ አመስጋኝ ከሆንክ ሌላ ቆንጆ ነገር ልትሻና ልታገኝ ትችላለህ::

> «ህይወታቸውን በተለየ መንገድ የሚመሩ ብዙ ሰዎች ምስጋና የሚባል ነገር ስለሌላቸው ድሆች ሆነው ይኖራሉ::»
>
> ዋላስ ዋትልስ

በእጅህ ያለውን ሳታመሰግን የበለጠ ለማግኘት አይቻልም:: ለምን? ምክንያቱም ውስታቢስነት ሲሰማህ የምትረጨው አመለካከትና ስሜት አሉታዊ ናቸውና:: የምቀኝነት፣ የተቃውሞ፣ ያለመርካት ወይም የ«በቂ አይደለም» ስሜቶች የምትሻውን አያስገኙህም:: እንዲያውም የማትፈልጋቸውን ነገሮች ይጨምሩብሃል:: እነዚህ አሉታዊ ስሜታዊነቶች መልካም ነገር እንዳይጠጋህ ይከላከላሉ:: አሁን የያዝከውን መኪና ሳታመሰግን አዲስ መኪና ብትሻ ወደ ውጪ የምትልከው ዋናው ፍሪኩንሲ ይኸው ይሆናል::

አሁን በእቅድ ስለያዝከው ነገር አመስጋኝ ሁን:: በህይወትህ ሳጋጠሙህ ነገሮች ሁሉ አመስጋኝ ሆነህ ስታስብ ተጨማሪ ምስጋና የምትሰጥባቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሮች ያለማቋረጥ ሲሆኑ ታይና ትደነቃለህ። መጀመር አለብህ። የስበት ህግም እነዚህን አመስጋኝ አመለካከቶች ያገኛቸዋልና ጨማምሮ ይሰጥሃል። በማመስገን ፍሪኩንሲ ትታጠርና ሁሉም መልካም ነገሮች ያንተ ይሆናሉ።

«የየቀኑ ምስጋናህ ፀጋ ወዳንተ የሚመጣበት ማስተላለፊያ ቀዳዳ ነው»።
-ዋላስ ዋትልስ

**ሊ ብሮወር**

ነገሮች በትክክል እየሄዱ አይደለም ሲሉ ሰዎች እያንዳንዱ በጊዜ ውስጥ እያለፈ ነው ብዬ እገምታለሁ። አንዴ በቤተሰቤ ውስጥ የሆነ ነገር በተከሰተበት ወቅት አንድ አለት አገኘሁና ይገፋው ቁጭ አልኩ። ይህን አለት ወሰድኩት። በኪሴ አስቀመጥኩትና ይህን አለት በነካሁት ቁጥር አንድን የማመሰግነውን ነገር ማሰላሰል እጀምራለሁ። እናም ጧት ጧት ከአንቅልፍ ስነሳ ከመልበሻው አወጣና ይህን አለት በኪሴ እከተዋለሁ። ምስጋና ለማቅረብ የምገዳደባቸውን ነገሮች ማሰላሰልም እጀምራለሁ። ማታ ምን አደርጋለሁ? ኪሴን ባዶ አደርጋለሁ።

በዚህ አሳብ ያጋጠመኝ የሆነ ተሞክሮ ነበረኝ። አንድ ከደቡብ አፍሪካ የመጣ ሰው ስጥለው አይቶኝ ነበር። ምንድን ነው ብሎ ጠየቀኝ። አስረዳሁትና እርሱም የውስታ አለት ብሎ ሰየመው። ከሁለት ሳምንት በኋላ ከደቡብ አፍሪካ ደብዳቤ ደረሰኝ። ሰውዬው በደብዳቤው «ልጄ ታይቶ በማይታወቅ ህመም እየተሰቃየ ነው» ብሎ ገፊልኝ። የጉበት በሽታ አይነት ነው ህመሙ። ሶስት የምስጋና አለቶች እንድልክለትም ጠየቀኝ። በመንገድ ያገኟቸው ማንኛውም አይነት አለቶች ናቸው። በእርግጥ እንደምልክለት ነገርኩት። አለቶቹ የተለዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነበረብኝና ወደ ወንዙ ሄድኩ። ትክክለኞቹን አለቶች መረጥኩ። ለሰውየውም ላኩለት።

ከአራትና አምስት ወራት በኋላ ከሰውየው ደብዳቤ ደረሰኝ። ልጁ መዳኑንና እንደገድ እየሰራ መሆኑን ገለፀልኝ። የሆነ ነገር ማወቅ ያለብኝ መሆኑን ነገረኝ። የምስጋና አለቶች በማለት ከሺህ በላይ

*አለቶቻችን አንዱን በአስር ዶላር ሸጠናል:: ገንዘቡንም ለበጎ አድራጎት አውለነዋልና እናመሰግንሃለን ብሎ ነገረኝ::*

ስለዚህ የአመስጋኝነት ባህሪ መኖር በጣም ጠቃሚ ነው::

ታላቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን ጊዜን፣ ቦታንና ግራቪቲን የምናይበትን መንገድ በአይነት ለውጦታል:: እንደኋላቀር መነሻውና ደሃ አጀማመሩ አንስታይን ያደረገውን ሁሉ ለማግኘት አይችልም ብለህ ማመን ትችል ነበር:: አንስታይን ስለሚስጥሩ ብዙ ያውቅ ነበርና በቀን መቶ ጊዜ «አመሰግናለሁ» ይል ነበር:: ከእርሱ በፊት አስተዋጽኦ ያደረጉትን የሳይንስ ሊቃውንት አመስግኗል:: ለእራሱ እድገት ያደረጉትን አስተዋጽኦም ተገንዝቦ ነበር::

የምስጋና አንዱ ጥቅም የምትፈልገውን ነገር ለማጋጋል በፈጠራ ሂደት ውስጥ ሊካተት መቻሉ ነው:: ጠይቅ በሚለው የመጀመሪያው የመፈጠር ሂደት ቦብ ፕሮክቶር የምትፈልገውን ነገር መዝግበህ በመያዝ ጀምር ሲል ይመክራል:: «እያንዳንዱን አረፍተ ነገር ደስተኛና ባለውለታ ነኝ ብለህ ጀምረው » ይላል::

ልክ የፈለከውን እንደአገኘህ ሆነህ አመሰግናለሁ ስትል ለአለም እጅግ ሃይለኛ ምልክት መላክህ ነው:: ያ ምልክት አሁን እያመሰገንክ በመሆኑ በእጅህ አስገብተኸዋል ይላል:: በእያንዳንዷ ጧት ከአልጋህ ስትነሳ የማመስገን ስሜት መሰማትን ባህል አድርገው::

ምስጢሩን ካወቅሁበትና ይህን ከሌሎች ጋር ለመጋራት ራዕይ ከሠነከበት ጊዜ አንስቶ ለአለም ደስታን የሚያመጣው የሚስጥሩን ፊልም ሳላመሰግን የዋልኩበት ቀን የለም:: ይህን እውቀት እንዴት አድርገን ወደ የፊልም ሾራ ማምጣት እንዳለብን የሚመለከት ምንም ሃሳብ አልነበረኝም:: መንገዱን እንደምናገኘው እምነት ብቻ ነበረኝ:: አተኩሬ ተቀመጥኩና ውጤቱን መጠባበቅ ጀመርኩ:: አስተድሜ ከፍተኛ ምስጋና ተሰማኝ:: እንደዚያ መሆን ስጀምር የጎርፉ በሮች ተከፈቱና ሚስጥሩ ወደህይወታችን መጉረፍ ጀመረ:: ስታላቁ የሚስጥሩ ቡድንና

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔም የልባዊ ስሜቶችና ውለታ እስከአሁን አልተለዩንም። ምስጋና የሚያቃጭልብንና የህይወታችን ዘይቤ የሆነብን ቡድን ሆነናል።

## በአይነ ህሊና የማየት ሃያል ሂደት

በአይነ-ህሊና ማየት ቀደምትና የወቅቱ ሊቃውንት ብዙ ያሉለት ሂደት ነው። «የዋናው ቁልፍ» በሚል በ1912 ቻርለስ ሀኔል በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ደራሲው 24 ሙከራዎችን በየሳምንቱ ይሰጣል። ይህንም የሚያደርገው በአይነ-ህሊና ማየትን ለማለማመድ ነው።

በአይነ-ህሊና ማየት ኃያል ነገር ነው። ምክንያቱም እራስህን ከምትፈልገው ነገር ጋር በአይምሮህ እየሳልክ ስታይ የምትፈልገውን ነገር አሁኑኑ የማግኘት አመለካከትና ስሜት ስለሚፈጥርህ ነው። በአይነ ህሊና ማየት ማተኮርና ጠንካራ ስሜትን መቀስቀስ ነው። በአይነ-ህሊና ስታይ ያን ጠንካራ ፍሪኩንሲ ወደ ውጪ እለም ትልካለህ። የስበት ህግ ያን ጠንካራ አመላካች ይይዝና ስዕሎቹን መልሶ ወደ አንተ ይልክልሃል። ልክ በአይነ ህሊናህ እንዳየሃቸው አይነቶችን ማለት ነው።

### ዶ/ር ዴኒስ ዌትሌይ

*በአይነ-ህሊና የማየት ሂደትን የወሰድኩት ከአፖሎ ፕሮግራም ነው። በ1980 እና 1990 በኦሎምፒክ ፕሮግራም ላይ አካተትኩት። የሚታይ የሞቶር ልምምድ ተብሎ ተጠራ።*

*በአይነ-ህሊናህ ስታይ እውን ታደርጋለህ። ስለአይምሮ አንድ አስደናቂ ነገር አለ። የኦሎምፒክ ሯጮችን በአይምሯቸው እናስሮጣቸውና ስለሁያው ነገር መረጃ የሚለጥ መሳሪያ እንሰካባቸዋለን። በመሮጫ መስክ ላይ ያሳዩት ተከታታይነት በአይምሯቸው ሲሮጡም እንደሚከሰት ታየ። እንዴት ሊሆን ቻለ? ምክንያቱም አይምሮ ሩጫውን እንዴት እንደሮጥከው ስለማይለይ ነው። በአይምሮህ ውስጥ ከነበርክ በአካልህም ትሆናለህ።*

አዲስ ነገር ስለሚፈጥሩና ስለፈጠሯቸው ነገሮች አስብ። ራይት ብራዘርስንና አውሮፕላናቸውን፣ ጆርጅ ኤስትማንንና ፊልሙን፣ ቶማስ

ኦዲሰንንና አምፖሉን፣ አሌክሳንደር ግርሃም ቤልንና ስልኩን፣ ወዘተ አስባቸው። አንድ ነገር የሚፈለሰፈው በፈልሳፊው አይምሮ ውስጥ የነገሩ ምስል ስለነበረ ነው። ቁልጭ አድርጐ በአይምሮው ስላስቀመጠው ስለሳለሙና ውጤቱንም እንዲሁ በአይምሮው ስለሳለሙና በለውየው አማካይነት አዲስ ነገር እንዲፈጠር ያደረጋሉ።

እነዚህ ሰዎች ምስጢሩን አውቀውታል። በማይዳሰሰው ነገር ላይ እምነት ነበራቸው። በውስጣቸው ያለው አቅም አለምን በማገዝ የተፈለሰፈውን ነገር ከለመታየት ወደ መታየት አመጣው። እምነታቸውና ግምታቸው የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ ምክንያት ነበሩ። የነዚህን ሰዎች የመፍጠር ችሎታ በየቀኑ እንጠቀምበታለን።

የነዚህን ፈላስፎች አይነት ጭንቅላት የለኝም ብለህ እያሰብክ ይሆናል። እነርሱ ነገሮችን አርቀው አሰቧቸው እኔ ግን አልችልም እያልክ ታስብ ይሆናል። ከእውነቱ ልትርቅ አትችልምና የምስጢሩን ታላቅ እውቀት ስትገበይ የፈላስፎቹ አይነት አይምሮ የሌለህ ሳይሆን እንዲያውም የበለጠ እንዳለህ ትማራለህ።

## ማይክ ዱሌይ

*በአይነ-ህሊናህ ስታይ ያ ምስል በአይምሮህ መኖሩንና መብሰልሰሉን ስታውቅ ሁልጊዜም በውጤቱ ላይ አትኩር።*

*ምሳሌ አለ። የእጅህን ግልባጭ ተመልከተው። የእጆችህን ግልባጮች፣ የቆዳህን ቀለም፣ የቆዳህን ጠቃጠቆ፣ የደም ቧንቧዎችህን ፣ ቀለበቶችህን ፣ የእጆችህን ጥፍሮች ወዘተ ተመልከታቸው። ሁሉንም ዝርዝር ጉዳዮች ተገንዘባቸው። አይኖችህን ከመክደንህ አስቀድሞ እነዚያን እጆችና ጣቶች በመኪናህ መሪ ዙሪያ እያቸው።*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ይህ ያን ያክል የእጅ ጽሑፍ ተሞክሮ ነው። በአሁኑ ወቅት ተሞክሮው እውነት ነው። የመኪናው መኖር አለመኖር አይሰማህም። ምክንያቱም አለኝ የሚል ስሜት ስላለህ ነው።*

t.me/OLDBOOKSPDF

የዶ/ር ቫይታል ቃላቶች በአይነ ህሊናህ በማየት ወዴት ለመሄድ እንደምትፈልግ ቁልጭ አድርገው አጠቃለውታል:: አይንህን ስትገልጥ እንደሚርገበገበው በአይነ-ህሊናህ ማየት እውነተኛ ይሆናል:: ያ ሁኔታ ያ መልዕክ እውነት ነው:: ማንኛውም ነገር የተፈጠረበት መስክ ነው:: አዚያ መስክ ውስጥ አሁን አካላዊው የእውነተኛው መስክ ውጤት ነው:: ሁሉም ነገር አለህ:: ሲሰማህ ታውቀዋለህ::

**ጃክ ካንፊልድ**

*ስበት የሚፈጥረው ስሜት ነው:: ስዕሉ ወይም አመለካከቱ አይደለም:: ብዙ ሰዎች « ደጉን ነገር ብስብ ወይም የምፈልገውን ነገር በአይነ-ህሊናዬ ማየት ብችል ያ በቂ ነው» ይላሉ:: እንደዚያ እያደረክ ነገር ግን ምንም የመትረፍረፍ ስሜት ካላደረብህ ወይም የመውደድ ስሜት ወይም የደስታ ስሜት ካጣህ የስበትን ኃይል ለመፍጠር አትችልም::*

**ቦብ ዶይል**

*በዚያ መኪና ውስጥ በእውነት እንዳሆንክ ሆነህ አስብ:: ያ መኪና በመኪናው ውስጥ ነኝ ኖሮኝ ቢሆን ብለህ ስታስብ ማለት ነው:: ሆኖ ቢሆን ማለት ግን በአሁኑ ብለህ ማሰብ እርግጠኛ ስሜት ነው:: ወደ ፊት ይሆናል ማለት ሲሆን በዛ ስሜት ጊዜ ያልሆነ ነው:: ከቆየህ ሁልጊዜም የወደፊቱ ነገር እንደሆነ ይኖራል::*

**ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ**

*ያ ስሜትና የውስጥ ምልክታ አሁን የአለም ኃይል ራሱን የማያስከስትበት ክፍት የመውጫ በር መሆን ይጀምራል::*

*«ይህ ኃይል ምን እንደሆነ የምለው የለኝም:: የማውቀው ነገር ቢኖር መኖሩን ብቻ ነው»*

አሌክሳንደር ግርሃም ቤል (1847-1922)

t.me/OLDBOOKSPDF

### ጃክ ካንፊልድ

*ሥራችን እንዴት የሚለውን መለየት አይደለም:: እንዴት የሚለው ምንድን የሚለውን መጥኖ ብለን ስንይዝ ስናምን የሚታይ ይሆናል::*

### ማይክ ዱሌይ

*«እንዴቶች» የአለም መገናኛዎች ናቸው:: ሁልጊዜ ባንተና በህልም መካከል የሚገኘውን አጭር፣ ፈጣንና እጅግ ስላማዊ መንገድ ያውቃሉ::*

### ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ወደ አለማችን ብትመልሰው በታደልከው ነገር ሁሉ እጅግ ትደነቅና ትገረም ነበር:: እዚህ ላይ ነው ምስጢርና ታምራት የሚታዩት::*

የምስጢሩ መምህራችን በአይነ-ህሊና ስታይ የምታመጣውን ነገሮች ያውቋቸዋል::ምስሉን በአይምሮህ ስታይና ስሜት ሲያድርብህ አሁኑኑ አግኝቼዋለሁ ወደሚል እምነት እራስህን ታመጣለህ:: አለማችንንም ታምናለህ:: ምክንያቱም በሚከሰተው ውጤት ስላተኮርክ ነው:: እንዴት ሊሆን ነው ለሚለው ምንም ግንዛቤ ባለመስጠትህ ነው:: በአይምሮህ ውስጥ ያለው ስዕል ልክ እንደሆነና እንደተደረገ ያያል:: ስሜቶችህም ተደርጓል ይላሉ:: አይምሮህና ሁለመናህ እንደሆነ ያዩታል:: ያ ነው በአይነ - ህሊና የማየት ጥበብ::

### ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ይህን በየቀኑ ማድረግ ትፈልጋለህ:: የሚያሰለች ሥራ ግን መሆን የለበትም:: ለምስጢሩ ዋናው ጠቃሚ ነገር ጥሩ ስሜት ነው:: በዚህ አጠቃላይ ሂደት ልትነቃቃ ትፈልጋለህ:: በተቻለ መጠን ልትነቃቃና ልትደሰት ትፈልጋለህ::*

ሁሉም በአይነ-ህሊና የማየት አቅም አለው:: በወጥቤት ስዕል ላመሳከርልህ:: ይህ እንዲሆን መጀመሪያ ወጥቤትን የተመለከቱ አመለካከቶችህን ሁሉ አስወግድ:: ስለወጥቤት አታስብ:: ወጥቤትህን

t.me/OLDBOOKSPDF

ከነቱምሳጥኑ፣ ማቀዝቀዣው፣ ምጣዱ፣ ምንጣፉና የመሳሰሉት ጋር ከአራስህ አውጣው::

የወጥ ቤትህን ምስል በአይምሮህ አይተሃል :: አላየህም? ደህና! በአይነ ህሊናህ አየኸው::

> «አወቀውም አላወቀው እያንዳንዱ በአይነ-ህሊና ያያል:: በአይነ ህሊና ማየት የግባማነት ትልቁ ሚስጥር ነው»::
>
> ጆቬረር ቤህረንድ (1881 - 1960)

ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ ካደረጓቸው ሴሚናሮች ይህን ተሞክሮ አካፍለውናል:: በአይነ-ህሊና የማየትን አስመልክቶ ማለታችን ነው:: እነሆ በአይምሮህ የማይነቃነቅ ስዕል ከፈጠርክ ያን ስዕል ይዞ ለመቆየት ይቸግራል:: ስለዚህ በስዕልህ ላይ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን አክልበት::

ለማስረዳት ያህል ወጥ ቤትህን እንደገና አስታውስ:: በአሁኑ ወቅት ወደ ወጥ ቤቱ ስትገባ አስብ:: ፍሪጁን ከፍተህ ቀዝቃዛ የጠርሙስ ውሃ እንዳገኘህ ይታሰብህ:: ጠርሙሱን ስታነሳ ቅዝቃዜ ይሰማሃል:: ባንዱ እጅህ ጠርሙሱን ይዘህ በሌላኛው ፍሪጁን ዝጋ:: አሁን ወጥ ቤትህን ከተለያዩ እንቅስቃሴዎች ጋር በአይነ-ህሊናህ እያየኸው ነው:: እንዲያ አድርጉ ማየትና ስዕሉንም ለማቆየት አሁን ቀላል ነው:: አይደለም?

> «ከምንገምተው በላይ ኃይልና የማድረግ አድል ሁላችንም ይዘናል:: በአይነ-ህሊና ማየት እጅግ ታላቅ ከሚባሉት ሃይሎች አንደኛው ነው»::
>
> ጆቬረር ቤህረንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

# በተግባር ኃያሉቹ ሂደቶች

## ማርሲ ሺምኦፍ

*በሀይወት ታምር ውስጥ በሚኖሩና በማይኖሩ መካከል ያለው ልዩነት በሀይወት ታምር የሚኖሩቱ የመሆንን መንገዶች ተለማምደዋቸዋል:: የስበት ህግን የመጠቀም ልምድ አዳብረዋል:: በየሄዱበት ሁሉ ታምር ይሆናል:: ምክንያቱም አጠቃቀሙን ያስታውሱታልና ነው:: ለአንዴ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ይጠቀሙበታል::*

ኃያሉን የስበት ህግ ሊያስረዱ የሚችሉ ሁለት የእውነት ታሪኮች አሉ:: አንደኛው ታሪክ ጂኒ በመባል ስለምትታወቅ ሴት ነው::

ጂኒ ምስጢሩ የሚለውን ዲቪዲ የገዛች ናት:: ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ዲቪዲውን ታየዋለች:: እናም መልዕክቱን ወደሰውነቷ ህዋሶች ትመጥጠዋለች:: በተለይ ቦብ ፕሮክቶር ያስገርማታል:: ስለሆነም ብታገኘው ድንቅ እንደሆነ ታስባለች::

አንድ ጧት ጂኒ ፖስታዎቿን ከሣጥኑ አወጣች:: በሚገርም ሁኔታ ፖስተኛው በአጋጣሚ የቦብ ፕሮክተርን ደብዳቤ ከጂኒ ፖስታ ሣጥን ከቶታል:: ጂኒ የማታውቀው ነገር ቦብ ፕሮክቶር ከእርሷ አራት ህንፃዎች ርቆ ይኖር እንደነበር ነው:: ይህ ብቻ አይደለም የጂኒና ቦብ ፕሮክቶር የቤት ቁጥር አንድ አይነት ነበር:: ደብዳቤውን ለትክክለኛው ተቀባይ ለመላክ ወሰደችው:: ቦብ ፕሮክቶር በሩን ከፍቶ ወጥቶ ከፊት ለፊቷ ሲቆም የቱን የህል እንደሚያስደስታት መገመት ትችላለህ? ቦብ በአለም እየተዘዋወረ ስለሚያስተምር አብዛኛውን ጊዜ በቤቱ አይገኝም:: ነገር ግን የአለም የጊዜ ዝንቅ ትክክለኛ የጊዜ አያያዝን ያውቃልና ቦብ ያን ጊዘ ከቤቱ አልወጣም:: የስበት ህግ ሰዎችን፣ ክነቶችንና ሁኔታዎችን ይሆኑ ዘንድ ይስባልና:: ቦብ ፕሮክቶርን ከቤቱ ብታገኘው ጂኒ የቱን ያህል ልትደሰት እንደምትችል ገምታለች::

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለተኛው ታሪክ ኮሊን የሚባል የአስር አመት ልጅን ይመለከታል። ኮሊን ምስጢሩን ተመልክቶታል። ወዶታልም። የኮሊን ቤተሰቦች የአንድ ሳምንት ጉብኝት ዲዝኒ አለም በሚባል በሚታወቀው ቦታ አድርገዋል። በመጀመሪያው ቀን ረዥም የመኪና ሰልፍ አጋጠማቸው። ቃኑ ሲሊት ኮሊንን እንቅልፍ ሳይወስደው «ነገ በሁሉም ቦታ ተሰልፌ ጊዜ ሳልፈጅ መሄድ ይኖርብኛል ብሎ አሰበ»።

በሚቀጥለው ጧት ኮሊንና ቤተሰቡ ልክ ፓርኩ እንደተከፈተ ኤፐኮት ማዕከል በሮች ላይ ደረሱ። የዲዝኒይ ሰራተኛ የሆነ ሰው ጠጋ አለና የኤፐኮት የቀኑ የመጀመሪያ ቤተሰብ እንዲሆኑለት ጠየቃቸው። በዚህ መሠረትም የክብር እንግዳነት ደረጃን ያገኛሉ። የተለየ የመ/ቤቱ ሰራተኛ ያጅባቸዋል። በኤፐኮት ጉዞአቸውን ያለምንም ወረፋ ያደርጋሉ። ኮሊን የተመኘው ማንኛውም ነገር ሆነ።

ያን እለት በመቶ የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ወደ ኤፐኮት ለመግባት መጠበቅ ነበረባቸው። ቤተሰቡ በመጀመሪያነት ለምን እንደተመረጠ ለኮሊን የሚያጠራጥረው ነገር አልነበረም። ሚስጥሩን በጥቅም ላይ ያዋለ መሆኑን ያውቅ ነበርና። በአሥር አመት ላይ አለሞችን የማሽከርከር ኃይል በራስህ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን ማወቅን አስበው።

> «አንድ ሰዕልህ ወደተጨባጭነት ይመጣ ዘንድ ምንም የሚከለክለው ነገር የለም እንደሚመጣ ካደረገው ኃይል ማለትም ከእራስህ በስተቀር»።
>
> ጄቨረር ቡህረንድ

## ጀምስ ሬይ

*ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ ይይዙታል። በእርግጥም የዛው ጉዳይ አሸናፊዎች ናቸው። «ተባርሬአለሁ» ይላሉ። «ይህን ፕሮግራም አይቸዋለሁ እናም ህይወቴን ወደ መለወጥ ልሄድ ነው» ይላሉ። ነገር ግን ውጤቶች አልታዩም። ከመሬት በታች ሰብሮ ለመሄድ ስለመዘጋጀት ነው የሚሉት ሁሉ። ነገር ግን የምድሩን ውጤቶች ሰውየው ይመለከትና « ይህ ነገር አይሰራም» ይላል። ምን እንደሆነ ታውቃለህ? «ምኞትህ ትዕዛዜ ነው » ትለውና ትሰወራለች።*

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጠራጠር አመለካከት በአይምሮህ እንዲሰርፅ ከፈቀድክ የሰበት ህግ ወዲውኑ ከአጠራጣሪ አመለካከቶች ጋር ይቧደናል:: የመጠራጠር አመለካከት ሲመጣብህ ወዲያውኑ አስወግደው:: በመንገዱ አስኪደው:: «አሁን እየተቀበልኩ ነው» በሚል ተካው:: ይሰማህም::

*ጀን አሣራፍ*

*የስበት ህግን አውቄ በጥቅም ላይ ለማዋልና የሚሆነውን ለማየት ፈልጌአለሁ:: በ1995 የራዕይ ሰሌዳ የሚባል ነገር ለመፍጠር ጀምሬ ነበር:: በዚህ ሰሌዳ ላይ እንዲኖረኝ የምፈልገውን ነገር ለማሳየት ፈልጌአለሁ:: እናም በሰሌዳው ላይ የምፈለገውን ነገር ስዕል ሳልኩበት:: በየቀኑ በቢሮዬ ውስጥ ተቀምጬ ይህን ሰሌዳ አመለከትና በአይነ-ህሊናዬ ያለ ምንም ጥርጥር የፈለኩትን ነገር ያገኘሁት ወደሚመስለኝ ሁኔታ እገባ ነበር::*

ለመንቀሳቀስ ዘግጁ ነበርኩ:: እቃዎችን ሁሉ መጋዘን ውስጥ አስቀመጥኩ:: በአምስት አመታት ውስጥ ሶስት የተለያዩ ጉዞዎች አድርጌአለሁ:: ጉዞዬ ካሊፎርኒያ ላይ ተጠናቀቀና ይህን ቤት ገዛሁ ከጥንት ቤቴ የነበረውን የቤት እቃ አመጣሁ:: አንድ ጧት ልጄ ኪናን ወደ ቢሮዬ መጣ:: ለአምስት አመት ታሽጐ የቆየው አንድ ሳጥን ከበሩ መግቢያ አጠገብ ነበረ:: «በሣጥኑ ውስጥ ምን አለ አባባ?» አለና ጠየቀኝ «የእኔ የራዕይ ሰሌዳዎች ናቸው» አልኩት:: «የራዕይ ሰሌዳ ምንድን ነው?» አለና እንደገና ጠየቀ «ደህና ግቦችን ሁሉ የማስቀምጥበት ነው» አልኩት:: በእርግጥም የአምስት አመት ተኩል ልጅ ሆኖ ያልኩትን ሊረዳኝ አልቻለም:: «ሆዴ ላሳይህ ቀላሉ መንገድ ይህ ነው» አልኩት::

ሳጥኑን ከፈትኩት:: በአንዱ የራዕይ ሰሌዳ ላይ ከአምስት አመት በፊት በአይነ-ህሊናዬ አየው የነበረው ቤት ስዕል ተስሏል:: የሚገርመው ነገር በዚያ ቤት ውስጥ ነበር የምንኖረው:: የገዛሁት የህልም ቤቴን ነበር:: ያን ቤት አይቼ አለቀስኩ:: ምክንያቱም በጉን ስላልኩ ነው:: «ለምን ታለቅሳለህ» ሲል ኪናን ጠየቀኝ:: በመጨረሻም የስበት ህግ እንዴት እንደሚሰራ ገባኝ:: የአይነ-ህሊና የማየት ኃይል ገባኝ:: ያነበብኩት፣

t.me/OLDBOOKSPDF

በህይወቱ ያደረኩት ፋብሪካዎችን የገነባሁበት መንገድ ሁሉ ቶይቶ ገባኝ:: ለመኖሪያ ቤቴም የሆነው እንዲያ ነው:: የህልም ቤታችንን ገዝሁት ነገር ግን አላወኩትም::

«መተንበይ ሁሉንም ነገር ነው:: የህይወት መጻኢ መሳቦች ቅድመ- እይታ ነው»::

አልበርት አንስታይን (1879-1955)

ትንበያህን ከራዕይ ሰሌዳ ጋር ባዕድ ልታደርገው ትችላለህ:: የምትፈልጋቸውን ነገሮች ስዕሎች በሰሌዳው ላይ ማስቀመጥ ትችላለህ:: ሰሌዳውን ሁልጊዜ ለማየት ከምትችልበት ቦታ ማስቀመጥህን አረጋግጥ:: ጆን አሣራፍ እንዳደረገት ማለት ነው:: የሳልካቸው ነገሮች አሁን በእጅህ እንደሚገኙ ይሰማህ:: ስታገኝና ስላገኘህም የምስጋና ስሜት ሲሰማህ ይህ ስዕሎቹን አጥፍተህ ሌሎች አዲስ ስዕሎችን ማስቀመጥ ትችላለህ:: ህፃናት ስለስበት ህግ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚረዳ አስገራሚ ዘዴ ነው:: የራዕይ ሰሌዳ ማዘጋጀት በአለም የሚገኙ ወላጆችንና መምህራንን እደሚያነሳሳ ተስፋ አደርጋለሁ::

በምስጢሩ ድረ-ገጽ መድረክ ከሚገኙት አንዱ የሚስጥሩን ዲቪዲ በራዕይ ሰሌዳው ላይ ሳለው:: ምስጢሩ የሚባለውን ፊልም አይቶታል:: ነገር ግን የራሱ ቅጂ የለውም:: የራዕይ ሰሌዳውን ካዘጋጀ ከሁለት ቀናት በኋላ አስቀድመው ካስታወቁት መካከል ለመጀመሪያ አስሮቹ ዲቪዲ የመስጠት ማስታወቂያ ለመለጠፍ ተነሳሳሁ:: የራዕይ ሰሌዳውን ያዘጋጀው ሰው ከአሥሩ አንዱ ነው:: በራዕይ ሰሌዳው ላይ ካስቀመጠው ከሁለት ቀናት በኋላ:: የምስጢሩ ዲቪዲ ይሁን የመኖሪያ ቤት የመፍጠርና የማግኘት ደስታ ከፍተኛ ነው::

ሌላው በአይነ ህሊና የማየት ተሞክሮ ማስረጃ እናቴ አዲስ ቤት ከመግዛቷ ጋር የተያያዘ ነው:: እናቴን ጨምሮ አያሌ ሰዎች ይህን ቤት ለመግዛት ጠይቀዋል:: እናቴ ያን ቤት የራሷ ለማድረግ ሚስጥሩን ለመጠቀም ወስናለች:: ቁጭ አለችና ስሟንና የዚያን ቤት አድራሻ ደጋግማ ፃፈች:: ያ አድራሻ የእርሷ እስከሚመስላት ድረስ መፃፏን ቀጠለች:: የቤት እቃዎቿን ሁሉ በዛ ቤት ውስጥ ስታስገባ ታያት:: ይህን ባደረገች በሰአታት ውስጥ ቤቱን ለመግዛት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት

t.me/OLDBOOKSPDF

ማግኘቱን በስልክ ተነገራት:: ተንቀጠቀጠች:: ገዥም ብሎ የሆነላት ግን ለአነበረም ምክንያቱም ቤቱ የእርሷ መሆኑን ቀድማ አውቃለችና ነው::

**ጃክ ካንፊልድ**

የምትፈልገውን ወስን:: እንደምታገኘ እመን:: ልታገኘው እንደሚገባና ያን ለማድረግ እንደሚቻል እመን:: አይኖችህን ለደቂቃዎች በየቀኑ ዝጋ:: የምትፈልገው ነገር እንደሚኖርህ በአይነ-ህሊናህ ይታይህ:: በእጅ ነው የሚል ስሜት ይሰማህ:: ከዛ ውጣና በምታመሰግነውና እያስደሰተህ ባለው ነገር ላይ አትኩር:: ወደ ቀንህ ሂድና ለአለም አርጨው:: አለምም ስትስብህ እመን::

## የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ጠባቂነት ኃይለኛ የመሳብ ሃይል ነው:: የምትፈልጋቸውን እንጂ የማትፈልጋቸውን ነገሮች አትጠብቅ::
- ምስጋና ኃይልህን ለመቀየርና የምትፈልገውን ነገር በበለጠ በህይወትህ ለማግኘት የሚረዳ ኃይለኛ ሂደት ነው:: በእጅህ ላለ ነገር አመስጋኝ ሁን:: እንዲያ ስትሆን ተጨማሪ ጥሩ ነገሮችን ትስባለህ::
- ወደፊት እንዲሆንልህ ለምትፈልገው ነገር ቀድመህ ማመስገን ፍላጎቶችህን ያጉለብታቸዋል:: የበለጠ ኃይለኛ አመላካች ወደ ውጪው አለም ይሰዳል::
- በአይነ-ህሊና ማየት በአይምሮህ ውስጥ የምትፈልጋቸው ነገሮች እያስደሰቱህ እያሉ ምስላቸውን የመፍጠር ሂደት ነው:: በአይነ ህሊና ስታይ አሁን አለኝ የሚል ኃይለኛ አመለካከትና ስሜትን ትፈጥራለህ:: የስበት ህግም ያን እውነት መልሶ ይልክልሃል:: ልክ በአይምሮህ እንደአየኸው አይነት አድርጎ::
- የስበት ህግን እንዲጠቅምህ አድርገህ ለመጠቀም የኑሮ ልምድህ እንጂ የአንድ ጊዜ ብቻ ኩነት አታድርገው::
- እያንዳንዱ ቀን ሲገባደድና ከመተኛትህ በፊት በዛ ቀን ውስጥ ስታደርጋቸው ወደዋልካቸው ነገሮች ተመለስ:: በፍላጉትህ ውስጥ ያልነበሩ ኩነቶችንና ወቅቶችን እንደገና አስተውላቸውና እንደምትፈልጋቸው አይነት አድርገህ አስተካክላቸው::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የገንዘብ ምስጢር

«አይምሮ የፀነሰውን . . . ያገኘዋል»

ደብሊው ክለመንት ሥቶን (1920 - 2002)

ጃክ ካንፊልድ

*ምስጢሩ ለእኔ እውነተኛ መለወጡ ነው:: ምክንያቱም ሃብታም ሰዎች የሌሎችን ሃብት በጥብጠው የበለፀጉ ናቸው ብሎ የሚያምን አባት የሳደገኝ በመሆኑ ነው:: እናም ያደኩት ስለገንዘብ አያሌ ነገሮችን እየሰማሁ ነበር:: «ገንዘብ ካለህ መጥፎ ትሆናለህ:: ሰይጣን ሰዎች ብቻ ናቸው ገንዘብ ያላቸው:: ገንዘብም ከዛፍ ላይ አይለቀምም:: ማን እመስልሃለሁ? ሮክ ፌለር?» የሚሉት አይነት አባባሎች የአባቴ ተወዳጅ አባባሎች ነበሩ:: በዚህ አይነቱ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው ያደኩት:: ደብሊው ክለመንት ስቶንን ካገኘሁ በኋላ ነው ህይወቴን መለወጥ የጀመርኩት:: ስቶን « ግብ እንዲኖርህ እሻለሁ:: ግብህም ትልቅ ሆኖ ስታገኘው አይምሮህን ብው የሚያደርግ መሆን አለበት:: ይህ የሚሆነውም ይህን ግብ ታገኛለህ ብዬ ስላስተማርኩህ ነው» አለኝ አብሬው እሰራ በነበረ ጊዜ:: በአመት ወደ ስምንት ሺህ ዶላር በማገኝበት ወቅት ነበር ስቶን እንዲያ ያለኝ:: አሁን እንዴት ያን አደርግ እንደነበር ምንም ሃሳብ የለኝም:: ምንም ስትራቴጂ አልነበረኝም:: የሚሆንበት አጋጣሚም እንዲሁ:: «ይህን አባባል ላምነው ነው፣ ላውጅ ነው፣ እውነት እንዲሆን አድርጌ ልንቀሳቀስ ነው» አልኩ:: አደረኩትም::*

*ካስተማረኝ ነገሮች አንዱ በየቀኑ አይኖቼን ዘግቼ ግቦቼን በአይነ ሀሊናዬ ማየት ያለብኝ መሆኑን ነበር:: ለነገሩ ያን ጊዜ መቶ ሺህ*



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶላር ከጠራቤ አስቀምጬ ነበር:: አንድ ጧት የገንዘቡን መኖር ለረጋግጥ አገኘሁት:: አለ:: እናም አይኖቼን ዘግቼ ይህን መቶ ሺህ ዶላር በአይኑሀሊ ናቤ የማየት የአንድ አመት ልምድ አዳበርኩ:: የሚገርም ሁኔታ ለሠላሳ ቀናት ምንም የሆነ ነገር አልነበረም:: ማንም ተጨማሪ ገንዘብ አልሰጠኝም::

ለአራት ወራት የመቶ ሺህ ዶላር ሃሳብን አስተናግጃለሁ:: ወደጭንቅላቴ መጣ:: የፃፍኩት መፃህፍ ነበረኝ:: «አራት ሺህ መፃህፍት እንዱን በሩብ ዶላር መሸጥ ብችል አንድ መቶ ሺህ ዶላር መሆን ይችላል» አልኩ:: አሁን መጽሐፉ እዛው ነበር:: ይህ አስተሳሰብ ግን አልነበረኝም:: አራት መቶ ሺህ ቅጆችን እንዴት አድርጌ መሸጥ እንዳለብኝ አላወቅኩም ነበር::

በሱፐርማርኬቱ ውስጥ ብሔራዊ አፈላላጊን አየሁ:: ለሚሊዮን ጊዜ ያን አይቼዋለሁ:: ወዲየውኑ ተስፈንጥሮ ወጣና ከመነሻ ሃሳብነት ወደመድረሻነት ተለወጠ:: «መጽሐፌን አንባቢዎች ቢያውቁት በእርግጠኝነት አራት መቶ ሺህ ሰዎች ይወጡና ይገዙት ነበር» ብዬ አሰብኩ::

ከስድስት ሳምንታት በኋላ ኒው ዮርክ ከሚገኘው ሁንተር ኮሌጅ ንግግር አደረኩ:: ንግግሩን ያደረኩት ለስድስት መቶ መምህራን ነበር:: ጥቂት ቆይታ የሆነች ሴት ቀረበችኝና « ጥሩ ንግግር ነበር:: ቃለ-መጠይቅ ላደርግልህ እፈልጋለሁ:: ካርዴን እሰጥሃለሁ» አለችኝ:: ለካስ የግል ታሪኳን ለብሔራዊ አፈላላጊ የሸጠች የግልና የነፃ ጋዜጠኛ ኖራለች:: የመፃህፉ ታሪክ ተገኘና ሽያጩም ይጦፍ ገባ::

ለማሳየት የፈለኩት ነጥብ እነዚህን ኩነቶች ሁሉ ሲትዮዋንም ጨምሮ ወደ ህይወቴ እየሳብኳቸው የነበረ መሆኑን ነው:: ታሪኩን ሳጥሬ በዛ አመት መቶ ሺህ ዶላር አላገኘሁም:: ዘጠና ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ዶላር ብቻ ነው ያገኘነው:: «አያዋጣም» ያልን ይመስልሃል? አላልንም:: ያልነው «ያስደንቃል» ነው:: ሚስቴ «መቶ ሺህ የሚያወጣ ከሆነ ሚሊዮንስ ለምን አያወጣም ?» ለለችኝ:: «አላውቅም፣ የሚያወጣ ይመስለኛል:: እስኪ እንሞክረው» አልኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

*የተመልኝ ከብጊኒያ የሮምሊቲ ቼክ ፃፈልኝ:: በፊርማው ላይ ፈንግ የሚታይበት ገስ አትሯል:: ምክንያቱም በህይወቱ የሃፊው የመጀመሪያው ሚሊዮን ቼክ በመሆኑ ነው::*

የምስጢሩ እውቀትንና የስበት ህግን አጠቃቀም በህይወትህ ለማንኛውም ነገር ታውላቸዋለህ:: ሂደቱ ለማንኛውም ነገር የሚሆን ነው:: ገንዘብ ከዚህ የተለየ አይደለም::

ገንዘብን ለመሳብ በሃብት ላይ አትኩሮት ማድረግ ይኖርብሃል:: ብዙ ገንዘብ የለኝም እያልክ የበለጠ ገንዘብ ለማምጣት አይቻልም:: ምክንያቱም በቂ የለኝም የሚል አመለካከት እያውጠነጠንክ ነው ማለት ነው:: በቂ ያልሆነ ገንዘብ በሚል ትኩረትክ በቂ ገንዘብ የለኝም የሚሉ ለመናገር የሚያስቸግሩ የበለጡ ሁኔታዎችን ትፈጥራለህ:: ይመጣልህ ዘንድ ስለተትረፈረፈ ገንዘብ አተኩር::
አዲስ አመላካች እርጭ በሃሳብ ደረጃ:: እጅግ ብዙ ገንዘብ በዛ ወቅት እንዳለህ ይሰማህ:: ሃብታም ነኝ የሚል ጨዋታ ስትጫወት በትዕበት ስለገንዘብ የተሻለ ስሜት ያድርብሃል:: ወደ ህይወትህም መፍሰስ ይጀምራል::

የጄክ አስገራሚ ታሪክ የሚስጥሩ ቡድን ባዶ ቼክ በሚስጥሩ ድረ-ገጽ ላይ እንዲፈጥር አደረገው:: ባዶው ቼክ ለአንተ ነው:: የተላከልህም ከአለማችን ባንክ ነው:: መሞላት ያለባቸውን መረጃዎች ሙሉና በየቀኑ ለማየት ከምትችልበት ቦታ አኑረው:: የገለፅከውን የሚያክል ገንዘብ አሁን ያለህ መሆኑ ስሜት ይሰጥህ:: ገንዘቡን ስለተለያዩ ነገሮች ስታወጣው ይታይህ:: አስደሳች መሆኑ ይሰማህ:: ያንተ መሆኑን እወቅ:: የሚስጥሩን ቼክ ተጠቅመው ብዙ ገንዘብ ያገኙ መሆናቸውን የሚገልፁ አያሌ ታሪኮችን ከብዙ ሰዎች አግኝተናል:: የሚሰራ አስቂኝ ጨዋታ ነው::

## መትረፈረፍን ሳብ

ብዙ ሰዎች ገንዘብ የማይኖራቸው ወደነሱ እንዳይመጣ በአመለካከታቸው ስለሚገድቡት ነው:: እያንዳንዱ አሉታዊ አመለካከት ምንም መልካም ነገር እንዳይቀርብ ይከለክላል:: ገንዘብም እንዲሁ ነው:: አሁን

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትፈልገው ገንዘብ ሁሉ በማይከለትበት ሁኔታ ይገኛል:: በቲ ገዘብ ከሌለህ ወደአንተ እንዳይመጣ በአመለካከትህ ገድበኸዋል:: ከገንዘብ የለኝም ብዙ ገንዘብ አለኝ ወደሚል ተሸጋገር:: ከጥንጣን ይልቅ ስለ አርዜት አስብ::

ገዘብ ስትፈልግ በውስጥህ ሃይለኛ ስሜት ይፈጠራል:: በስበት ህግ አማካይነት የምትፈልገው ገንዘብ ወደ አንተ ይሳባል::

ከልምዴ ልንገራችሁ:: ምስጢሩን ከማወቁ በፊት ድርጅቴ በዛ አመት ከፍተኛ ኪሳራ የገጠመው መሆኑን የሂሳብ ሰራተኞች ነግረውኝ ነበር:: አስር አመት ደከሜ ድርጅቴ ከዕጄ አምልጦ ሊወድቅ ነበር:: ድርጅቴን ከውድቀት ለማዳን የሚበጅ ገንዘብ ስሻ ነገሮች ሁሉ ባሰባቸው:: መውጪያ መንገድ የሌለ መሰለኝ::

ምስጢሩን ካወቅሁ በኋላ ነገሮች ሁሉ ተለወጡ:: የድርጅቴ ሁኔታም እንዲሁ:: ምክንያቱም የአስተሳሰብ ዘዴዬን ቀየርኩ:: የሂሳብ ሰራተኞቹ ስለድርጅቴ መውደቅ ሲነዛነዙ እኔ ስለተትረፈረፈ ሃብትና ደህንነት ማተኮር ጀመርኩ:: እያንዳንዱ የሰውነቴ ክፍል ይህች አለም ያለመሰሰት እንደምትሰጠኝ ያውቅ ነበር:: ሰጠችኝም:: በመጠራጠር ፋንታ የምፈልገው እንደሚሆን ማሰብ ጀመርኩ:: ምስጋናም አቀረብኩ:: ደስታም ተሰማኝ:: አመንኩም::

በምስጢር ወደምስጢሩ እንድትገባ እፈልጋለሁ::

በህይወትህ ወደምትፈልገው ለመድረስ አጭሩ መንገድ አሁን ደስተኛ መሆንና ደስታ መሰማት ናቸው:: ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ለማግኘት እጅግ ፈጣኑ መንገድ ይህ ነው:: ወደ ውጪው አለም የደስታና የመርካት ስሜቶችን እርጭ:: እንደዚያ ስታደርግ አሀፋውን ታገኛለህና:: የምትፈልገውን መልሶ የሚያመጣ አመላካች አስፈንጥር:: ስታስፈነጥር ተመልሰው ወደ አንተው የህይወትህ ምስሎችና ተሞክሮዎች ሆነው ይላኩልሃል:: የስበት ህግ ውስጣዊ አመለካከቶችህንና ስሜቶችህን የህይወትህ ክፍል አድርጎ መልሶ እያንፀባረቃቸው ይገኛል::

t.me/OLDBOOKSPDF

# በብልፅግና ላይ አተኩር

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*እንዴት አድርጌ ብዙ ገንዘብ ላገኝ ነው የሚለው የብዙ ሰዎች ጭንቀትን መገመት እችላለሁ:: መልሱም ተመኝ ነው:: በምስጢሩ ስንነጋገርባቸው ከነበሩት ነገሮች መካከል አንዱ ይኸው ነበር:: ያንተ ኃላፊነት የምትፈልገውን ማሳወቅ ነው:: አንዱ ገንዘብ ከሆነ መጠኑን አሳውቅ:: ሃያ አምስት ሺህ ዶላር እንዲኖረኝ፣ ያልተጠበቀ ገቢ እንዳገኝ፣ በሚቀጥሉት ሰላሳ ቀናት ገንዘብ ማግኘት እንድችል ወዘተ እፈልጋለሁ ብለህ አሳውቅ:: ልታምነው የሚገባ መሆን አለበት::*

ላለፉት ጊዜአት ገንዘብ ላገኝ የምችለው በሥራዬ ብቻ ነው ብለህ ስታምን ኖረህ ከሆነ ይህን አመለካከት ወዲያውኑ አስወግድ:: እንዲህ አይነት አመለካከት አይጠቅምም::

የተትረፈረፈ ሀብት ያለህ መሆኑን አሁን ወደመገንዘቡ እየመጣህ ነው:: እንዴት ሆኖ ገንዘቡ ወደ አንተ መምጣት እንደሚችል ያንተ ሥራ አይደለም:: ያንተ ሥራ መጠየቅ፣ እያገኘህ እንደሆነ ማመንና አሁኑኑ መደሰት ነው:: ገንዘቡን እንዴት እንደምታመጣልህ ለአለም ተውላት::

## ቦብ ፕሮክቶር

*ብዙ ሰዎች ከዕዳ ነፃ የመሆን ግብ አላቸው:: ይህ አይነት ፍላጎት ለዘለአለሙ ከእዳ ሳትወጣ እንድትኖር ያደርግሃል:: እንዲሆን የምታስበውን ነገር ሁሉ ትስበዋለህ:: «ከዕዳ ልላቀቅ» ትላለህ:: ከዕዳ እየወጣህ ይሁን እየገባህ አያገባኝም:: እዳን እያብሰለሰልክ ከሆነ እዳን እየሳብክ ነው:: ዕዳህን የምታወራርድበት ፕሮግራም ቀይስና በመበልፀግ ላይ አተኩር::*

እንዴት መክፈል እንዳለብህ ግራ የሚያጋቡ ዕዳዎች ካሉብህ በነዚያ ዕዳዎች ላይ ለማተኮር አትችልም:: ምክንያቱም ሌላ ተጨማሪ ዕዳ ስለምታመጣ ነው:: በብልፅግና ላይ ብቻ እንድታተኩር የሚረዳህ መንገድ ማግኘት ይኖርብሃል:: ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ የሚያደርግ መንገድ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሸት አለብህ:: የፈለገው ዕዳ ይኑርብህ እንዲህ ስታደርግ ብቻ ነው መልካሙን ሁሉ ማግኘት የምትችለው::

## ጀምስ ሬይ

*«በሚቀጥለው አመት ገቢዬን በሁለት እጅ አጥፈዋለሁ» ይላሉ ብዙ ሰዎች:: የሚያደርጉትን ተመልከት:: ያሰቡት እንዲሆን የሚረዳ ምንም ተግባር አይፈፅሙም:: ወዲያና ወዲህ ይንገላወዱና «አልችለውም» ይላሉ:: ገምት ምን? «ምኞትህ ትዕዛዜ ነው»::*

«አልችለውም» የሚለው ቃል በአፍህ ወጥቶ ከሆነ ይህን ለመለወጥ ያለህ አቅም አሁን ነው:: «እችለዋለሁ» በሚል ቀይረው:: ደጋግመህ ተናገረው:: እንደገደል ማሚቶ ሁን:: ለሚቀጥሉት ሰስት ቀኖች የምትሻውን ነገር ሁሉ እያየህ «ይኖረኛል» በል:: የምትመኛትን መኪና ሲነዷት ካየህ «ይኖረኛል» በል:: እንዲህ ስትል እራስህን ትቀይራለህ:: ስለገንዘብም የተሻለ ስሜት ያድርብሃል:: የህይወት ስዕሎችህ ሁሉ ይለወጣሉ::

## ሊዛ ኒኮልስ

*በእጥረትና አለመኖር ላይ አተኩረህ ከቤተሰብህ ጋር ብትነዛነዝበት፣ ከጓደኞችህ ጋር ብትወያይበት፣ ለልጆችህ በቂ ገንዘብ የለኝምና ልንገዛው አንችልም ብትላቸው መቼውንም ልትገዛው አትችልም:: ምክንያቱም ወደ አንተ የምትስበው የበለጠ የሌለህን ነገር ስለሚሆን ነው:: የተትረፈረፈ ሃብት ወይም ብልፅግና የምትፈልግ ከሆነ በመትረፍረፍና ብልፅግና ላይ አትኩሮት አድርግ::*

> «የሚታይ ሃብት የሚመጣበት መንፈሳዊ መነሻ አልተገባደደም:: ሁልጊዜም ካንተ ጋር ነው:: ለዕምነትህና ጥያቄህ አፀፋ ይሰጣል»::
>
> ቻርለስ ፊልሞር (1854-1948)

አሁን ምስጢሩን ታውቃለህና እንድ ባለፀጋ ስታይ የዛ ሰውዬ አስተሳሰብ አብዛኛውን ጊዜ ስለሃብት እንጂ ስለማጣት እንዳልሆነ ታውቃለህ:: ቸር

t.me/OLDBOOKSPDF

በመመኘታቸው ቸር እንዳገኙ ትረዳለህ:: ሃብት በማጊለጡ ላይ አተኩሩና አለሃም በፈለጉት መልኩ ሰዎችን፣ ሁኔታዎችንና ኩነቶችን ልትሰጣቸው አንቀሳቀሰችላቸው::

እነሱ ያላቸው ሃብት አንተም አለህ:: ባንተና በነርሱ መካከል ያለው ልዩነት እነሱ ሃብት ያመጡላቸውን አመለካከቶች አስበዋቸዋል:: ሃብትህ በማይከሰተው ሁኔታ ላይ ይገኛልና ወደማጊታይነት እንዲመጣ ሃብትን አስብ::

## ዳቪድ ሺርመር

*ምስጢሩ መጀመሪያ እንደገባኝ ሰሞን በፖስታ ሣጥኔ ውስጥ ማይታ እዳ አገኝ ነበር:: «እንዴት ይህ ሁሉ ሊመጣ ቻለ ?» እያልኩ አስብ ነበር:: የሰበት ህግ የምታተኩርበትን ሁሉ ታገኘዋለህ ይላል:: እናም የባንክ ሂሳብ ደረሰኝ:: በደረሰኙ ላይ የነበረውን አጥፍቼ አዲስ ድምር አስቀመጥኩ:: በባንኬ ውስጥ ማግኘት የምፈልገውን መጠን ነው ያስቀመጥኩት:: የቼክ ጥራዝ በፖስታ ሣጥኔ ውስጥ ሲላክ በአይነ ህሊናዬ አየሁ:: በአንድ ወር ውስጥ ነገሮች መለወጥ ጀመሩ:: የሚገርም ነው:: በፖስታ ሣጥኔ ውስጥ ዛሬ ቼክ አገኘሁ:: ጥቂት እዳ ብቻ መጣብኝ:: ከዕዳዬ የበለጠ ቼክ ግን መጣልኝ::*

ምስጢሩ የሚለው ፊልም ከታዬ ወዲህ ብዙ ሰዎች «ፊልሙን ካየን ወዲህ ብዙ ቼኮች አገኘን» ብለው ነግረውናል:: ይህ የሆነበት ምክንያት አትኩሮታቸውንና ግንዛቤአቸውን በዳዊት ታሪክ ላይ ማድረግ ከጀመሩ በኋላ አትኩሮታቸውና ግንዛቤአቸው ቼክ ስላመጡላቸው ነው::

አንድ ጨዋታ ፈጠርኩ:: ይህም ጨዋታ ስሜቴን ለወጠልኝ:: በዚህ ጨዋታ እዳዎች ሁሉ ቼኮች እንደሆኑ አድርጌ አስመሰልኩ:: ቼኮቹን እከፍትና በመደሰት «ብዙ ገንዘብ ለእኔ፣ አመሰግናለሁ» እላለሁ:: እያንዳንዱን እዳ ቼክ ነው ብዬ እገምታለሁ:: እንዲያውም ከፊትለፊቱ ዜሮ በመጨመር የበለጠ እንዲበዛ አደርገዋለሁ:: ማስታወሻዬን አውጥቼ «ደርሶኛል» ብዬ እጽፋለሁ:: ዜሮ የጨመርኩበትን ሁሉ እመዘግበዋለሁ:: በእያንዳንዱ መጠን ፊትለፊት «አመሰግናለሁ» ብዬ እጽፋለሁ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለደረሰኝም የምስጋና ስሜት አሳድራለሁ። እያንዳንዱ እዳ ካገኘሁት ጋር ሲነፃፀር ትንሽ ነው። በምስጋና እዳዬንም እከፍላለሁ።

ቼ!! ናቸው የሚል ስሜት ሳያድርብኝ እዳዎቼን ከፍቼ እንብቤ አላውቅም። እንዲህ አድርጌ እራሴን ሳላሳምን እዳዎቼን ስከፍት ሆዴ ይናጣል። ይህ የሆድ መናጥ ተጨማሪ እዳ እያመጣብኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ይህን ስሜት ማስወገድና በደስታ ስሜት መተካት እንዳለብኝ አውቃለሁ። እንዲህ ሳደርግ የበለጠ ገንዘብ ማግኘት እችላለሁ። እዳዬን በሚመለከት የፈጠርኩት ጨዋታ እረድቶኛል። ህይወቴን ለውጦልኛል። ልትፈጥረው የምትችለው ብዙ ጨዋታ አለ። የውስጥ ስሜትህን ከግምት በማስገባት የቱ የተዋጣለት እንደሆነ እራስህ ታውቃለህ። ስታምን ውጤቱ ሁሉ በቅጽበት ይመጣል።

## ሎራል ላንግሜይር

*(የገንዘብ ስትራቴጂስት፣ ተናጋሪና የግልና የድርጅት አማካሪ)*

*ያደኩት «ገንዘብ ለማግኘት ጠንክረህ ሥራ» እየተባልኩ ነው። ይህን «ገንዘብ በቀላሉና ወዲያው ወዲያው ይገኛል» በሚል ለወጥኩት። በመጀመሪያ ውሸት ይመስላል። ልክ ነው? « አንተ ውሸታም፣ ይህ ከባድ ነው» የሚል የአይምሮ ክፍል አለ። ስለዚህ ይህ ትንሽ የጠረጴዛ ኳስ ግጥሚያ ለተወሰነ ጊዜ እንደሚቆይ ማወቅ ይኖርብሃል።*

«በርትቼ መስራትና ገንዘብ ለማግኘት መታገል አለብኝ» የሚል አመለካከት ካለህ ይህን ወዲያውኑ አስወግድ። እንዲያ በማሰብ የዛ አይነት ፍሪኩነሲ ሊኖርህ ቻለ። የህይወት ተሞክሮህ ስዕሎችም ሆኑ። የሎራል ላንግማዬርን ምክር ውሰድና ይህን አመለካከትህን «ገንዘብ በቀላሉና ወዲያው ይመጣል» በሚል ተካው።

## ዴቪድ ሺርመር

*ሃብት መፍጠርን በተመለከተ ሃብት የአይምሮ ጣጣ ነው። እንዴት እንደምትመለከተው ነው ነገሩ ሁሉ።*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ሎራል ላንግሚይር*
*ከተራው ህዝብ ጋር ያደረኩትን ምክክር ሣጠነው 80 ከመቶ የሚሆነው ስነልቦናቸውንና አስተሳሰባቸውን የሚመለከት ይመስለኛ ል:: «እ! ማድረግ ትችላለህ:: እኔ አልችልም» ሲሉ ሰዎች አውቃለሁ:: ሰዎች ከገንዘብ ጋር ያላቸውን የውስጥ ግንኙነትና ውይየት የመለወጥ ችሎታ አላቸው::*

> «መልካሙ ነገር የምታውቀው ነገር እንድታምን ከተማርከው የተሻለ መሆኑን የወሰንክ እለት የተትረፈረፈ ሃብት እንዲኖርህ የመጠየቅ ማርሽህን የቀየርክ መሆኑ ነው:: ግብ መምታት የሚመጣው ከውስጥ እንጂ ከውጪ አይደለም»
>
> ራልፍ ዋዶ ኤመርሰን (1803-1880)

የበለጠ ገንዘብ እንዲኖርህ ስለገንዘብ ጥሩ ስሜት ሊኖርህ ይገባል:: በእርግጥ ሰዎች በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው ስለገንዘብ ጥሩ ስሜት አይኖራቸውም:: ነገር ግን እነዚያ አሉታዊ አመለካከቶች ገንዘብ እንዳይቀርብህ ያደርጋሉ:: ያን አዙሪት ማቆም አለብህ:: ማቆም የምትችለው ደግሞ ስለገንዘብ ጥሩ መስማት ሲጀምርህ ነው:: በእጅህ ስለአለው ገንዘብ አመስጋኝ ስትሆን ነው:: «ከሚበቃኝ በላይ አለኝ» ማለት ጀምር:: ስሜቱም ይደርብህ:: «የተትረፈረፈ ገንዘብ አለ:: ወደእኔም እየመጣ ነው:: እኔ የገንዘብ ማግኔት ነኝ:: ገንዘብ እወዳለሁ እርሱም ይወደኛል:: በእየቀኑ ገንዘብ አገኛለሁ:: አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ» በል::

## ገንዘብ ለማግኘት ገንዘብ ሥጥ

የበለጠ ገንዘብ በህይወትህ ለማግኘት መስጠት ሃይለኛ ተግባር ነው:: ምክንያቱም ስትሰጥ «ብዙ አለኝ» ማለትህ ነውና:: በአለም ያሉት ሃብታሞች እጅግ ሩህሩሆች መሆናቸውን ያወቅክ እለት ሊገርምህ ይችላል:: ብዙ ገንዘብ ይሰጣሉ:: በስበት ህግ መሰረት በሰጡ ቁጥር አለም ትከፈትና የገንዘብ ጎርፍ መልሳ ትልክላቸዋለች::

t.me/OLDBOOKSPDF

«የምስጠው ገንዘብ የለኝም» ብለህ እያስብክ ከሆነ መልካም አሁን ለምን በቂ ገንዘብ እንደሌለህ ታውቃለህ:: የምትሰጠው በቂ ገንዘብ የሌለህ ሲመስልህ መስጠት ጀምር:: በመስጠት ላይ ስታምን የስበት ህግ የምትሰጠውን ጨምሮ ይሰጥሃል::

በመስጠትና በመስዋት መካከል ልዩነት አለ:: ከልብ መስጠት ያስደስታል:: መስዋት አያስደስትም:: እጅግ ተቃራኒ ስለሆኑ ሁለቱን አትቀላቅል:: አንዱ የእጥረት ሌላው ደግሞ ከበቂ በላይ የሚሉ አመለካከቶችን የሚረጩ ናቸው:: አንዱ ጥሩ ስሜት አለው ሌላኛው የለውም:: መስዋት ብሎ ብሎ ተቃውሞን ይወልዳል:: ከሙሉ ልብህ መስጠት ልታደርግ ከምትችለው አስደሳች ነገር አንዱ ነው:: የስበት ህግ ያን አመላካች ግጥም አድርጎ ይይዛል:: እጅግ የበዛም ሊጎርፍልህ ይችላል:: ልዩነቱን ለማወቅ ትችላለህ::

### ጀምስ ሬይ

*እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያገኙ ሰዎች አገኛለሁ:: ግንኙነታቸው ግን መልካም ጠረን ይጎድላቸዋል:: ያ ሃብት አይደለም:: ገንዘብን ማሳደድና ሃብታም መሆን ትችላለህ:: ባለፀጋ መሆንን ግን አያስተማምንም:: ገንዘብ የብልፅግና አካል መሆኑን እየካድኩ አይደለም:: ያለ ምንም ጥርጥር ነው:: ነገር ግን አንድ አካል ብቻ ነው:: መንፈሳዊ የሆኑ ብዙ ሰዎችንም አገኛለሁ:: እነዚህ ደግሞ ሁልጊዜ የታመሙና የተሰበሩ ናቸው:: ይህም ብልፅግና አይደለም:: ህይወት በሁሉም መልክ ምልዑ ማለት ነው::*

ባለፀጋ መሆን መንፈሳዊነት ይጎድለዋል እየተባልክ አድገህ ከሆነ ካተራይን ፐንደር የምታዘጋጀውን «የመጽሐፍ ቅዱስ ሚሊየነሮች» የሚለውን ተከታታይ አንብብ:: በነዚህ የተከበሩ ፅሑፎች ውስጥ አብርሃም፣ ኢሣቅ፣ ያቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴና ኢየሱስ የብልፅግና አስተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ እራሳቸው ሚሊኒሮችም ነበሩ:: በአሁኑ አለማችን ያሉ ሚሊኒየሮች ሊገምቱት በማይችሉት ደረጃ የባለፀጋ አኗኗር ስልት ነበራቸው::

t.me/OLDBOOKSPDF

አንተም የግዛቱ ወራሽ ነህ። ማግኘት የተፈጥሮ መብትህ ነው። በብዛት የማግኛው ቁልፍ በእጅህ ነው። ማንኛውንም ጥሩ ነገር ትመኛለህ። አለምም ትሰጥሃለች። ነገር ግን ትይዘው ዘንድ ጥራው። አሁን ምስጢሩን ታውቀዋለህ። ቁልፉ አለህ። ቁልፉ የራስህ አመለካከትና ስሜት ነው። ይህን ቁልፍ ህይወትህን ሙሉ በእጅህ ይዘኸዋል።

## ማርሲ ሺሞፍ

*በምዕራባውያን ወግ ብዙ ሰዎች ግብ የመምታት ፍላጎት አላቸው። ትልቅ ቤት ይፈልጋሉ። ንግዳቸው ውጤታማ እንዲሆን ይሻሉ። ሁሉንም ውጫዊ ነገሮች ይፈልጋሉ። በጥናት ለማረጋገጥ እንደቻልነው እነዚህን ውጫዊ ነገሮች ማግኘት የምንፈልገውን ለማግኘታችን ዋስትና አይሆንም። የምንፈልገው ነገር ደስታ በመሆኑ። እነዚህን ውጫዊ ነገሮች የምንፈልጋቸው ደስታን ያመጡልናል በሚል ነው። ይህም ቢሆን ግን ኋላ ቀር ነው። ውስጣዊ ደስታን መፈለግ ይኖርብሃል። ለሁሉ አስቀድሞ የውስጥ ሰላምና ራዕይ ሊኖርህ ይገባል። ሁሉም ውጫዊ ነገሮች ይህን ተከትለው ብቅ ይላሉ።*

የምትፈልገው ማንኛውም ነገር የውስጥ ሥራ ነው። የውጪው አለም የውጤት አለም ነው። የአመለካከቶች ውጤት ነው። አመለካከቶችህንና ፍሪኩንሲህን በመደሰት ላይ አድርጋቸው። የደስታ ስሜት ይኑርህ። ይህን ስሜት በአመለካከት ደረጃ ወደ ውጪው አለም አስተላልፈው። እውነተኛ ገነት በምድር ታያለህ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ገንዘብን ለመሳብ በሃብት ላይ አተኩር:: በገንዘብ እጥረት ላይ አተኩረህ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት አይቻልም::
- የምትፈልገውን ያህል ገንዘብ አለኝ ብለህ መገመት ጠቃሚ ነው:: ሃብትን የተመለከቱ ጨዋታዎች ተጫወት:: ስለገንዘብ የተሻለ ስሜት ያድርብሃል:: . የገንዘብ አመለካከትህ ሲለወጥ የበለጠ ገንዘብ ይመጣልሃል::
- በአሁኑ ወቅት የደስታ ስሜት ማሳደር ገንዘብ እንዲመጣ የሚያደርግ ፈጣኑ መንገድ ነው::
- «ልገዛው እችላለሁ» የማለት ባህል ይኑርህ:: እናም አመለካከትህን ትለውጥና ስለገንዘብ የተሻለ ስሜት ሲያድርብህ ይጀምራል::
- በህይወትህ ብዙ ገንዘብ ታገኝ ዘንድ ገንዘብ ስጥ:: ቸር ስትሆንና ተካፍሎ መብላት የደስታ ስሜት የሚሰጥህ ከሆነ «ብዙ አለኝ» ትላለህ::
- በመልክት ሣጥንህ ውስጥ ቼኮች እንደምታገኝ ስሜት የሚሰማህ ከሆነ «ብዙ አለኝ » ትላለህ::
- የሃብት አመለካከትህን ሚዛን አጠንክር:: ሃብትን አስብ::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የግንኙነቶች ምስጢር

## ሜሪ ዲያመንድ

(የፊንግ ሹ አማካሪ፣ መምህርና ተናጋሪ)

ምስጢሩ ማለት የአለማችን ፈጣሪዎች እኛው ነን ማለት ነው:: ለመፍጠር የምንፈልገው ማንኛውም ምኞት በህይወታችን ውስጥ ይሆናል:: ስለዚህ ምኞቶቻችን፣ አመለካከቶቻችንና ስሜቶቻችን እጅግ ወሳኝ ናቸው:: ምክንያቱም በእውን ስለሚከሰቱ ነው::

አንድ ቀን ወደ አንድ የስዕል ዳይሬክተር ቤት ሄድኩ:: ይህ ሰው የታወቀ የፊልም ደራሲ ነው:: በቤቱ እያንዳንዱ ጠርዝ ላይ የአንዲት ቆንጆ ሴት ምስል በጨርቅ ተጋርዶ ተቀምጧል:: «አትታየኝም» በሚል አምሳያ ፊቷን ያዞረች ትመስላለች:: «በፍቅር ህይወትህ ውስጥ ችግር ያለብህ ትመስላለህ» አልኩት ዳይሬክተሩን:: «የልብ አዋቂ ነህ እንዴ?» አለኝ:: «አይደለሁም ነገር ግን ተመልከት ያቺ ሴት በሰባት ቦታ ላይ ትገኛለች » አልኩት:: «የዚያ አይነት ሥዕል ስለምወድ ነው እራሴ ነኝ የሳልኩት» አለኝ:: «ይህ የባሰ መጥፎ ነው ምክንያቱም ያን ፈጠራና የመፍጠር ችሎታ ያኖርከው አንተ ነህ» አልኩት::

እፁብ ድንቅ የሆነ ሰው ነው:: የሴት ተዋንያን ከበውታል:: ምክንያቱም ሥራው ያ ነውና የፍቅር ህይወት የለውም:: «ምን ትፈልጋለህ» ብዬ ጠየቅሁት:: በሳምንት ለሶስት ሴቶች ቀጠሮ መስጠት እፈልጋለሁ አለኝ:: «መልካም:: ሣለው:: እራስህን ከሶስት ሴቶች ጋር አድርገህ ሣልና በሳሎንህ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ስቀለው» አልኩት::

ከስድስት ወራት በኋላ አየሁትና ጠየቅሁት:: «የፍቅር ህይወትህ እንዴት ነው?» አልኩት:: «ግሩም ነው:: ሴቶች ይጠሩኛል:: ከኔ ጋር መቀጣጠር ይፈልጋሉ» አለኝ:: «ፍላጎትህ እንዲህ ስለሆነ



t.me/OLDBOOKSPDF

*እሱ ነው» አልኩት:: «ለአመታት ሴት ቀጥሬ አላውቅም አሁን ግን በሳምንት ለስት ሴቶች ቀጠርኩ:: ይፋጁብኝ ጀመር»:: አለኝ:: «መልካም ይሁንልህ» አልኩት:: «አሁን መረጋጋት እፈልጋለሁ:: ማግባት እፈልጋለሁ:: ፍቅር እሻለሁ» አለኝ:: «ደህና በስዕል አሳየው» አልኩት:: እጅግ ቆንጆ የፍቅር ስዕል ሣለ:: ከአመት በኋላ አገባ:: ደስተኛ ነው::*

*ይህ የሆነበት ምክንያት ሌላ ፍላጎቱን አወጣና ነው:: አንድም ነገር ሳይሆን ለአመታት በውስጡ ተመኘ:: ያልሆነበት ምክንያት ምኞቱ ባለመከሰቱ ነው:: ውጫዊው ደረጃው ለምሳሌ ቤቱ ምኞቱን ሁልጊዜ ይፃረረው ነበር:: ስለዚህ ይህ እውቀት ከገባህ ልትጫወትበት ጀምር::*

የሜሪ ዲያመንድ ደንበኛ ታሪክ ፌንግ ሹ የምስጢሩን አስተምህሮ እንዴት ለማሳየት እንደቻለች የሚያሳይ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው:: አመለካከቶቻችንን ስንጠቀምባቸው እንዴት ሃያል ፈጣሪዎች እንደሆኑ ይህ ምሳሌ ያሳያል:: የምንወስደውን ማንኛውንም ተግባር የሚቀድም አመለካከት አለ:: አመለካከቶች የምንናገረውን ቃላት የሚሰማንን ስሜቶችና ተግባሮቻችንን ይሰራሉ:: ተግባር የተለየ አቅም አለው:: ምክንያቱም እንድንተገብር የሚያደርጉን አመለካከቶች ናቸውና::

አመለካከታችንን ላናውቅ እንችላለን:: ነገር ግን ከተግባር በኋላ ምን አይነት አመለካከቶች እንደነበሩን ለመገንዘብ እንችላለን:: የፊልም ደራሲውን ታሪክ ብናይ ውስጣዊ አመለካከቶቹ በሚሰራው ነገሮች ሁሉ ይንፀባረቁ ነበር:: ፊታቸውን ከእርሱ ያዞሩ ብዙ ሴቶችን በስዕል አሳይቷል:: የውስጥ ስሜቶቹ ምን እንደነበሩ ይታይሃል? ምንም እንኳን በቃሉ ብዙ ሴቶችን ለመቅጠር ቢፈልግም ውስጣዊ ስሜቱ ግን ያን በስዕሎቹ ላይ ለማሳየት አልቻለም:: ተግባሮቹን ሆን ብሎ ለመለወጥ መርጦ በሚፈልገው ነገር ላይ እንዲያተኩር ምክንያት ሆነው:: ይህችን ትንሽ ለውጥ በማድረጉ ህይወቱን መሣልና ህያው እንዲሆን አደረገ:: ይህም የሆነው በስበት ህግ አማካይነት ነው::

አንድን ነገር ወደህይወትህ ለማምጣት ተግባርህ ከፍላጎትህ ጋር የማይቃረን መሆኑን አረጋግጥ:: ማይክ ዱሊ ቆንጆ ምሳሌ አለው ይህን

t.me/OLDBOOKSPDF

በተመለከተ:: ይህ ሰው ምስጢሩ በሚለው ሲኒማ ተካትቷል:: የድምፅ ትምህርት ተከታትሏል:: ታሪኩ የህይወት ጓደኛዋን ለማግኘት የፈለገች የአንዲት ሴት ነው:: ሁሉን ጥሩ ነገሮች አድርጋለች:: ባሏ `ምን መምሰል እንዳለበት ቁልጭ አድርጋ አውቃለች:: በአይን-ህሊናዋ አይታዋለች:: ይህ ሁሉ ሆኖ የሰውዬውን ምንም አይነት ምልክት ማየት አልተቻለም::

አንድ ቀን መኪና እያቆመች እያለች የምታደርገው ሁሉ ከምትፈልገው ጋር የሚቃረን መሆኑን አጫረባት:: መኪናዋን ከጋራዥ መሃል ብታቆም ለባሏ መኪና ማቆሚያ ቦታ እንደማይኖር ታያት:: ተግባሮቿ የፈለገችውን እንደምታገኝ እየነገሯት ነበር:: ወዲያውኑ መኪናዋን ወደ ጥግ አድርጋ አቆመች:: ግማሹን ቦታ ላሰበችው ባሏ ተወች:: ወደ መኝታ ክፍሏ ሄዳ የልብስ ሳጥኗን ከፈተች:: ለባሏ ልብስ ማስቀመጫ የሌለ መሆኑን ተገነዘበች:: ልብሶቿን ጥግ አስይዛ ቦታ አመቻቸች:: ትተኛ የነበረውም አልጋውን ሙሉ በሙሉ ሞልታ ነበር:: ጥግ ይዛ መተኛት ጀመረች::

አንድ እራት ላይ ይህች ሴት ታሪኳን ለማይክ ዱሊይ አጫወተችው:: በዛን ወቅት ካጠገባቸው ተቀምጦ የነበረው የምኞት ባሏ ነበር:: እነዚህን ተግባራት ካከናወነችና ሁሉንም ነገር ልክ በእጇ እንደያዘችው አድርጋ ከተንቀሳቀሰች በኋላ የተመኘችው ባል ተገኘ:: በደስታ ተጋብተው እየኖሩ ነው አሁን::

የእህቴ የግሌንዳም ታሪክ ሌላው ምሳሌ ነው:: ግሌንዳ ምስጢሩ የሚለው ሲኒማ የፕሮዳክሽን ማናጀር ናት:: የምትኖረውና የምትሰራው አውስትራሊያ ሲሆን አሜሪካ በሚገኘው ጽ/ቤት ከኔ ጋር ሆና ለመስራት ወደ አሜሪካ ለመሄድ ፈለገች:: ግሌንዳ ምስጢሩን ጠንቅቃ ታውቀው ነበር:: እናም የምትፈልገውን ሁሉ ለማግኘት ትክክል የሆነውን ሁሉ ታደርግ ነበር:: ያም ሆኖ አውስትራሊያ እያለች ወራት አለፉ::

ግሌንዳ የፈለገችውን ለማግኘት በሚያስችላት መልኩ እየሆነች እንዳልሆነ ተረዳች:: እናም ጠንከር ያሉ ተግባራትን መውሰድ ጀመረች:: ለጉዞዋ የሚሆነውን ሁሉ አዘጋጀች:: እባልነቶቿን ሰረዘች:: የማትፈልገውን ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ሰጠች:: ሻንጣዎቿን ጠረዘች:: በአራት ወራት ውስጥ ግሲንዳ ጊሪክ ገባች::

ዲሆንልህ የጠየከተውን ነገር አስብ:: እንቅስቃሴዎችህ ለማግኘት ትመኘውን ነገር የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን አረጋግጥ:: ልክ እያገኘህ ይሆን አድርገህ ተንቀሳቀስ:: ዛሬ ብታገኘው የምትሻውን ፍላጎትህን ፒያንፀባርቁ ተግባራት አድርግ:: ፍላጎቶችን ለማግኘት ክፍል ትርህ:: ይህን ስታደርግ የምኞትህን ሃያል አመላካች ትሰዳለህ::

# ሥራህ አንተ ነህ

## ሊዛ ኒኮልስ

*በግንኙነት ውስጥ ማን መከተት እንዳለበት መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው:: ከሁሉ አስቀድሞ ግን ሸሪካህን ሳይሆን እራስህን እወቅ::*

## ጀምስ ሬይ

*እራስህ ያልወደድከውን ኩባንያ ማን እንዲወድልህ ትፈልጋለህ? እንደገና የስበት ህግ ወይም ምስጢሩ ኩባንያህን የመውደድ ነገር ያመጣልሃል:: ግልፅ መሆን ይኖርብሃል:: «ሰዎች ለአንተ እንደሚያደርጉልህ አንተም ለነሱ ማድረግ ትፈልጋለህ?» ብዬ ልጠይቅህ እወዳለሁ::*

ሰዎች እንዲሆኑልህ በምትፈልገው አይነት ለእራስህ ካልሆንክ ነገሮችን ለመለወጥ አትችልም:: ተግባራቶችህ ጠንካራ አመለካከቶችህ ናቸው:: እናም እራስህን ካልወደድክና ካላከበርክ ዋጋ የሌለህ፣ የማትጠቅምና የማይገባህ የሆንክ አይነት አመላካች ትረጫለህ:: ያ አመላካችም መተላለፉን ይቀጥላልና ብዙ ሰዎች አንተን በበጐ አይን የማያዩበት ሁኔታ ይኖራል:: እንደነዚህ አይነት ሰዎች ውጤት ናቸው:: አመለካከትህ ደግሞ ምክንያት ነው:: እራስህን ውደድና አክብር:: ይህንም ምልክትና ፍሪኩንሲ አስተላልፍ:: የስበት ህግ ስለሚሰራ በሚወዱህና በሚያከብሩህ ሰዎች ትከበባለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙ ሰዎች ለሌሎች ተሰጥተዋል። እንደዚያ የሚያደርጉትም ለሌሎች ጥሩ ነን ብለው በማሰብ ነው። የተሳሳተ ነው። እራስን መስዋት ማድረግ ከፍፁም እጥረት የሚመጣ ነው። «ለሁላችንም የሚሆን ስለሌለ የእኔን ልተውላችሁ» እንደማለት ነው። ይህ አይነት ስሜት ቂይቶ ተቃውሞን ያመጣል። ለሁሉም የተትረፈረፈ ነገር አለና እያንዳንዱ የራሱን ፍላጎት የማሟላት ኃላፊነት አለበት። ለሌላ ሰው ማሟላት አትችልም። ለሌላ ሆነህ ማሰብና ስሜት ማሳደር ስለማትችል ነው። ሥራህ አንተ ነህ።

## ዶር ጆን ግሬይ

*የራስህ መፍትሔ ሁን። ወደ ሌላ ሰው እየመለከትክ «ዛሰለዬ ክሆና የበለጠ ልትሰጠኝ ይገባሃል» አትበል። በግልባጩ ለእራስህ ብዙ ስጥ። ለእራስ ለመስጠት ጊዜ ውሰድ። እራስህን አጥግብና ለሌላ ትረፍ።*

«ለመወደድ እራስህን አጥግብ፤ ማግኔት እስክምትሆን ድረስ»።

ቻርለስ ሃኔል

ብዙዎቻችን እራሳችንን በመጨረሻ እንድናይ ነው የተነገረን ። ስለሆነም ዋጋቢስነትንና የማይገባኝነትን ሰበናል። እነዚህ ስሜቶች ባደሩብን ቁጥር የበለጠ የአልረባምና አይገባኝም ስሜቶች ያድሩብናል። ያን አመለካከት መስጠጥ አለብህ።

«ለአንዳንዶቹ እራስን በጣም መውደድ የማይቻል ይመስላቸዋል። ይህ ጉዳይ አሁንም በተለየ ብርሃን ሊታይ ይችላል። ይህንም የምናደርገው አንደኛነትን መፈለግ ባልተገደበው ከታዘዘ ደግሞ ሁለተኛነትን በመሻት ከዚሁ በቋሚነት ተጠቃሚ ለመሆን ስለምንችል ነው»

ፕሬንቲስ ሙልፎርድ

ራስህን ካላስተደሰትክ ለሌላ የምትሰጠው አታገኝም። ስለዚህ ቀድመህ ወደራስህ ማጋደል ጠቃሚ ነው። የራስህን ደስታ አስቀድመህ አድምጥ። ሰዎች የራሳቸው ደስታ ኃላፊነት አለባቸው። ለራስህ ማጋደል ካትጀምርና የሚያስደስትህን ስታደርግ ሊርቁህ የማትገባ የደስታ ምንጭና

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሀሳባትና አዋቂዎች እንሀባራቱ ምሳሌ ትሆናለህ:: ደስ ባለህ ጊዜ ለለመስጠት እንኳ ምንም አታስብም:: የተፈጥሮ ሂደት ነው::

**ሊዛ ኒኮልስ**

ከብዙ ሰዎች ጋር ግንኙነት የፈጠርኩት ውበቴን ለማሳየት ነው:: ምክንያቱም የራሴ ቁንጅና ለራሴ ስላልታየኝ ነው:: በልጅነቴ ዕኳረዶውቼ የሚገርሙ ሴቶች የቻርለስ መላዕክት ነበሩ:: አስገራሚ ሆነውም እኔን አይመስሉም:: ሊዛን እስካፈቀርኩበት ጊዜ ድረስ የራሴን ቆዳ፣ ከናፍርት፣ አርብና ጥቁር አመልማሎ ሀገር እጠላ ነበር:: ሊዛን ከወደድኩ በኋላ ግን አለም ሁሉ ይወደኝ ጀመረ::

እራስህን የምትወደበት ምክንያት እራስህን ስትወድ ጥሩ ስሜት ሊሰማህ ስለሚችል ነው:: ስለ ራስህ መጥፎ ከተሰማህ አለም ላንተ ያላትን ፍቅርና መልካም ነገር ትገድባለህ::

ስለራስህ ጥሩ ስሜት ከሌለህ ህይወትህን መጠህ አውጥተህ እየደፋህ ነው:: ጥሩ ነገርህ ማለትም ጤናህ፣ ሃብትህና ፍቅርህ ሁሉ በጥሩ ስሜትና ደስታ ፍሪኩንሲ ላይ ነው:: የማያልቅ ሃይልና አስደናቂ የጤናና ሃብት ስሜት ጥሩ የመሰማት ፍሪኩንሲ ናቸው:: ስለራስህ ጥሩ ካልተሰማህ የበለጠ መጥፎ ስሜት እንዲኖርህ የሚያደርጉ ሰዎችን፣ ሁኔታዎችንና ኩነቶችን በሚስብ ፍሪኩንሲ ላይ ትሆናለህ::

አትኩሮትህን ለውጥና ስለራስህ መልካም ነገሮች አስብ:: በውስጥህ ሊኖሩ የሚገባቸውን አውንታዎች ተመልከት:: በነዚህ ላይ ስታተኩር የስበት ህግ ስለራስህ የበለጠ ጥሩ ነገር ያሳይሃል:: የምታስበውን ታገኛ ለህ::

ግድረግ ያለብህ ስለአንተ አንድ ጥቅል አመለካከት እንዲኖርህ ነው:: ስበት ህግ የበለጠ አመለካከት እንዲኖርህ በማድረግ አሀፋውን ሰጥሃል:: ስለራስህ ጥሩ ነገሮችን ተመኝ:: ታገኛለህም::

t.me/OLDBOOKSPDF

## ቦብ ፕሮክቶር

ስለአንተ አንድ ትልቅ ነገር አለ:: ለአርባ አራት አመታት እራሴን አጥንቻለሁ:: አንዳንዴ ራሴን ለመሳም እፈልጋለሁ:: ስለራስ ብስለት እያወራሁ አይደለም:: የማወራው ስለአንተ ያለኝን ጤናማ ክብር በተመለከተ ነው:: እራስህን ስታፈቅር ወዲያው ሌሎችን ታፈቅራለህ::

## ማርሲ ሺሞፍ

ከሰዎች ጋር ግንኙነት ካለን መጣመራችን አይቀርም:: «የስራ ባልደረቦቼ ሰነፎች ናቸው፣ ባለቤቴ ሊያሳብደኝ ነው፣ ልጆቼ አስቸጋሪዎች ናቸው፣ ወዘተ» ይባላል:: በሌሎች ሰዎች ላይ በማተኮር ማለት ነው:: ነገር ግን ግንኙነቶችን የዘዘ ዘንድ ስለሌሎች ከመጥፎ ነገር ይልቅ መልካሙን ብንናገር ይበጃል:: በሌሎች ላይ እየተማረርን ከሆነ የባሰ ነገር ይመጣል እንጂ የተሻለ ነገር አይከተልም::

ምንም እንኳን ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት አስቸጋሪ ነገር ቢገጥምህም ያን አይነት ግንኙነት አሁንም ልታስተካክለው ትችላለህ:: ማስታወሻ አውጣና ለ30 ቀናት ስለዚያ ሰው የምታመሰግነውን ነገር ሁሉ ፃፈው:: ለምን ሰዎቹን እንደምትወዳቸው አውጥተህ አውርድ:: ተጫዋችነታቸውን ታደንቃለህ:: እረዳትነታቸውን ታደንቃለህ:: እንደዚህ መልካም ጎኖቻቸውን ስታጣጥም ከነሱ የምታገኘው የበለጠ የሚጣፍጥ ምግባራትን ይሆናል:: ችግሮችም ቀስ በቀስ ይተናሉ::

## ሊዛ ኒኮልስ

ሰዎች እንዲያስደስቱህ እድል በሰጠህበት አብዛኛው ጊዜ በፈለከው መጠንና መንገድ ማድረግ ያቅታቸዋል:: ለምን? ምክንያቱም ለራስህ እርካታና ደስታ ኃላፊው አንድ ሰው እርሱም አንተ በመሆንህ ነው:: ሌላው ቀርቶ ወላጆችህ፣ ልጅህ፣ ሚስትህ ወዘተ ደስታህን ለመቆጣጠር አይችሉም:: የደስታህ ተካፋይ ብቻ ናቸው:: ደስታህ ከራስህ ጋር ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

ደስታህ ሁሉ በፍቅር ፍራክንሲ ላይ ነው። ይህ ፍሪኩንሲ ፍሪኩንሲዎች ሁሉ የበላይ ነው። ፍቅርን በልብህ እንጂ በእጅህ ማንበልበል አትችልም። ፍቅር የመሆን ጉዳይ ነው። ፍቅርን የምታረጋግጠው በሌሎች ሲገለፅ ነው። ፍቅር ስሜት ነው። ያን የፍቅር ስሜት ማስተላለፍ የምትችለው አንተ ነህ። የፍቅር ማመንጪት አቅምህ ገደብ የለውም። ስታፈቅር ከቀረው አለም ጋር የተሟላ ህብር ይኖርሃል። እስከቻልክ ድረስ ሁሉንም ነገርና ሁሉንም ሰው ውደድ። በምትወደው ላይ አተኩር። ፍቅር ይሰማህ። እናም ፍቅርና ደስታ ሲመላለሱብህ ታያለህ። የስበት ህግ የምትወዳቸው ተጨማሪ ነገሮች ያቀርብልሃል። ይህ ነው ሃቁ።

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ግንኙነት እንዲኖርህ ስትፈልግ አመለካከትህ፣ ቃላቶችህና ተግባርህ ከፍላጎቶችህ ጋር የማይጋጩ መሆናቸውን አረጋግጥ።
- ሥራህ አንተ ነህ። እራስህን ሳታረካ ሌላ የምትሰጠው ምንም ነገር የለም።
- እራስህን ውደድ። አክብር። እናም የሚወዱህና የሚያከብሩህ ሰዎች ታገኛለህ።
- ስለራስህ መጥፎ ከተሰማህ ፍቅርን ትገድባለህ ስለራስህ መጥፎ ስሜት የሚያጭሩ ብዙ ሰዎችና ሁኔታዎች ይመጡብሃል።
- ከራስህ የሚገኙ የምትወዳቸውን ነገሮች አተኩርባቸው። የስበት ህግም ስለአንተ የበለጠ ታላላቅ ነገሮችን ያሳይሃል።
- ግንኙነት እንዲሠራ በሌሎች ሰዎች በምታያቸው የምታደንቃቸው ነገሮች ላይ አትኩሮት አሳድር። ከደካማ ጎናቸው ይልቅ በጥንካሬአቸው ላይ ስታተኩር አንተም ተጨማሪ ሆነው ታገኛቸዋለህ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# የጤና ምስጢር

## ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*(የኳንተም ፊዚክስ ባለሙያና የህዝብ ፖሊሲ ኤክስፐርት)*
*አካላችን የአመለካከታችን ውጤት ነው። አመለካከታችንና ስሜታችን የቱን ያህል የአካላዊ ይዘታችን አወቃቀርና ተግባር እንደሚወስኑት በህክምና ሳይንስ አማካይነት ለመረዳት እየጀመርን ነው።*

## ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ

*ስነ-ልቦናዊ ህክምና (ፕላሴቦ) የሚፈውስ መሆኑን አውቀናል። ፕላሴቦ ልክ እንደስኳር እንክብል በሰውነት ላይ ምንም ተፅዕኖ ውጤት ያለው አይደለም። ለበሽተኛው ፕላሴቦ እንደሌላ ህክምና መሆኑን ንገረው። ይቀበላል። የሰውልጅ አይምሮ ከህክምና የበለጠ የማዳን ሚና ያለው መሆኑ ታውቋል።*

የምስጢሩን መጠን እያወቅክ ስትመጣ በሰው ልጅ ህይወት ሥር ጤናንም ጨምሮ የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ በጉልህ ለማየት ትችላለህ። የፕላሴቦ ውጤት ዋናው ክስተት ነው። ህመምተኛው የተሰጠውን ኪኒን ሲያምነውና ያድነኛል ብሎ ሲያስብ ያመነበትን ያገኛል። ይፈወሳል።

## ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ

*አንድ ሰው ታምሞና የህመሙን ምክንያት በአይምሮው ውስጥ እያፈላለገ መድሃኒት ልጠቀም አልጠቀም እያለ ከሆነና ህመሙም አጣዳፊ ከሆነበት መድሃኒት መውሰድ አዋቂነት ይሆናል። እያንዳንዱ ማዳን ቦታ አለው።*

በአይምሮ አማካይነት መፈወስ በመድሃኒት ከማዳን ጋር ህብር ሊኖረው ይችላል። ህመም ካለ ህመሙን በመድሃኒት ማስታገስ ይቻላል። ህመሙ ሲታገስ ሰውየው በጤና ላይ ለማተኮር ይችላል። የተሟላ ጤንነትን ማሰብ ማንም ሰው በግሉና በውስጡ ሊያደርገው የሚችል ነገር ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሊዛ ኒኮልስ

አለም የመትረፍረፍ ዋና ክፍል ናት:: ይህ መትረፍረፍ ይሰማህ ዘንድ እራስህን ስታዘጋጅ መደነቅ፣ ደስታ፣ ፍሰሃና አለም ያዘጋጀችልህ ትልቅ ነገር ሁሉ ማለትም ጤና፣ ሃብትና ጥሩ ተፈጥሮ ይገኝልሃል:: ነገር ግን በአሉታዊ አስተሳሰብ ከተሞላህ አለመመቸት ይሰማሃል:: ህመም ይሰማሃል:: እያንዳንዱን ቀን በሰላም ለማሳለፍ ይከብድሃል::

## ዶ/ር ቤን ጆንሰን

(ሃኪም፣ ደራሲና የህክምና ቡድን መሪ)
በሺህ የሚቆጠሩ ምርመራዎችና በሽታዎች አሉ:: ደካማ ነገሮች ናቸው:: የአንድ ነገር ውጤቶች ናቸው:: የጭንቀት:: በሰንሰለቱ ላይ በቂ ጫና ብታደርግና በስርአቱም ላይ ብታደርግ አንዱ አገናኝ ይበጠሣል::

ጭንቀት የሚጀምረው በአንድ አሉታዊ አስተሳሰብ ነው:: አንድ አስተሳሰብ ሳይገደብ ከቀጠለ ሌላ እየወለደ ጭንቀት እስኪፈጠር ድርስ ይቀጥላል:: የጭንቀት ምክንያት አሉታዊ አስተሳሰብ ነው:: ምንም ይሁን አንድን መልካም አመለካከት በሌላ እያዳበርክ የጭንቀት ምክንያት የሆነውን አሉታዊ አስተሳሰብ መለወጥ ትችላለህ::

## ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ

አካላዊ ቅንብራችን መረጃ ሲሰጠን ስለሚፈልግ ህመምን ይፈጥራል:: ሲያመን የተዛባ አመለካከት እንዳለን ወይም እንደማንወድና ምስጋና-ቢስ እንደሆን ያሳውቀናል:: የአካል ምልክቶችና ጠቋሚዎች አስቸጋሪ አይደሉም::

ዶ/ር ዲማርቲኒ ፍቅርና አመስጋኝነት የህይወታችንን አሉታዊነት ሁሉ ያስወግዳል ይሉናል:: ፍቅርና ምስጋና ባህርን ይሰነጥቃሉ፣ ተራራ ይገፋሉ፣ ታምራትን ይፈጥራሉ:: ፍቅርና ምስጋና ምንም አይነት በሽታን ያስወግዳሉ::

t.me/OLDBOOKSPDF

**ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ**

*በተደጋጋሚ የሚነሳው ጥያቄ «አንድ ሰው በአካሉ ላይ የሆነ በሽታ ወይም የህይወት አለመመቻቸት ሲያጋጥመው በተስተካከለ አመለካከት ሊያስወግደው ይችላል ወይ? የሚለው ነው:: መልሱም ያለጥርጥር «አዎ»» ነው::*

# መሳቅ/ሣቅ የተዋጣለት መድሃኒት ነው

**ካቲ ጉድማን፣ (የግል ታሪክ)፣**

*የጡት ካንሰር አለብሽ ተባልኩ:: ከልቤ በእውነትና በጠንካራ እምነት ድኛለሁ ብዬ አመንኩ:: በየቀኑ «በዙ ምስጋና ይድረስህ ድኛለሁ» እላለሁ:: እንዲያ እያልኩ ብዙ ጊዜ አለፈ:: መዳኔን ከልቤ አመንኩት:: ካንሠር በአካሉ ውስጥ እንደሌለ ሆኜ ተሰማኝ:: እራሴን ለማዳን ካደረኳቸው ነገሮች መካከል አንዱ የሚያስቁ ፊልሞች ማየት ነበር:: ማድረግ የነበረብኝ መሳቅ፣ መሳቅ እንደገና መሳቅ ነው:: መጨነቅ አልነበረብኝም:: ምክንያቱም ለመዳን በምንቀሳቀስበት ወቅት ይህ የሚያባብሰው እንደኛው መጥፎ ነገር ጭንቀት መሆኑን እናውቅ ነበርና ነው:: ካንሰር አለብሽ ከተባልኩበት እስከዳንኩበት ጊዜ ድረስ በግምት ሶስት ወራት ይሆን ነበር:: ያም ያለምንም የጨረር ወይም ኬሚካል ህክምና ነበር::*

ይህ ቆንጆና አነቃቂ የካቲ ጉድማን ታሪክ ሶስት ታላላቅ ኃይሎች በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጥልናል:: እነርሱም የመፈወስ ምስጋና ኃይል፣ የማግኘት እምነት ኃይልና በሰውነታችን የህመም ማስወገጃ ሣቅ ኃይል ናቸው::

ካቲ ሣቅን በህክምናው ውስጥ ያካተተችው የኖርማን ኩዚንስ ታሪክን ከሰማች በኋላ ነው:: ኖርማን የማይድን ህመም አለብህ ተብሎ በህይወት የሚኖረው ለጥቂት ወራት ብቻ መሆኑን ዶክተር ነግሮታል:: ኖርማን ራሱን ለማዳን ወሰነ:: ለሶስት ወራት አስቂኝ ሲኒማዎችን አየ:: በተጨማሪም ያለማቋረጥ ሣቀ:: በነዚህ ሶስት ወራት ውስጥ በሽታው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሰውነቱ ለቆ ወጣ። የኖርማንን መዳን ዶክተሮቹ ታምር መሆኑን አመኑ። በሣቁ ቁጥር ኖርማን እሉታዊነትን ሁሉ ያስወግድ ነበር። ከዚሁ ጋር ህመሙንም አስወገደ። ሣቅ እውነትም አምሳያ የሌለው መድሃኒት ነው።

## ዶ/ር ቤን ጆንሰን

*ሁላችንም የምንመጣው ከሆነ እቅድ ጋር ነው። ይህም ፕሮግራም «እራስን ማከም» ተብሎ የጠራል። ቁስል ይይዝሃል። ማሻረየው አብሮ ነው ያለው። ባክቴሪያ ይገባብሃል የሰውነትህ የህመም መቆጣጠሪያ ሥርአት ባክቴርያውን ይዋጋና ትድናለህ።*

## ቦብ ፕሮክቶር

*ህመም ጤናማ ስሜት ባለው አካል ውስጥ አይኖርም። ሰውነትህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዋሳትን በየቀኑ ይበትናል። ይህኑ ያህል ህዋሳትንም በዛው ጊዜ ውስጥ እንደ አዲስ ይፈጥራል።*

## ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*ለነገሩ የሰውነታችን ክፍሎች በየቀኑ ይተካሉ። አንዳንድ የአካላት ክፍሎች ለመተካት ወራት ይፈጃሉ። አንዳንዶቹም አመታትን ያስቆጥራሉ። ነገር ግን በእያንዳንዱ አዲስ አመት ሁላችንም አዳዲስ ቅርፃዊ አካል ይኖረናል።*

ሰውነታችን በየአመቱ የሚታደስ ከሆነ ህመም ለምንድን ነው በሰውነታችን ውስጥ ለአመታት የሚኖረው? ሊኖር የሚችለው በአመለካከት ብቻ በሽታውን በማዳመጥና ለበሽታው ትኩረት በመስጠት መሆን አለበት።

t.me/OLDBOOKSPDF

# የፍፁምነት አመለካከት ይኑርህ

የፍፁምነት አመለካከት ይኑርህ:: ህብራዊ አመለካከት ባለበት ሰውነት ውስጥ ህመም አይኖርም:: ፍፁምነት ብቻ መኖሩን እወቅ:: ትክክለኛነትን ባዳመጥክ ቁጥር ወደአንተ እንዲቀርብ ታደርገዋለህ:: ያልተስተካከለ አመለካከት የሰው ልጅ ህመም ሁሉ መንስኤ ነው:: የበሽታ፣ የድህነትና ያለመደሰትም ምክንያት ነው:: አሉታዊ አመለካከቶችን ስናወጣና ስናወርድ ከሚገባን ውርስ እራሳችንን መገንጠላችን ነው:: «የማወጣ የማወርደው የተስተካከለ አመለካከትን ነው:: የሚታየኝ ትክክለኛነት ነው:: እኔ ትክክል ነኝ» ብለህ አሳውቅ:: ለመሆን ተመኝ:: እያንዳንዷን ቅንጣት ግግም ማለትና ቅልጥፍና ማጣት ከሰውነቴ አስወግጃለሁ:: ሰውነቴን እንደ ህግን አካል ቀልጣፋ አድርጌ በማየት ላይ አተኩሬአለሁ:: እናም እያንዳንዱ ገራራና ታማሚ መገጣጠሚያ ሁሉ ተወግዷል:: በአንድ ሌሊት ነው ይህ ሁሉ የሆነው::

ማርጀት በአይምሯችን ሁል ጊዜ እንዳለ እናያለን:: በእያንዳንዱ አጭር ጊዜ ውስጥ አዲስ ሰውነት እንዳለን ሳይገለ ያስተምራል:: ማርጀት የተገደበ አስተሳሰብ ነው:: እንዲህ አይነቱን አመለካከት ከንቃተ-ህሊናህ አውጥተህ በመጣል የፈለገውን ያህል የትውልድ ዘመን በአይምሮህ የታጨቀ ቢሆንም አካልህ ገና ወራት ብቻ የሞላው ህፃን መሆኑን እወቅ:: ቀጣዩን ልደትህን ልክ የመጀመሪያው ልደትህ እንደሆነ አድርገህ አክብረው:: የልደት ኬክህን በስድሳ ሻማዎች አትክበበው እርጅናን መጥራት ካላስፈለገህ በስተቀር::

የተሟላ ጤንነትን፣ አካልን፣ የተስተካከለ ክብደትንና ማቆሚያ የሌለው ወጣትነትን አስብ:: በማያቋርጥ የትክክለኛነት አስተሳሰብ ሁሉንም እውን ታደርጋቸዋለህ::

**ቦብ ፕሮክቶር**

*ህመም ካለብህ ካተኮርክበትና ስለሱም ለሰዎች የምታወራ ከሆነ ተጨማሪ የህመም ህዋሳትን ትጋብዛለህ:: በተሟላ ጤና ላይ እንኳ ለሁ ብለህ አስብ:: ህመምን ዶክተሩ ይከታተለው::*

t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሲያማቸው የሚያደርጉት ስለህመማቸው ማውራት ነው:: ይህም የሚሆነው ሁልጊዜ ስለህመሙ ስለሚያስቡ ነው:: አስተሳሰባቸውን ወደቃልነት ይለውጡታል:: ትንሽ ደህንነት ካልተሰማህ አታውራ:: አመለካከትህ ለዚህ ህመም ምክንያት እንደሆነ እወቅ:: እስኪቻልህ ድረስ «በግሩም ሁኔታ ላይ ነኝ» በል:: «ጥሩ ስሜት አለኝ» በል :: እንደዚያም ይሰማህ:: የሆነ ሰው «እንዴት ነህ? ምን ይሰማሃል? » ቢልህ ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ በማስታወስ ልታመሰግነው ይገባሃል:: ስትመልስለትም የምትፈልገውን ነገር ብቻ ተናገር::

አችላለሁ ብለህ ካላሰብክ በስተቀር ምንም ነገር መያዝ አትችልም:: እችላለሁ ብሎ ማሰብ በአመለካከትህ እንዲሆን መጋበዝ ነው:: ሰዎች ስለህመማቸው ሲያወሩ የምታዳምጥ ከሆነ ለራስህ እየጋበዝክ መሆኑን እወቅ:: ስታዳምጥ አስተሳሰብህና አትኩሮትህ በህመም ላይ ይሆናል::አመለካከትህን ሁሉ በአንድ ነገር ላይ ስታደርግ ደግሞ ይሁንልኝ ብለህ እየጠየቅክ ነው:: ስለዚህ ስለህመም የሚያወራልህን ሰው ወደ ሌላ ነገር መልሰው::

## ሊዛ ኒኮልስ

*ሁለት የሆነ ችግር የገጠማቸው ሰዎች አሉህ እንበል:: ነገር ግን አንደኛው በደስታ ላይ ማተኮር መርጧል:: ለምን ቢባል ደስተኛና አመስጋኝ እንደሆነ በማተኮር ተስፋ ሳይቆርጥና ይሆናል በማለት ለመኖር ፈልጓል:: ሁለተኛው ሰውም አለ:: ነገር ግን ምንም እንኳን ችግሩ ከአንደኛው ሰው ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም የዚህኛው ምርጫ በበሽታው፣ በህመሙና በሃዘን መኖር ሆነ::*

## ቦብ ዶይል

*ሰዎች በችግራቸውና በምልክቶቹ ላይ ሲያተኩሩ ማቆም ያቅታቸዋል:: ከመታመም ወደ ጤናማነት ካልተመለሱ በስተቀር አይድኑም:: ምክንያቱም የስበት ህግ እንደዚያ ስለሆነ ነው::*

t.me/OLDBOOKSPDF

«እስከቻልን ድረስ እያንዳንዱ የሚያስጠላ አስተሳሰብ በሰውነት ውስጥ የተቀመጠ መጥፎ ነገር መሆኑን እናስታውስ»

ፐሬንቲስ ሙልፎርድ

## ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*የደስታ አመለካከቶች ወደ ደስተኛ ስነ-ህይወት ይመራሉ:: ደስተኛ አካል ጤነኛ ነው:: አሉታዊ አስተሳሰብና ጭንቀት እንዴት አድርገው ሰውነትንና ተግባሩን እንደሚያዳክሙት ተመልክቷል:: ምክንያቱም ሰውነታችንን ያለማቋረጥ የሚገጣጥሙት፣ እነደገና የሚያሞቅሩትና የሚጠፍሩት አመለካከቶቻችንና ስሜቶቻችን ናቸውና::*

አካልህን በሚመለከት ምንም ይከሰት መለወጥ ትችላለህ:: አስደሳች አመለካከቶችን አስብ:: ደስተኛ መሆን ጀምር:: ደስታ የመሆን ሁኔታ ነው:: እጣትህ ደስታ መሰማት በሚለው ቁልፍ ላይ ነው:: ቁልፉን ተጫነው:: አጥብቀህ እንደተጫንከው ቀጥል::

## ዶ/ር ቤን ጆንሰን

*አካላዊ ጭንቀትን ከሰውነትህ አርቅ:: ሰውነትህም እንዲያደርግ የተመደበውን ሁሉ ያደርጋል:: እራሱን የፈውሳል:: በሽታን ለማስወገድ መታገል የለብህም:: አሉታዊ አመለካከትን ማስወገድ የተፈጥሮ ጤንነትህን ከውስጥህ ለመመለስ ይበቃል:: እናም ሰውነትህ ራሱን ያድናል::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ኩላሊቶች እንደገና ሥራቸውን መሥራት ሲጀምሩ አይቻለሁ:: ካንሠር ሟምቶ አይቻለሁ:: የማየት አቅም ሲሻሻልና ተመልሶ ሲመጣ አይቻለሁ::*

ስለምስጢሩ ከማወቄ በፊት የማንበቢያ መነፅር እጠቀም ነበር:: አንድ ምሽት የምስጢሩን እውቀት በየዘመኑ ስመረምር የማነበውን ለማየት መነፅሮቼን አገኘሁ:: ቆም አልኩ:: ያደረኩት ነገር ተሰማኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

አርጅና የአይንን የማየት አቅም እንደሚቀንስ ከህብረተሰቡ ሰምቻለሁ:: ሰዎች ለማንበብ እጃቸውን ሲወጥሩ አይቻለሁ:: የአይን የማየት ችሎታ እድሜ ሲገፋ እንደሚደክም አምኛለሁ:: እንዲህ በማለቴም ደርሶብኛል:: ሆን ብዬ ሳላደረኩትም እንኳ እንዲደርስብኝ አድርጊአለሁ:: በአመለካከቴ የመጣሁት መሆኑን ስላወቅሁ የሃያ አንድ አመት ልጅ እያለሁ አይ እንደነበረው እያየሁ ታየኝ:: በጨለመ ምግብ ቤት ውስጥ፣ ከአውሮፕላን ውስጥና በኮምፒዩተሬ ያለችግር እየገፍኩ እራሴን ተመለከትኩ:: «ቁልጭ አድርጌ አያለሁ» እያልኩ ደጋግሜ ተናገርኩ:: የምስጋናና የደስታ ስሜት አደረብኝ:: በሶስት ቀናት አይኖቼ ዳኑ:: መነፅር አልጠቀምም:: ቁልጭ አድርጌ አያለሁ::

የምስጢሩ ሲኒማ አንደኛው ተዋንያን ለሆነው ለዶ/ር ቤን ጆንሰን ስላደረኩት ነገር ነገርኩት:: «አይኖችህ በሶስት ቀናት እንደዚያ እንዲሆኑ ምን መሆን እንዳለበት አውቀሃል? » አለኝ:: እኔም «አላውቅም:: አለማወቄንም አመሰግናለሁ:: ያ አስተሳሰብ በራሴ ውስጥ አልነበረም:: እንደማደርገው አውቅ ነበር ፈጥኜ እንደማደርገው::» አልኩት::

ዶ/ር ጆንሰን የማይድን በሽታን ከራሱ ሰውነት አስወግዷል:: ከእርሱው አስደናቂ ታሪክ ጋር ሲወዳደር የእኔ አይን ታሪክ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: እኔ ይሻለኛል ብዬ የጠበኩት በአንድ ቀን ውስጥ ነበረ:: ሶስት ቀን መፍጀቱ ብዙም አላስደነቀኝም:: ጊዜና መጠን የሌሉ መሆናቸውን አስታውስ:: ቡግርን ማዳን ሌላ በሽታን ከማዳን አይለይም:: ሂደቱ አንድ አይነት ነው:: ልዩነቱ የአይምሮ ነው:: ስለዚህ የሆነ ህመም እንዲይገዝህ አድርገህ ከሆነ በአይምሮህ የቡግር ያህል አድርገህ አሳንሳት:: አሉታዊ አመለካከቶችን ሁሉ አርቅና ስለጤናህ መስተካከል አተኩር::

## የማይድን ምንም ነገር የለም

**ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ**

*የማይድን ማለት በውስጥ የሚድን ማለት ነው እላለሁ ሁልጊዜ::*

t.me/OLDBOOKSPDF

የማይድን የሚባል ነገር እንደሌለ አምኛለሁ:: አውቃለሁ:: በሆነ ጊዜ አይድንም የተባለ ህመም ድኗል:: በአይምሮዬና በምፈጥረው አለም ውስጥ «አይድንም» አይኖርም:: በዚህ አለም የተትረፈረፉ ነፍሎች አሉ:: ናና ተቀላቀል:: ቃምራት የቀን ተቀን ክንዶች የሆኑባት አለም ናት:: መትረፍረፍ የገነፈሰባት አለም ናት:: ገነት የምትመስል አለም ናት:: አትመስልም?

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ህይወትህን መለወጥና እራስህን ማዳን ትችላለህ::*

## ሞሪስ ጉዳማን

(ደራሲና አለም አቀፍ ተናጋሪ)

*ታሪኬ የሚጀምረው ከማርች 10 ቀን 1981 ነው:: ይህ ቀን መላ ህይወቴን ለወጠልኝ:: የማልረሳው ቀን ነው:: አውሮፕላን ተጋጭቶ ሙሉ በሙሉ ሽባ ሆኜ ሆስፒታል ገባሁ:: የጀርባ አጥንቴ ደቋል:: የመጀመሪያና ሁለተኛ የጀርባ አጥንቶቼ ተሰብረዋል:: መብላትና መጠጣት አልችልም::*

*ዋናው ነገር አስተሳሰቤ ተለወጠ:: ጤነኛ ሰው ሆኜ ሥዕሉ ታየኝ:: ከዛ ሆስፒታልም ወጥቼ ታየኝ:: ሆስፒታል ውስጥ እያለሁ አብሬው እሰራ የነበረው አይምሮዬ ብቻ ነው:: አይምሮው ካለህ ደግሞ ነገሮችን እንደገና ባንድ ላይ ማድረግ ትችላለህ::*

*የመተንፈሻ አካሌ ስለተጐዳ የምተነፍሰው በመሳሪያ ነበር:: ነገር ግን «በሃይል ተንፍስ» የሚል ድምፅ ተሰማኝ:: ከምፈልገው የጤና ስሜት የሚከለክለኝ ነገር በአይምሮዬ ሊመጣ አልቻለም::*

*የልደት እለት ከሆስፒታል እንደምወጣ ግብ አደረኩ:: አደረኩትም:: በሁለት እግሮቼ ተራመድኩ:: ይሆናል ያለ የለም:: ያን ቀን አልረሳውም::*

ሞሪስ ጉድማን የታምር ሰው ተብሎ ይታወቃል፡፡ የእርሱ ታሪክ ለምስጢሩ የተመረጠበት ምክንያት የሰው ልጅን አይምሮ የማያልቅና ያልተገደበ አቅም የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡ ሞሪስ የፈለገውን ለማግኘት የሚረዳውን አስተሳሰብ ያውቀው ነበር፡፡ የሞሪስ ጉድማን ታሪክ ብዙ ሰዎች ወደ ጤናቸው እንዲመለሱ የሚረዳ አስተሳሰብ ግምትና ስሜት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ የህይወቱን እጅግ ግዙፍ ፈተና ወደ እጅግ ግዙፍ ስጦታነት ለውጦታል፡፡

ምስጢሩ የሚለው ፊልም መታየት ከጀመረ ወዲህ ሰዎች ፊልሙን ማየት ከጀመሩ ጀምሮ ከተለየዩ ህመሞች የተፈወሱ ስለመሆኑ ታምራዊ ታሪኮች ደርሰውናል፡፡ ካመንክ ሁሉም ነገር ይቻላል፡፡

የጤናን ርዕስ በሚመለከት ዶ/ር ቤን ጆንሰን ካለው ጋር ልተውህ፡፡ «የኤነርጂ ህክምና ላይ እየደረስን ነው፡፡ የአለም ማንኛውም ነገር ፍሪኩንሲ አለው፡፡ ማድረግ ያለብህ ፍሪኩንሲህን ለውጥ ወይም ተቃራኒ ፍሪኩንሲ ይኑርህ፡፡ በአለም ማንኛውንም ነገር ለመለወጥ ያን ያህል ቀላል ነው፡፡ ይህ ግዙፍ ነገር ነው፡፡ እስከአሁን ያላጋጠመን እጅግ ትልቁ ነገር ይህ ነው» ብሏል ዶ/ር ቤን ጆንሰን፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- የጥላሴብ ውጤት የስበት ህግ የተተገበረ ምሳሌ ነው፡፡ ህመምተኛው የተሰጠኝ ኪኒን ያድነኛል ብሎ ካመነ ያድናል፡፡
- የተሟላ ጤንነት ላይ ማተኮር ሁሉላችንም ለማድረግ የምንችለው ነገር ነው፡፡
- ሣቅ ደስታን ይሰጣል፡፡ አሉታዊነትን ያስወግዳል፡፡ ወደሚያስደንቅ ፈውስ ይመራል፡፡
- ህመም ከሰውነት ውስጥ የሚኖረው በአመለካከት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ህመምን በማዳመጥና በእሱው ላይ በማተኮር ነው፡፡ ትንሽ ደህና ያለመሆን ስሜት ከተሰማህ አታውራ፡፡ ሰዎች ስለህመማቸው ሲያወሩ ካዳመጥክ ህመማቸውን ታበረታባቸዋለህ፡፡ ይልቅስ ወሬህን በመልካም ነገር ላይ አድርግ፡፡ እነዚያ ሰዎች ጤነኞች መስለው ይታዩህ፡፡
- የማርጀት እምነት በአይምሮአችን ውስጥ ነው ያለው፡፡ እናም ይህን አመለካከት ከንቃተ ህሊናህ አውጣና ጣል፡፡ በጤናና በላለማዊ ወጣትነት ላይ አተኩር፡፡
- ህብረተሰብ ስለህመምና እርጅና የሚያወራውን አትስማ፡፡ የዚህ ዓይነት አሉታዊ መልዕክት ምንም አያደርግልህም፡፡

## ሊሳ ኒኮልስ

ሰዎች የሚፈልጓቸውን ነገሮች ተመልክተው «እሺ ይሁን፣ ያን አፈልገዋለሁ» የማለት አዝማሚያ አላቸው፡፡ ነገር ግን የማይፈልጓቸውን ነገሮች ነው የሚመለከቱት፡፡ በህብረተሰባችን ውስጥ ከቁሳቁሶች ጋር በመታገል እንደሰታለን፡፡ ከካንሰር ጋር ውጊያ፣ ከድህነት ጋር ውጊያ፣ ከጦርነት ጋር ውጊያ፣ ከአደንዛዥ ዕፅ ጋር ውጊያ ፣ ከአሸባሪ ጋር ውጊያ፣ ከአመፅ ጋር ውጊያ ነው ሥራችን፡፡ ከማንፈልገው ነገር ጋር የመዋጋት አዝማሚያ አናሳያለን፡፡ ይህ ደግሞ ውጊያን ያበዛብናል፡፡

## ሃል ድወስኪን

(አስተማሪና የሲዲና ዲቪዲ ደራሲ)

የምናተኩርበትን ነገር ሁሉ እንፈጥረዋለን፡፡ እየተካሄደ ባለ ጦርነት ላይ ለምሳሌ ብንናደድ ኃይላችንን ወደ ጦርነቱ መጨመራችን ነው፡፡ እራሳችንን ወደ ጦርነቱ እያስገባን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግብግብን ነው የሚፈጥረው፡፡

«ግብግብ የገጠምነው ነገር ቀጣይ ነው»

ካርል ዩንግ (1875 - 1961)

## ቦብ ዶይል

ግብግብ የገጠምከው ነገር ቀጣይነት የሚሆነው ምክንያቱ «እምቢ፣ ይህን ነገር አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም ይህን ዓይነት ስሜት ያሳድርብኛልና» ብለህ ግብግብ ስለገጠምክ ነው፡፡ «ይህን ስሜት በእውነት አልፈልገውም» የሚል ጠንካራ ስሜታዊነትን ታዳብራለህ፡፡ እንዲህ ያልከው ስሜት እየጋለበ ይመጣልሃል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ግብግብ መግጠም የተስተሳሰፉ ስዕሎችን ስመስወጥ እንደ መሞከር ያስ ነው:: ከንቱ አካሄድ ነው:: በውስጥ ተጓዝና በአስተሳሰብህ አዲስ አመለካች ፈጭተህ አዲስ ስዕሎችን ፍጠር::

የሆነውን ነገር አልቀበልም ስትል የማትወዳቸውን ስዕሎች እያበረታታህ መሆኑ ነው:: እንደዚህ ባደረክ ቁጥር የስበት ህግ እንደሚያስረዳው ሁኔታው እጅግ ይገዝፋል::

## ጃክ ካንፊልድ

*ፀረ-ጦርነት ንቅናቄ ተጨማሪ ጦርነትን ይፈጥራል:: ፀረ አደንዛዥ ዕፅ መሆን አደንዛዥ እፅን ይጨምራል:: ምክንያቱም አተኩረን ያለነው በማንፈልገው ነገር በጦርነት በአደንዛዥ እፅ ላይ ነውና::*

## ሊዛ ኒኮልስ

*አንድን ነገር ለማጥፋት ከፈለግን በዛ ነገር ላይ አተኩር ብለው ሰዎች ያምናሉ:: በመተማመን፣ በፍቅር፣ በፀጋ፣ በትምህርት ወይም በሰላም ላይ ማተኮር በችግር ላይ አቅምን ሁሉ ከማዋል የተለየና ተቃራኒ ነው::*

## ጃክ ካንፊልድ

*ማዘር ቴሬሳ አስተዋይ ነበሩ:: «ጦርነትን በሚያወግዝ ሰልፍ ላይ አልካፈልም:: ስላምን የተመለከተ ሰልፍ ስታደርጉ ጋብዙኝ» ብለዋል:: ምስጢሩ ገብቷቸዋል:: አውቀውታልም:: ተመልከት በአለም ላይ ምን እንዳስከተሉ::*

## ሃል ደዎስኪን

*ፀረ ጦርነት ከሆንክ ሰላምን ደጋፊ ሁን:: ይልቅየው ርሃብን ተቃዋሚ ከሆንክ በቂ ምግብ ያላቸውን ደግፍ:: አንድን ፖለቲከኛ ተቃዋሚ ከሆንክ የሱን ተቃዋሚዎች ደግፍ:: አብዛኛውን ጊዜ ህዝብ የማይወደው ነው የሚመረጠው ምክንያቱም ሙሉ አቅምና አትኩሮት ስለሚያገኝ ነው::*

t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህ ዓለም መጀመሪያው አንድ አስተሳሰብ ነው። ታላላቅ ነገሮች የበለጠ ይተልቃሉ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ያስቧቸዋልና። አስተሳሰባችን እነዚህን ነገሮች ከአናኗራችን ሳይለዩ ይይዛቸዋል። አይምሯችንን ከነዚህ ነገሮች ላይ ብናነሳ ከፍቅር ላይ ብናተኩር አይኖሩም። ይተኑና ይጠፋሉ።

«አስታውስ። ይህ መገንዘብ ያለብህ እጅግ አስቸጋሪና አስገራሚ አረፍተ ነገር ነው። የቱን ያህል አስቸጋሪ ይሁን፣ የትም ይገኝ፣ የተጐዳው ማንም ይሁን ሌላ ማንም የለም አንተ ነህ እራስህን ማየት ስለምትፈልገው ነገር ማሳመን ያለብህ»

ቻርለስ ሃብ

ጃክ ካንፊልድ

የማትፈልገውን ማወቅ ትክክል ነው። ምክንያቱም «ይህ የማትፈልገውን ነው» የሚል ማነፃፀሪያ ይሆንሃልና። ነገር ግን ሃቁ የማልፈልገው ነው» የሚል ማነፃፀሪያ ይሆንሃልና። ነገር ግን ሃቁ ስለማትፈልገው የበለጠ ስታወራ ወይም ስለመጥፎነቱ ስትናገር ሁልጊዜ ስለዛ ስታነብ ተበራክቶ ይመጣብሃል።

በአሉታዊ ነገሮች በመጠመድ አለምን አታግዛትም። በአውንታዊ ነገሮች ስትጠመድ ታበራክታቸዋለህ ብቻ አይደለም ወደራስህም ታግተለትላቸዋለህ።

የምትፈልገው ስዕል ሲታይ አመላካቹን መቀየርና አዲስ መፍጠር ይናርብኃል። አለማዊ ሁኔታ ቢሆንም አቅም አለህ። ሁሉም ሰው ተደስቶ ይታይህ። ምግብ ተትረፍርፎ ይታይህ። ለምትፈልገው ነገር አመለካከትህን አትንፈግ። የፈለገው ነገር በአካባቢህ እየሆነም የፍቅርና የደህንነት ስሜት ሲኖርህ የሚያስችል አቅም አለህ።

t.me/OLDBOOKSPDF

**ጀምስ ሬይ**
*«ደህና! ጀምስ፣ ሊነገረኝ ይገባል» ይላሉ ሰዎች ብዙ ጊዜ:: መረጃው ሊደርስህ ይገባ ይሆናል:: መጨነቅ ግን የለብህም::*

ሚስጥሩን እንዳወቅሁ ከዚህ በኋላ ዜና አላይም፣ አላነብም ብዬ ወሰንኩ:: ምክንያቱም ስለሚያበሳጩኝ ነው:: መጥፎ ዜና በማሰራጨታቸው የዜና አገልግሎቶችና ጋዜጦች አይወቀሱም:: የአንዲት ዓለም ነዋሪዎች እንደመሆናችን የሁላችንም ኃላፊነት ነው:: ርዕሱ ከባድ ድራማ ሲሆን ብዙ ጋዜጦች እንገዛለን:: አለም አቀፍ ወይም ብሔራዊ ውድመትን ከተናገሩ የዜና አውታሮች ትችት ሰማይ ይነካል:: ስለዚህ የዜና አገልግሎቶችና ጋዜጦች ብዙ መጥፎ ወሬ ያወሩልናል:: ምክንያቱም እንደህብረተሰብ እንፈልገዋለን የምንለው ዜና ያን አይነቱን ነውና:: ሚዲያው ውጤት እኛ ደግሞ ምክንያት ነን:: የስበት ህግ በተግባር ላይ ሆኖ ማለት ነው::

አዲስ አመላካች ሲኖረንና በምንፈልገው ላይ ስናማትር የዜና አግልግሎቶችና ጋዜጦች የሚያቀርቡልንን ይለውጣሉ::

**ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ**
*የተረጋጋህ ሆነህና ከማትፈልገው ነገር ላይ አትኩሮትህን ለመንቀል እንድትችል ተማር:: በምትመኘው ላይ የማተኮር ተሞክሮ አዳብር:: ኃይል አትኩሮት ወዳለበት ስለሚፈስ::*

«በሃቅ አስብ:: አመለካከቶቹም አለምን ይመግባሉና»
ወራቶ ቦቫር (1808 - 1889)

በዚህ አለም ያለህን ክስተታዊ ኃይል ማየት እየጀመርክ ነው? መልካም መሆናቸው በሚሰማህ ነገሮች ላይ ስታተኩር ወደ አለም የበለጡ ጥሩ ነገሮች እያመጣህ ነው:: ወደራስህ ህይወትም እንዲሁ:: ጥሩ ሲሰማህ ሂወትህን ከፍ ታደርጋለህ:: አለምንም እንዲሁ ከፍ ታደርጋለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ
የውስጠ ድምፅና ራዕይ ከውጫዊው ይልቅ ጥልቅ፣ ግልፅና የሚሰሙ ሲሆኑ ሂወትህን ገዝተህዋል ማለት ነው::

ሊዛ ሂኮልስ
አለምን ወይም የአካባቢህን ሰዎች መለወጥ ሥራህ አይደለም:: ከአለም ጋር መጓዝ ብቻ ነው ስራህ:: በፈሪዋ አለም ውስጥ ማዘክር ጥምር::

አንተ የአለም አለቃ ነህ:: እርሷም ለእያንዳንዱ ትዕዛዝህ መልስ ትሰጣለች:: የማትፈልጋቸው ስዕሎች ቀልብህን አይሳቡት:: ኃላፊነት ውሰድ:: ከቻልክ ብርሃን ስጣቸው:: ኋላም ተዋቸው:: ይሂዱ:: እናም ለምትፈልገው አዲስ አስተሳሰብ ይኑርህ:: ስሜቱም ይደርብህ:: በመሆኑም አመስግን::

## አለም የተትረፈረፈች ናትና

ዶ/ር ጆ ቫይታል
ሁልጊዜ የምጠይቀው ነገር እያንዳንዱ ሰው ምስጢሩን እየተጠቀመበት ነው ወይ? የሚል ነው::

ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ
የምስጢሩ አስተምህሮ ቁንጅና እያንዳንዱ ሊያገኘው የሚችል ብዙ ነገር መኖሩን ማሳየቱ ነው::

በሰዎች አይምሮ ውስጥ እንደ ቫይረስ የሚያደርገው ውሸት አለ:: እሱም «ለንመኘው የሚገባ ምንም በቂ ጥሩ ነገር የለም» የሚለው ነው:: እጥረት፣ ውሱንነትና በቂ ያልሆነ ነገር አለ:: ያ ውሸት ሰዎች በፍርሃት፣ ስስትና ገብጋባነት እንዲኖሩ አድርጓቸዋል:: እነዚያ የፍርሃት፣ ስስትና ገብጋባነት ተሞክሮዎቻቸው ሆኑ:: በመሆኑም አለም የቅዠት ቢኒን ወስዳለች::

t.me/OLDBOOKSPDF

*ሃቁ ልንፈልገው የሚገባን ከበቂ በላይ ነገር አለን:: ከበቂ በላይ ፈጣሪ አስተሳሰቦች አሉ:: በቂ አቅም አለ:: ከበቂ በላይ ፍቅር አለ:: ከበቂ በላይ ደስታ አለ:: ይህ ሁሉ የእራሱን ገደብ - አልባነት በሚያውቅ አይምሮ ውስጥ መምጣት ይጀምራል::*

በቂ የለም ብሎ ማሰብ የውጪውን ስዕል ማየትና ሁሉም ነገር ከውጪ ይመጣል ብሎ ማሰብ ነው:: እንደዚያ ስታደርግ እጥረትንና ጉድለትን ታያለህ:: አሁን ምንም ነገር ከውጪ እንደማይገኝ ታውቃለህ:: ማንኛውም ነገር መጀመሪያ የሚገኘው ከአስተሳሰብና ስሜት ነው:: እናም እንዴት እጥረት ይኖራል? አይቻልም:: የማሰብ ችሎታህ ገደብ የለውም:: ይሆናስ ብለህ የምታስባቸው ነገሮችም ገደብ የላቸውም:: ለሁሉም ሰው እንዲሁ ነው::

**ጀምስ ሬይ**

በዚች አለም ለአንዴ ያለፈ እያንዳንዱ አስተማሪ ህይወት እጥረት የሌለው ማለት እንደሆነ ነግሮናል::

> «የዚህ ህግ ይዘት እጥረትን አታስብ የሚል ነው:: ተትረፍርፎ ይታይሀ:: መትረፍረፍ ይሰማህ:: በመትረፍረፍ እመን:: ምንም አይነት የእጥረት ስሜት በአይምሮህ አይግባ»::
>
> ሮበርት ኮሊየር

**ጆን አሣራፍ**

*የተፈጥሮ ሃብት እየተመናመነ ነው ብለን ስናስብ ለተመሳሳይ አላማ የሚውሉ አዳዲስ የተፈጥሮ ሃብቶች እናገኛለን::*

የቤሊዝ ዘይት ቁፍሮ ታሪክ የተፈጥሮ ሃብትን በማስገኘት የሚያነቃቃ ምሳሌ ነው:: የቤሊዝ ብሔራዊ ኃይል የተወሰነ የንግድ ድርጅት ዲሬክተሮች በታዋቂው በዶ/ር ቶኒ ኩይን የሰለጠኑ ነበሩ:: ደክተሩ በሰባዊ ስነመዋቅር የሰለጠኑ ነበሩ:: በዶ/ር ኩይን የማሰልጠን ብቃት ብሊዝ ብቃት ያላት ዘይት አምራች አገር እንደምትሆን ተማምነዋል:: እንደ የስፔን ዜጎች ዘይት የመቆፈር ደፋር እርምጃ ወስደዋል:: በአንድ አጭር አመት ህልማቸው እውን ሆነ:: ቤሌዝ በጥራቱ ከፍተኛ ያሆነ

ዘይት አገኙ:: አምሳ ሌሎች ካምፓኒዎች ያልቻሉትን ማለት ነው::
አይምሯቸው ያልተገደበ መሆኑን ያመኑ የተሰየ ቡድን አባላት ጠንካራ
እምነት ስለነበራቸው ቤሊዝ የዘይት አምራች አገር ሆነች::

እንኳንና የምንም ነገር የተፈጥሮ ሃብት የሌላ ነገር እጥረትም የለም::
እጥረት ያለው በሰው አይምሮ ውስጥ ነው:: ገደብ ለሌለው የመፍጠር
ችሎታችን እድል ስንሰጥ መትረፍረፍን እንጋብዛለን:: እጅግ አዲስ የሆነ
አለም እናያለን::

ዶ/ር ጆን ዴማርቲኒ
*አድለኞች መሆናችንን የምንገነዘበው ራዕያችን ጉልህ ባለማድረጋችንና በአካባቢያችን ያለውን ነገር ሁሉ ስለማናይ ነው::*

ዶ/ር ጆ ቫይታል
*ሰዎች ከልባቸው መኖር ሲሹና የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲንቀሳቀሱ ታውቃለህ:: ተመሳሳይ ነገርን ለማግኘት አይንቀሳቀሱም:: እዚያ ላይ ነው ቁንጅናው:: ሁላችንም ቢ ኤም ደብሊው መኪና አንፈልግም:: ሁላችንም አንድ ሰው አንወድም:: አንድ አይነት ተሞክሮ አንፈልግም:: አንድ አይነት ልብስ አንወድም እያልክ ባዶ ቦታውን ሙላ::*

ሙሉ የተከበረች አለም ውስጥ ነህ:: ህይወትህን ለመፍጠር የሚገርም
ኃይል አለህ:: ለእራስህ የሚሆን ፈጠራ ለማድረግ ምንም የተገደበ ነገር
የለብህም:: ምክንያቱም የማሰብ ችሎታህ ያልተገደበ በመሆኑ ነው::
የሌሎችን ህይወት ግን መፍጠር አትችልም:: ለእነሱ ለማሰብ
አትችልም:: አመለካከትህን ብትጭንባቸው አፀፋው ተመሳሳይ ይሆናል::
ስለዚህ ሁሉም የሚፈልገውን ህይወት ይፈጥር ዘንድ ተወው::

ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ
*ለሁሉም የሚሆን በቂ ነገር አለ:: ካመንከው፣ ሲታይ ከቻለ፣ ከተንቀሳቀስክበት ይከሰትልሃል:: ሃቁ ያ ነው::*

t.me/OLDBOOKSPDF

«አድለኛ ከሆንክ፣ የደህንነትና ህመም ጠላት ከሆንክ ምክንያቱ ኃይልህን ስለማታውቀው ወይም ሊገባህ ስላልቻለ ነው:: አለም እየሰጠችህ የመሆኑ ጥያቄ አይደለም:: አለም ለሁሉም ድርሻውን ትሰጣለች:: አታዳላም»::

ሮበርት ኮሊየር

## ሊዛ ኒኮልስ

*የምትፈልገው ነገር ሁሉ አለ:: ትጨብጠዋለህም:: ልትመኘውም ይገባል:: ሆን ብለህ የምትሻ መሆን አለብህ:: ሆን ብለህ ስትፈልግ አለም ታቀርብልሃለች:: ከበውህ ያሉትን ውብ ነገሮች ለይተህ አወቃቸው:: ባርካቸው:: አድንቃቸው:: በግልባጩ ደግሞ በማይሆኑህ ነገሮች ላይ ማረምረምህን ግታ:: የበለጠ ታገኝ ዘንድ የምትወደውን ነገር ሁሉ አንጓፍጠው::*

ሊዛ «አድንቅና ባርክ» ያለቻቸው ቃላት በወርቅ የሚመዘኑ ናቸው:: በህይወትህ ማንኛውንም ነገር አድንቅ:: ባርክም:: እንዲህ ስታደርግ በእጅግ ከፍተኛ የፍቅር ፍሪኮንሲ ላይ ትሆናለህ:: በመፀሐፍ ቅዱስ ዕብራውያን ጤና፣ ሃብትና ደስታ ለማግኘት መባረክን ይጠቀሙ እንደነበር ተፅፏል:: የምርቃትን ሃይል ያውቁት ነበር:: ብዙ ሰዎች ሌላን መርቀው የሚያውቁት ባነጠሰ ጊዜ ብቻ ነው:: መዝገበ ቃላት መመረቅን በሉአላዊ ድጋፍ አማካይነት ደህንነትንና ፀጋን ለማግኘት የሚደረግ ሲል ይተረጉመዋል:: እናም መባረክን ጀምር:: ሁሉንም ነገር ሰውንም ባርክ:: ማድነቅም እንዲሁ ነው:: አንድን ሰው ስታደንቀው ፍቅር ትሰጠዋለህ:: ያን ግዙፍ የፍቅር ፍሪኮንሲ ትረጫለህ:: መቶ እጥፍ ሆኖ ወደ አንተ ይመለሳል::

ማድነቅና መባረክ አሉታዊነትን ሁሉ ያሟሟል:: ጠላቶችህንም ጭምር አድንቅ:: ባርክ:: ጠላትህን ከረገምክ እርግማኑ [illegible]
ይሆናል:: ካደነካችጡሩ [illegible]

Scanned wi

t.me/OLDBOOKSPDF

*ዶ/ር ዴኒስ ዌትሌይ*
*የለፉት ዘመናት ብዙ መሪዎች ሥልጣንን ለሌሎች ሳያካፍሉና ኃላፊነትም ሳይሰጡ በመቅረታቸው የሚስጥሩን ትልቅ ክፍል ሳቱት፡፡*

አሁን ስለአለምና ስለራስህ ታውቃለህ፡፡ በዚህ እውቀት ሳቢያ አለምንና የራስህን እውነታ እየተገነዘብክ ነው፡፡ እኔ አለምን በሚመለከት የሚስጥሩ ብልጭታ የታየኝ ከሮበርት ኮሊየር፣ ፕሬንቲስ ሙልፎርድ፣ ቻርለስ ሃኔልና ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ አስተምህሮቶች ነው፡፡ ከዚህ መረዳት ጀምሮ ሙሉ ነፃነት ተሰማኝ፡፡ አንተም ተመሳሳይ ነፃነት እንደሚኖርህ የልብ እምነት አለኝ፡፡

ከቻልክ በመኖርህና በአመለካከትህ ለዚች አለም ትልቁን ጥሩ ነገር ታመጣለህ፡፡ ለሰው ልጆች መፃኢ ጊዜም እንዲሁ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ግብግብ ስትገጥም ግብግብ ገጣሚን ታመጣለህ:: ምክንያቱም በርትተህ በዚሁ ስሜታዊነት ላይ አተኩረሃልና ነው:: ማንኛውንም ነገር ለመለወጥ ወደ ውስጥህ ተመለስና በአስተሳሰብህና ስሜትህ አዲስ አመለካች እርጭ::
- በአሉታዊ ነገሮች ላይ በማተኮር ይችን አለም አትጠቅማትም:: በአሉታዊ ነገሮች ላይ ስታተኩር እያበዛሃቸው ብቻ ሳይሆን ለራስህ ህይወትም አከለህ እያመጣሃቸው ነው::
- በአለም ችግሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ አቅምህን ሁሉ ለእምነት ፣ ፍቅር፣ መትረፍረፍ፣ ትምህርትና ሰላም ላይ አውል
- የጥሩ ነገሮች እጥረት አይገጥመንም ምክንያቱም ለሁሉም የሚሆን ከበቂ በላይ አሉና ነው:: ህይወት ሩሽሩሽ ነው::
- ገደብ ከሌለው የተፈጥሮ አቅርቦት ላይ የምትፈልገውን በአስተሳሰብህና ስሜትህ መዝገን ትችላለህ:: ወደ እውነተኛው ተሞክሮህ ልታመጣውም አቅም አለህ::
- ማንኛውንም ነገር ባርክና አድንቅ:: አሉታዊነትንና ጥላቻን አሟምተህ እራስህን እጅግ ከፍተኛ ከሆነው ከፍቅር ፍሪኩንሲ ጋር ታገናኛለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

## የአንተ /የእራስህ/ ምስጢር

### ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*እራሳችንን ስናይ አካላችንንም ጨምሮ የሚታየን የበረደው ክምር ጫፍ ነው።*

### ቦብ ፕሮክቶር

*ስለዚህ ለትንሽ ጊዜ አስብ። እጅህን ተመልከት። ጠንካራ መስሉ ይታያል። በእውነት ግን አይደለም።*

### ጆን አሣራፍ

*ማንኛውም ነገር እጅህ፣ ውቂያኖስ ይሁን ወይም ኮከብ የተሰራው ከአንድ ነገር ነው።*

### ዶ/ር ቤን ጆንሰን

*ማንኛውም ነገር ኃይል ነው። ትንሽ እንድትረዳው ላግዝህ። አለም አለች። ጋላክሲአችን፣ ፕላኔታችን፣ ህዋሳቶቻችን፣ ሞሉኪሉችና አቶሞችም አሉ። ከዛ ኃይል አለ። ልናስባቸው የምንችለው አያሌ ደረጃዎች አሉ። ነገር የአለም የማንኛውም ነገር ኃይል ነው።*

ምስጢሩን እንዳወቅሁ ሳይንስና ፊዚክስ ስለዚህ እውቀት ምን እንደተረዱ ለማወቅ ፈለግሁ። ያገኘሁት ነገር እጅግ የሚደንቅ ነበረ። የኳንተም ፊዚክስና ሳይንስ ግኝቶች ከምስጢሩ አስተምህሮቶች ጋር ህብር ያላቸው ናቸው። ከታላላቆቹ መምህራን አስተምህሮቶች ጋርም እንዲሁ።

በትምህርት ቤት ሳይንስ ወይም ፊዚክስ አልተማርኩም። ያም ሆኖ በኳንተም ፊዚክስ ላይ የተፃፉ ውስብስብ መፃህፍት ሃሳብ የመረዳት



t.me/OLDBOOKSPDF

ችግር አይገጥመኝም:: ምክንያቱም እንዲገባኝ ስለምፈልግ ነው:: ኳንተም ፊዚክስ ሚስጥሩ እንዲገባኝ እጅግ ጠቅሞኛል::

እንዴት ኃይለኛው የማሰራጫ ጣቢያ እንደሆንክ ልግለፅልህ:: ባጭር ቋንቋ ኃይል ሁሉ በሆነ ፍሪኩንሲ ይርገበገባል :: ኃይል እንደመሆንህ አንተም በተወሰነ ፍሪኩንሲ ትርገበገባለህ:: የአንድን ጊዜ ፍሪኩንሲህን የሚወስነው የምታስበውና የሚሰማህ ስሜት ነው: የምትፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ከኃይል የተሰሩ ናቸው:: እነርሱም እርግብግቢት አላቸው:: ሁሉም ነገር ኃይል ነው::

ስለምትፈልገው ነገር ስታስብ ያን ፍሪኩንሲ ትረጫለህ:: የምትፈልገውን ነገር ኃይል በዛ ፍሪኩንሲ እንዲርገበገብ ታደርገዋለህ:: እናም እራስህ ታመጣዋለህ:: በምትፈልገው ነገር ላይ ስታተኩር የዛን ነገር አቶሞች ንዝረት ትለውጠውና ወደራስህ እንዲርገበገብ ታደርገዋልህ:: ታላቁ የማሰራጫ ጣቢያ የሆንክበት ምክንያት በአስተሳሰብህ ኃይልህን የማተኮር አቅም የተሰጠህ በመሆንህ ነው::

የምትፈልጋቸውን ነገሮች ስትስባቸውና ጥሩነታቸው ሲሰማህ ወዲያውኑ ወደዛው ፍሪኩንሲ ትስተካከላለህ:: ይህም የሁሉም ነገሮች ኃይል ወደአንተ እንዲርገበገቡ ያደርጋል:: ቀጥሎም በህይወትህ ታገኛቸዋለህ:: የስበት ህግ «ማንኛውም ነገር እምሳያውን ይስባል» ይላል:: አንተ የማግኔት ኃይል ነህ:: እናም እያንዳንዱን ወደአንተ በኤሌክትሪካዊ ኃይል ታተርበዋለህ:: እያንዳንዱም ነገር አንተን በተመሳሳይ ይስብሃል:: የሰው ልጅ የራሱን ኃይል ማግኔታዊ ያደርጋል:: ምክንያቱም ከሰው ሌላ የሚፈልገውን የሚያውቅና ስለዚሁም ስሜት የሚያድርበት ስለሌለ ነው::

ወደ አንድ መቶ አመት ከሚጠጋ ጊዜና የሳይንስ ግኝቶች ከጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ቻርለስ ሃኔል አለም እንዴት እንደሰራች አውቋል::

> «አጠቃላይ መንፈስ አዋቂ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭም ነው:: ይህም ተጨባጭ በስበት ህግ አማካይነት ኤሌክትሮኖችን ባንድ አድርጎ አቶሞችን እንዲሰሩ የሚያደርግ የስበት ኃይል ነው:: አቶሞቹ በተራቸው ባንድነት ይሆኑና ሞለኪውሎችን ይፈጥራሉ:: ሞለኪውሎቹ ተጨባጭ ቅርፅ ይይዛሉ:: ህጉም

t.me/OLDBOOKSPDF

በእያንዳንዱ መከሰት ላይ ፈጣሪ ኃይል ሆኖ እናገኘዋለን። በአተሞች መስራት ብቻ ሳይሆን ልንገምተው በምንችለው በማንኛውም ነገር ላይ ሁሉ እንጂ»

ቻርለስ ሃኔል

## ቦብ ፕሮክቶር

ስለምትኖርበት ከተማ አያገባኝም። በአካልህ ውስጥ ሳምንት ለሚሆን ጊዜ ከተማውን ሁሉ ብርሃናማ ለማድረግ የሚችል ኃይል አለህ።

«ይህን ኃይል መገንዘብ ህያው የማስተላለፊያ ገመድ መሆን ነው። ህያው የማስተላለፊያ ገመድ አለም ናት። የእያንዳንዱን ግለሰብ ሁኔታ የሚያረካ በቂ ኃይል ትሸከማለች። የግለሰብ አይምሮ አጠቃላይ አይምሮን ሲነካ ኃይሉን ሁሉ ያገኛል»።

ቻርለስ ሃኔል

## ጀምስ ሬይ

ብዙ ሰዎች እራሳቸውን በምድራዊ አካላቸው ይገልፃሉ። አንተ ግን ውሱን አይደለህም። አጉልቶ በሚያሳይ መነፅር ሳይቀር የኃይል መስክ ነህ። ስለኃይል የምናውቀው ይህን ነው። አንድን የኳንተም ፊዚክስ ባለሙያ «አለምን ማን ፈጠራት?» በለው። «ኃይል» ይልሃል። ደህና! ኃይልን ግለፀው በለው።

«አይጠፋም፣ አይፈጠርም። ሁሌም የነበረ ነው። የነበረ ሁሉ ኗሪ ነው። ቅርፅ ይይዛል ከቅርፅ ተነስቶና ከቅርፅ ወጥቶ» ይልሃል። አንድን የሃይማኖት ትምህርት የተማረ ሰው «አለምን ማን ፈጠራት?» ብለህ ጠይቀው። «እግዚአብሔር» ይልሃል። እግዚአብሔርን ግለፀው በለው። «ሁልጊዜ የነበረ፣ ሁልጊዜ አየኖረ ያለ፣ የማይፈጠረና የማይጠፋ፣ ሁልጊዜም የነበረ፣ የሚኖር፣ ከቅርፅ ወጥቶ በቅርፅ በኩል ወደ ቅርፅ የሚሄድ» ይልሃል። የቃላት ለውጥ ካልሆነ በስተቀር የሁለቱም ገለፃ አንድ አይነት መሆኑን ተመልከት። ስለዚህ እዛና እዚህ የምሽከረከር ስጋ ለባሽ ነኝ ብለህ የምታስብ ከሆነ እንደገና አስብ። አንተ መንፈሳዊ አካል ነህ። በግዙፍ የኃይል መስክ ውስጥ የምትንቀሳቀስ የኃይል መስክ ነህ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሁሉ እንዴት መንፈሳዊ አካል ያደርግሃል? ለእኔ የዚህ ጥያቄ መልስ የሚሰጥሩ አስተምህሮ ታላቁ ክፍል ይመስለኛል:: ኃይል ነህ:: ኃይል ደግሞ አይፈጠርም አይጠፋም:: ኃይል ቅርፁን ብቻ ነው የሚለውጥ:: ያ ማለት አንተ፣ እውነተኛ ያንተ ይዘት፣ የተጣራው እራስ-ኃይል አንተው ነበርክ:: አንተውትም ትሆናለህ:: ሌላ አትሆንም::

ጠለቅ ሲል ያን ታውቀዋለህ:: አለመሆንን ማሰብ ትችላለህ? ምንም እንኳን እያሌ ተሞክሮ ያለህ ብትሆንም አለመሆንን ልታስበው ትችላለህ? ልታስበው አትችልም:: ስለማይቻል:: አንተ ዘላለማዊ ኃይል ነህ::

## አንዱ አጠቃላይ አይምሮ /መንፈስ/

### ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*ኳንተም ሜካኒክስ አረጋግጦታል:: ኳንተም ኮስሞሎጂም እንዲሁ:: አለም የመጣችው ከሃሳብ መሆኑን:: ሁሉም የአካባቢያችን ቁስ አካል የዘቀጠ ሃሳብ ነው:: በመጨረሻ የአለም መነሻ እኛው ነን:: ይህን አቅም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስንሞክረው ስልጣናችንን ለመተግበርና የተሻለ ለማግኘት እንጀምራለን:: ማንኛውንም ነገር እንፈጥራለን:: በንቃተ ህሊናችን ያለውን ሁሉ እናውቃለን:: የማታ ማታ አለምን የሚያንቀሳቅሳት አጠቃላይ መንፈስ/አይምሮ/ ነውና:: የዚያ ኃይል አውንታዊ ወይም አሉታዊ አጠቃቀም ጤናችንን፣ አካባቢአችንን፣ ወዘተ ይወስናል:: ኃይላችንን የምንጠቀምበት መጠን ደግሞ በአስተሳሰብ ደረጃችን የሚወሰን ነው::*

አንዳንዶቹ ቀደምት ተመራማሪዎች አለምን ልክ አንደ ዶ/ር ሃጌሊን ሏሪው አጠቃላዩ መንፈስ (አይምሮ) ብቻ ነው. ብለው ነው የገለፁት:: አንዱ መንፈስ የሌለበት ቦታ የለም ብለዋል:: በማንኛውም ውስጥ ሏሪነቱን አብስረዋል:: ሁሉም ነገር አጠቃላዩ መንፈስ ከሆነና ሁለንተናው በሁሉም ቦታ የሚገኝ ከሆነ በአንተም ውስጥ አለ::

ምን ማለት እንደሆነ እንድትረዳ ላግዝህ:: እያንዳንዱ አጋጣሚ አለ:: ሁሉም እውቀት፣ ግኝትና መፃኢ ፈጠራዎች ለአጠቃላዩ መንፈስ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚታይ ናቸው:: የሰውን አይምሮም እስኪሰባቸው ይጠባበቃሉ:: ታሪኮችን ማግኛውም ፈጠራና ግኝት ከአጠቃላዩ መንፈስ የተገኘ ነው:: ከአጠቃላዩ መንፈስ እንዴት ይገኛል? ያን መንፈስ ስትገነዘብ:: እስደናቂውን አርቆ አመለካከትህን ስትጠቀም:: ልታሟላቸው የሚገቡ ፍላጎቶችን ተመልከት:: ይህን ለማድረግ ትልቅ ፈጠራ እንዳለህ ገምት:: ፍላጎቶችን አስታውስ:: ሲረኩ ይታይህ:: ምንም ነገር መፈለስፍ አይኖርብህም:: ያ የኃያሉ መንፈስ ኃላፊነት ነው:: ያንተ ኃላፊነት ጥያቄ ማቅረብ ብቻ ነው:: ስትጠይቅ ስታምንና ሲሰማህ ታገኛለህ::

«የአምላክ መንፈስ ብቸኛው እውነታ ነው»

ቻርለስ ፊልሞር

## ደን አሣራፍ

*ሁላችንም የተገናኘን ነን አይታየንም እንጂ :: «እዛ ውጪ» እና «እዚህ ውስጥ» የሚባል ነገር የለም::*

ሁሉም የአለም ነገር የተዛመደ ነው:: አንድ የኃይል መስክ ነው:: ከየትም አቅጣጫ ተመልከተው ውጤቱ አንድ አይነት ነው:: አንድ ነን:: የአንድ ኃይል መስክ ክፍሎች ነን:: የፈለከውን ብለህ ጥራው ሁላችንም አንድ ነን::

አሁን ስለስበት ህግ አንድ ከመሆናችን አኳያ ብታስብ ፍፁም ትክክል መሆኑን ታያለህ:: ስለሌላው ያለህ አሉታዊ አመለካከት የቱን ያህል እራስህን እንደሚጎዳው ትረዳለህ:: አንድ ነን :: እራስህ ጉዳትን ካልጠራህ ጉዳት አይደርስብህም:: ምርጫው ያንተ ነው:: አሉታዊ ስሜትና አመለካከት ሲኖርህ እራስህን ከአንዱና ከጥሩ ነገር ትነጥላለህ:: እያንዳንዱን አሉታዊ ስሜታዊነት ስታስብ ከፍርሃት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ታገኘዋለህ:: ከመገንጠል አመለካከትና ከሌሎች በመለየትህ ሳቢያ የመጣ ነው::

ውድድር የመገንጠል ምሳሌ ነው:: መጀመሪያ የውድድር አስተሳሰብ ካለህ ከእጥረት አመለካከት የመጣ መሆኑን ተረዳ:: እጥረት ካለ ነገሮችን ለማግኘት እንታገላለን:: ያሸነፍክ እንኳን ቢመስልህ አታሸንፍም:: በስበት ህግ መሰረት ስትወዳደር ከአንተ ጋር የበለጠ የሚወዳደሩ ሰዎችን

ትጋብዛለህ:: በመጨረሻም አታሸንፍም:: ሁላችንም አንድ ስለሆን ስትወዳደር ከራስህ ጋር ነው የምትወዳደረው:: ውድድርን ከአይምሮህ አውጣ:: በህልምህና በራዕይህ ላይ አተኩር:: ውድድርን ሁሉ ከጥያቄህ አውጣ::

አለም የሁላችን ናት:: ለሁላችንም ያላትን ታቀርባለች:: ሁሉንም ነገር የምታገኘው ግን በሰዎች ሁኔታዎችና ኩነቶች አማካይነት ነው:: የስበት ህግን የአቅርቦት ህግ ነው ብለህ አስብ:: ህጉ ነው ማለቂያ ከሌለው አቅርቦት እንድታገኝ የሚያስችልህ:: የምትፈልገውን ነገር ትክክለኛ ፍሪኩንሲ ስትረጭ ትክክለኛ ሰዎች፣ ሁኔታዎችና ኩነቶች ወዳንተ ይሳቡና ይሰጡሃል::

የምትፈልጋቸውን ነገሮች የሚሰጡህ ሰዎች አይደሉም:: ያን የተሳሳተ እምነት ከያዝክ እጥረት ያጋጥምሃል:: ምክንያቱም አቅርቦትን የጠበቅከው ከውጪው አለምና ሰው በመሆኑ ነው:: እውነተኛው ሰጪ የማይዳሰሰው መስክ ነው:: በፈለከው ስም ጥራው:: የሆነ ነገር ስታገኝ በስበት ህግ የሳብከው መሆኑን አስታውስ:: ከአጠሳይ ሰጪው ጋር ህብር ስለአለህ እንዳገኘኸው ይግባህ:: አጠቃላዩ መንፈስ ከሁሉም በላይ የሆነው ሰውን፣ ሁኔታን፣ ኩነትን ሊሰጥህ ያቀርብልሃል:: ምክንያቱም ህጉ እንደዚያ ስለሆነ ነው::

## ሊዛ ኒኮልስ

*አብዛኛውን ጊዜ አካላችን ብለን ከምንጠራጠረው ነገር ጋር እንለያያለን: መንፈስህን ብቻ ትይዛለህ:: መንፈስህም ክፍሉን የሚሞላ ግዝፈት አለው:: ዘላለማዊ ህይወት ነህ:: አንተ እግዚአብሔር በሰው ቅርፅ ሆኖ ነህ:: ምልዑ ነህ::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*በቅርጻችን የእግዚአብሔር ምስሉች ነን ልንል እንችላለን:: አለም እራሷን የተገነዘበችበት ሌላ መንገድ ነን ለማለት እንችላለን:: የመሆን መቻል ዘላለማዊ መስክ ነን ለማለት እንችላለን:: ሁሉም ልክ ነው::*

«ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ ማንነትህ የማይዳሰስና የማይከሰት ነው»
አር ቡክሚኒስተር ፋለር *(1895 - 1983)*

t.me/OLDBOOKSPDF

አንተ ሥጋ የለበስክ አምላክ ነህ:: ዘላለማዊ ነህ:: ኃያል ነህ:: ጥበብ ነህ:: ገዛዥ ነህ:: ትክክለኛ ነህ:: ትልቅ ነህ:: ፈጣሪና በዚች ፕላኔት የራስህን ፍጥረት እየፈጠርክ ያለህ ነህ::

**ጀምስ ሬይ**

ዘለማዶች ሁሉ የፈጠረሀን ምስል ይዘህ የተፈጠርክ መሆኑን ነግረውሃል:: ይህ የራስክን አለም ለመፍጠር የሚያስችል አምላካዊ አቅም አለህ ማለት ነው:: አለህም:: ምናልባት እስከአሁን አስገራሚ ነገሮችን ፈጥረህ ሊሆን ይችላል:: አልፈጠርክምም ይሆናል:: የምጠይቅህ «የህይወትህ ውጤቶች በእውነት የምትፈልጋቸው ናቸው? ይጠቅሙኃል?» የሚሉትን ነው:: የማይጠቅሙህ ከሆነ መለወጥ ያለብህ ጊዜ አሁን ነው:: ምክንያቱም ያን ለማድረግ አቅም አለህና ነው::

«ኃይል ሁሉ በውስጣችን ነውና በቁጥጥራችን ስር ነው»
ሮበርት ኮሊየር

## አንተ ያለፈ ጊዜህ አይደለህም

**ጃክ ካንፊልድ**

ብዙ ሰዎች በህይወት የተጎዱ ይመስላቸዋል:: ለጉዳታቸውም ያለፉ ሁነቶችን ያመላክታሉ:: ከባለጌና ከሰነፍ ቤተሰብ ውስጥ እንደማደግ የመሳሰሉ ምክንያቶችን ይጠቁማሉ:: አያሌ የሥነ-አእምሮ ባለሙያዎች ወደ 85 ከመቶ የሚጠጋ ቤተሰብ የፈረሰ መሆኑን ያምናሉ:: እንዲህ ከሆነ የማንም ቤተሰብ የተለየ አይደለም::

የእኔ ወላጆች ጠጪዎች ነበሩ:: አባቴ ተጫውቶብኛል:: እናቴ የስድስት አመት ልጅ እያለሁ አባቴን ፈታችው:: እንግዲህ የሁሉም ታሪክ ከሞላ ጎደል ይህን መሰል ነው:: ጥያቄው «አሁን ምን ይደረግ?» ነው:: ምክንያቱም አንድም በአለፈው ላይ ካሊያም በምትፈልገው ላይ አትኩሮት ማድረግ ያለብህ ስለሆነ ነው:: ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

*በሚፈልጉት ላይ ሲያተኩሩ የማይፈልጉት ይሸሻል:: የሚፈልጉት ሲበዛ ተቃራኒው ይሰወራል::*

«በህይወት ጨለማማ ጉን አይምሮውን ያሳረፈ ወይም በአሉታዊ መጥፎ አጋጣሚና አስመሳካት ላይ ደግሞ ደጋግሞ የሚጥር ሰው በመግኢ-ዘመኑም ይኸው ይሆን ዘንድ ይፀልያል:: በመግኢ-ዘመንህ መጥፎ እድል ብቻ ከታየህ ለዚህ መጥፎ እድል እየፀለይክ ነውና በእርግጥ ታገኘዋለህ»::

ፕሬንቲስ ሙልፎርድ

ወደ ኋላ መለስ ብለህ ባለፉት ችግሮች ላይ ካተኮርክ ተጨማሪ ችግሮችን እየጋበዝክ ነው:: የፈለገው ይሁን ተወው:: ቂም ከያዝክ ወይም ለአንድ ላለፈ ነገር አንድን የሆነ ሰው ምክንያት እያደረክ ከሆነ እራስህን እየጎዳህ ነው:: የሚገባህን ህይወት የምትፈጥረው ራስህ ነህ:: ሆን ብለህ በምትፈልገው ላይ ስታተኩርና ጥሩ ስሜት ሲያድርብህ የስበት ህግ አህሩውን ይመልስልሃል:: ማድረግ ያለብህ ነገር መጀመር ነው:: ስትጀምረው ታምሩን ታየዋለህ::

## ሊዛ ኒኮልስ

*የመዳረሻህ ነዳፊ አንተው ነህ:: ደራሲውም:: ታሪኩን ፃፊው ብዕሩ በእጅህ ነው:: ውጤቱም የመረጥከው ነው::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*የስበት ህግ ውበቱ ባለህበት ደረጃ መጀመር የምትችል መሆኑ ነው:: ሃቀኛ አስተሳሰብ ማሰብ መጀመር ትችላለህ:: የህብርና ደስታ ስሜት ማመንጨት መጀመር ትችላለህ:: ህጉ የአህሩ ምላሹን መስጠት ይጀምራል::*

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

*ስለዚህ አሁን «አለም ከበቴ በላይ አላት» የሚል የተለየ አመለካከት ለማዳበር ጀምር:: ወይም «እያረጀሁ አይደለም:: ወጣት እየሆንሁ*

t.me/OLDBOOKSPDF

*ነው» የሚል እምነት አሳድር:: በስበት ህግ መሰረት እንደፈለከው ይሆንልሃል::*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*እራስህን ከትውልድ፣ ባህልና ማህበረሰባዊ እምነት አባዜ ለመነጠል ትችላለህ:: ለአንዴና ለመጨረሻ በውስጥህ ያለው ኃይል በአለም ካለው የበለጠ መሆኑን አረጋግጥ::*

## ዶ/ር ፍሬድ አላን ወልፍ

*«መልካም፣ ጥሩ ነገር ነው:: ላደርገው ግን አልችልም:: ልታሰራኝ አትችልም. አያሰራኝም:: ገንዘብ የለኝም:: አልችልም፣ አልችልም፣ አልችልም» እያልክ ልታስብ ትችላለህ::*
*እያንዳንዱ «አልችልም» ፈጠራ ነው::*

እኔ ነኝ የሚሉትን ቃላት እቅም ታላላቆቹ አስተማሪዎች የዘገቧቸው መሆኑን ዶ/ር ሙልፍ ጨለፍ አድርገውልናል:: «እኔ ነኝ » ስትል የሚከተሉት ቃላት መፍጠርን አጠንክረው ይጠራሉ:: ምክንያቱም የሆነ ነገር በእውን የተከሰተ እንዲሆን እያበሰርክ ስለሆነ ነው:: በእርግጠኝነት እያልከው ነው:: «ደክሞኛል፣ የለኝም፣ አሞኛል፣ ዘግይቻለሁ፣ ወፍሬአለሁ፣ አረጀሁ ወዘተ » ካልክ ወዲያውኑ ጂኒው ተቀብሎ «ፍላጎትህ ትዕዛዜ ነው» ይልሃል:: ይህን ካወቅህ ለጥቅምህ «እኔ ነኝ «የሚሉትን ቃላት መጠቀም መጀመር ጥሩ ሃሳብ አይሆንም? መልካሙን ሁሉ እያገኘሁ ነው የሚለውስ? « ደስተኛ ነኝ፣ እለኛ፣ ጤነኛ ነኝ፣ ፍቅር ነኝ፣ አልዘገይም፣ ዘላለም ወጣት ነኝ፣ በየቀኑ አቅሙ-ሙሉ ነኝ ማለትስ?»

ቻርለስ ሃኔል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰው ልጅ ሊፈልጋቸው የሚችሉ ነገሮችን የሚያዋህድ ማረጋገጫ መኖርን ጠቁሞዋል:: ይህ ማረጋገጫ ሁሉም ነገሮች ህብረ-ዊ ሁኔታዎችን ያመጣል ሲሉም ነግረውናል:: የዚህ ምክንያት ማረጋገጫው ከእውነቱ ጋር ተመሳሳኝ ስለሆነ መሆኑን በተጨማሪ ነግረውናል:: እውነት ሲከሰት ደግሞ የስህተት አይነት ሁሉ ጥፉን ይደባል::

t.me/OLDBOOKSPDF

ማረጋገጫው «እኔ ምሉዑ፣ ትክክለኛ፣ ጠንካራ፣ ኃይለኛ፣ አፍቃሪ፣ ሰላማዊና ደስተኛ ነኝ» የሚል ነው።

የምትፈልገው ነገር ከማይታይ ወደሚታየው እንዲመጣ የምትፈልገው ከሆነ የምትፈልገው ነገር ፍፁም እውነት ነው ብለህ እመን። ይህም የምትሻው ነገር በብርሃን ፍጥነት እንዲከሰት ያደርገዋል። ሁለተኛ ጥያቄህ ይህ እውነት ነገር በአጠቃላዩ መንፈሳዊ መስክ ውስጥ ያለ መሆኑ ይሁን። ይኸውም ያ መስክ ብቻ ነው። በአይምሮህ አንድን ነገር ስታሳድር እውነት መሆኑን እወቅ። መከሰት መቻሉም ከጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም።

«ይህ ህግ ሊያደርግልህ የሚችለው ነገር ገደብ የለውም። በራስህ ሃሳብ ለማመን ይዳዳህ። ያሰነበውን ሁሉ የተከናወነ ሃቅ እንደሆነ አድርገህ አስብ»።

ቻርለስ ሃኔል

ሄነሪ ፎርድ በሞተር የሚሰራ ተሽከርካሪ ራዕዩን ሲያመጡ በአካባቢያቸው የነበሩ ሰዎች አሾፉውባቸዋል። «እብዶ መሆን አለበት የዚህ አይነት ሃሳብ የሚያራምደው» ተብለው ነበር። ሄነሪ ፎርድ ያሾፉባቸው ሰዎች ከሚያውቁት የበለጠ ያውቁ ነበር። ሚስጥሩንና የአለምን ህግ አውቀውት ነበር።

«እችላለሁ ብለህም ሆነ አልችልም ብለህ ካሰብክ በሁለቱም መንገድ ትክክል ነህ»

ሄነሪ ፎርድ (1863 - 1947)

የምትችል ይመስልሃል? በዚህ እውቀት በመረዳት ብዙ ነገር ማግኘት ትችላለህ። ባለፉት ጊዜአት የቱን ያህል ብሩህ መሆንህን ገት አድርገህ አይተኸው ይሆናል። አሁን ግን ከፍተኛ አይምሮ መሆንህንና የምትፈልገውን ሁሉ ከከፍተኛው አይምሮ የምታገኝ መሆኑን ታውቃለህ። የምትፈልገውን ሁሉ ታደርጋለህ። ለመግለፅ ከሚቻለው በላይ አዋቂ ነህ። ይህን ለራስህ መንገር ጀምር። ማን እንደሆንክ ተገንዘብ።

**ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ**

t.me/OLDBOOKSPDF

*ለዚህ የሆነ ገደብ አለው? በፍፁም የለውም:: ያልተገደበን ሀያውያን ነው:: ጣራ የለንም:: በዚች ፕላኔት ያለ ማንኛውም ግለሰብ የችሎታ፣ የዝቃት፣ የኃይል፣ ወዘተ ምንም ገደብ አልተደረገበትም::*

# አስተሳሰቦችህን ተገንዘብ

እንዲሆን ከፈቀድክለት አይምሮህ እንደባቡር አይነት ሊሆን ይችላል:: ወደለፉ ሃሳቦች ይወስድሃል:: ያለፉ መጥፎ ክስተቶችን ጉትቶ በማምጣት ስለወደፊቱ ሊያሳስብህ ይችላል:: ልትቆጣጠራቸው የማትችላቸው ሃሳቦችም ይፈጠራሉ:: በአሁኑ ጊዜ መሆንህን ስትገነዘብና ምን እያሰብክ እንደሆነ ስታውቅ በአስተሳሰብህ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ትችላለህ:: አትምህም ይኸው ነው::

የተሻለ ለመገንዘብ እንዴት ትችላለህ? አንደኛው መንገድ ቆም ብሉ «ምን እያሰብኩ ነው? ምን እየተሰማኝ ነው?» በማለት እራስህን መጠየቅ ነው:: ይህን በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ አድርገው:: ኃይልህ ነው:: ምክንያቱም አቅምህ ስለአቅምህ ያለህ ግንዛቤ መሆኑን አስታውስ:: ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ የዚህን አቅም ግንዛቤ «ለማስታወስ አስታውስ» ሲሉ ደምድመውታል:: እነዚህ ቃላት የህይወቴ መዝሙር እምብርት ሆነዋል::

«የኃይል እውነተኛው ሚስጥር የኃይል ንቃተ ህሊና ነው»::.

ቻርለስ ሃኔል

የሚስጥሩ ምንነትን ስትገነዘብና በጥቅም ላይ ለማዋል ስትጀምር ጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ ያገኛሉ:: በስበት ህግ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት ስትጀምር ጥያቄ መጠየቅ ባህልህ መሆን ይጀምራል:: ይህን ስታደርግ ደግሞ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ታገኛለህ:: ለዚያ አላማ ይህን መጽሐፍ እራሱን ልትጠቀምበት ትችላለህ:: መልስ የምትፈልግ ከሆነ ወይም ስለሆነ ነገር መምሪያ ካስፈለገህ አስቀድመህ ጥያቄ አንሳ:: ከዛም በኋላ ይህን መጽሐፍ አልፈህ፣ አልፈህ ክፈት:: ገፆቹ በተከፈቱበት ቦታ ላይ መመሪያዎቹና መልሶቹን ታገኛለህ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ሃቱ፡ እሰም ጥያቄዎችህን ሁሉ ስትመልስልህ መኖሯ ነው። ነገር ግን የማንዛቤ አጥረት እያሰብህ መልስ ማግኘት አትችልም። በእንዳዚህ ስለአለው ነገር ሁሉ ግንዛቤ ይኑርህ። ምክንያቱም በየቀኑ በማንኛውም ሰአት ለጥያቄዎችህ መልስ እያገኘህ ነውና። መልሶቹ የሚመጡበት መንገዶች የተወሰኑ አይደሉም። ጋዜጣ ስታነብ ልታገኛቸው ትችላለህ። ከሌላ ሰው ወሬ ልትሰማ ትችላለህ ወዘተ። ለማስታወስ አስታውስና የተገነዘብክ ሁን።

በራሴ ህይወትና በሌሎችም ህይወት ያገኘሁት ነገር ቢኖር ለሰእራሳችን መልካም አመለካከት የሌለን መሆኑንና እራሳችንን የማንወድ መሆኑን ነው። እራስን አለመውደድ የምንፈልገውን ነገር ከእኛ ያርቅብናል። እራሳችንን መውደድ ሲያቅተን ነገሮችን ከእኛ ለማራቅ እየገፋናቸው ነው።

የፈለገው ነገር ይሁን የምንፈልገው ከሆነ ፍቅር ይወሰውሰዋል። የምንወዳቸውን ነገሮች ለመሣብ ፍቅርን ማስተላለፍ አለብን። ነገሮችም ወዲያውኑ ከተፍ ይላሉ። የፍቅርን ፍሪኩንሲ ለማስተላለፍ እራስህን መውደድ አለብህ። ይህ ለብዙዎቻችን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። አሁን እያየኸው ባለው ውጫዊ ነገር ላይ ካተኮርክ እራስህን ውጥረት ላይ ልትጥል ትችላለህ። ምክንያቱም ስለራስህ አሁን እያሰብክ ያለኸውና እየተሰማህ ያለው ቀደም ያለው አስተሳሰብህ ውጤት ስለሚሆን ነው።

እራስህን ሙሉ በሙሉ ለመውደድ በእራስህ አዲስ መጠን ላይ ማተኮር አለብህ። በውስጥ ባለው እሁንነት ማተኮር አለብህ። ጊዜ ወስደህ ፀጥ ብለህ ቁጭ በል። ውስጥህንም አዳምጥ። ስታዳምጥ እራሱን ሲከስትልህ ይጀምራል። ስሜቱም ፍፁም የፍቅር፣ የፍስሃና የምልዐነት ነው። የእሁኑ እውነተኛው አንተ ነህ። በእሁኑ ላይ ስታተኩርና እሁንን ስታመሰግን እራስህን ሙሉ ለሙሉ ትወዳለህ።

እራስህን መተቸት ስትጀምር ወዲያውኑ ወደእሁኑ አትኩሮትህን መልሰው። እንደዚህ ስታደርግ ተከስተው የነበሩ ጉድለቶች በሙሉ ይወገዳሉ። ምክንያቱም ጉድለት በእሁን ብርሃን ውስጥ መኖር አይችልምና ነው። እንደዚህ እያደረክ በሽታን በደህንነት፣ ድህነትን

t.me/OLDBOOKSPDF

በማግኘት፣ እርጅናን በመጣትነት ወዘተ ተካ። በውስጥህ ያለውን እሁን ውደድ። አተኩርም።

«የማይታበለው ሃቅ «እኔ» የሚለው የተሟላና ትክክለኛ መሆኑ ነው። እውነተኛው «እኔ» መንፈሳዊ ነው። እናም ትክክለኛ መሆን አያንሰውም። ምንም እጥረት፣ ውስንነት ወይም ህመም ፈፅሞ የለውም»

ቻርለስ ሃኔል

## የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- ሁሉም ነገር ሃይል ነው። አንተ የኃይል ማግኔት ነህ፣ እናም እራስህን ወደ ሌሎች ነገሮች ታበረታለህ እነርሱም ወደ አንተ እንደዚሁ ያደርጋሉ።
- አንተ መንፈሳዊ ሀልው ነህ። ኃይል ነህ። ኃይልም አይፈጠርም አይሰወርም። የቅርፅ መለወጥ ብቻ ነው የሚያደርገው።
- አለም የመጣችው ከሃሳብ ነው። የራሳችን ብቻ ሳይሆን የአለምን እድል ፈጣሪዎች ነን።
- የማያልቅ የሃሳብ አቅርቦት አለልህ። እውቀት፣ ግኝቶችና መፈልሰፍ ሁሉ የመሆን እድል ያላቸውና በአጠቃላዩ መንፈስ ውስጥ ያሉ ናቸው። የሰው አይምሮም የራሱ ያደርጋቸው ዘንድ ይጠባበቃሉ። ማንኛውም ነገር በንቃተ ህሊናህ ውስጥ ተይዟል።
- ሁላችንም ግንኙነት አለን። እናም አንድ ነን።
- ያለፉ ችግሮች፣ የባህል ጣጣዎችና የህብረተሰብ እምነቶች ሁሉ ይወገዱልህ። የምትፈለገውን ህይወት መፍጠር የምትችለው እራስህ ነህ።
- ምኞቶችህን እውን ለማድረግ አጭሩ መንገድ የፈለከውን ነገር ፍፁም ሃቅ መሆኑን መረዳት ነው።
- አቅምህ ያለው ከአመለካከትህ ነው። ይህን ተግንዘበህ ተቀመጥ። በሌላ አነጋገር «ለማስታወስ አስታውስ»።

t.me/OLDBOOKSPDF

# የህይወት ምስጢር

## ኒል ዶናልድ ቫልሽ

*(ደራሲ፣ አስም እትፍ ተናጋሪና መንፈሳዊ መሪህ)*
*እግዚአብሔር ራዕይህን፣ ተልኮህንና የመሳሰሉትን የጻፈበት ጥቁር ሰሌዳ በሰማይ ተንጠልጥሎ አልተቀመጠም። ማን እንደሆንኩ ለመረዳት እችል ዘንድ ያን ጥቁር ሰሌዳ ማግኘት ይኖርብኛል። ጥቁሩ ሰሌዳ ደግሞ የለም።*

*እናም አላማህ አላማዬ ነው ያልከው ነው። ተልዕኮህም ለእራስህ የሰጠኸው ተልዕኮ ነው። ህይወትህ እንዲሆን የፈጠርከው አይነት ህይወት ይሆናል።*

የህይወት ጥቁር ሰሌዳህን መሙላት ያለብህ አንተው ነህ። ጥቁር ሰሌዳህን ባለፉ ጓዞች ሞልተኸው ከሆነ አፅዳው። የማይጠቅምህን ያለፈ ነገር ደምስሰው። እዚህ ስለደረስክ ብቻ አመስግን። አሁን ንፁህ ሰሌዳ አለህ። እዚህ ላይ አሁኑኑ ጀምር። ደስታህን ተጐናፀፍና ኑረው።

## ጃክ ካንፊልድ

*ይህን ነጥብ ለመረዳት ረዥም አመት ፈጅቶብኛል። ምክንያቱም በአስተዳደጌ ማድረግ የሚጠበቅብኝ ነገር እንዳለ ይነገረኝ ስለነበረ ነው። የተጠበቀብኝን ነገር ባላደርግ እግዚአብሔርን እንደማስቀይም ተነግሮኛል።*

*የመጀመሪያው አላማዬ እራሴን ማስደሰት መሆኑ እንደገባኝ ደስታ የሚያመጡልኝን ነገሮች ብቻ ማድረግ ጀመርኩ። «ካላስደሰተህ ተወው» የሚል አባባል አለኝ*



t.me/OLDBOOKSPDF

### ኒል ዶናልድ ቫልሽ

*ደስታ፣ ፍቅር፣ ነፃነት፣ ፈንጠዝያ፣ ሣቅ:: ይህ ነው:: ለአንድ ሰአት ቆጭ ብለህ ተመስጠህ ደስታን እየሞከርከው ከሆነ ባድናቆት አድርገው:: ሳንድዊች መብላት ደስታ የሚያመጣልህ ከሆነ ተጥልበት::*

### ጃክ ካንፊልድ

*ከድመቴ ጋር ስጫወት በደስታ ላይ እሆናለሁ:: በተፈጥሮ መካከል ስጓዝ ደስ ይለኛል:: እናም ሁልጊዜ እንዲያ ለመሆን እፈልጋለሁ:: ሳደርገው ግን ፈልጌው መሆኑን ማረጋገጥ አለብኝ:: የፈለኩት ከሆነ ይፈፀማልና::*

የምትወደውንና ደስታ የሚያመጣልህን ነገር አድርግ:: ደስታ የሚያመጣልህን ነገር ካላወቅህ «የሚያስደስተኝ ምንድን ነው?» ብለህ ጠይቅ:: የስበት ህግ የሚያስደስትህን ሁሉ ያጉርፍልሃል::

### ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*ውስጣዊ ደስታ በእርግጥ የግብ መምታት ነዳጅ ነው:: አሁን ደስ ይበልህ:: አሁን ጥሩ ይሰማህ:: ያን ነው ማድረግ ያለብህ:: ይህን መጽሐፍ በማንበብህ ያገኘሽው ቁም ነገር ይህ ከሆነ እጅግ ትልቅ የሆነውን የሚስጥሩን ክፍል አግኝተሽዋል::*

### ዶ/ር ጆን ግሬይ

*ጥሩ ስሜት የሚያሳድርብህ ማንኛውም ነገር ሁልጊዜ ተጨማምሮ የሚመጣልህ ነው:: ይህን መጽሐፍ አሁን እያነበብክ ነው:: አንተ ነህ እንዲህ ያደረከው:: ወስደህ በጥቅም ላይ ማዋል መቻል የራስህ ውሳኔ ነው:: ይህ የሚሆነው ጥሩ ስሜት አሳድሮብህ ከሆነ ነው:: ካልሆነ ግን ካንተ አርቀው:: ሌላ የሚያስደስትህ ነገር ፈልግ:: ልብህን የሚሰውር ሌላ ነገር አግኝ::*

የምስጢሩ እውቀት ተሰጥቶሃል:: በዚህ እውቀት ምን ማድረግ ያለብህ ስለመሆኑ በአንተው እጅ ነው:: ለእራስህ የመረጥከው ነገር ሁሉ ትክክል

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጠቀምበት አልጠቀምበት በልና ወስን። የመምረጥ ነፃነት ያንተ ነው።

«ሀሳብህን ተከተል። አለያም በሯን ትከፍትልሃለች።»

ጆሴፍ ካምቤል

## ሊዛ ኒኮልስ

ሀሳብህን ስትከተል በሚያደርግ ደስታ ውስጥ ትኖራለህ። ራስህን ለአለም የተትረፈረፈ ሀብት ታዘጋጃለህ። ከምትወዳቸው ጋር ህይወትን ለመጋራት ትጓጓለህ። ጉጉትህ፣ ፍቅርህና ሀሳብህ ተባባሪ ይሆናሉ።

## ዶ/ር ጆ ቫይታል

ሁለጊዜ የማደርገው እንደዚያ ነው። ጉጉቴን፣ ፍቅሬንና ርህራሄዬን መከተል። እማደርገውም ሁልጊዜ ነው።

## ቦብ ፕሮክቶር

ህይወትን ተዝናናበት። ምክንያቱም ህይወት ክስተታዊ ነውና። ህይወት ትልቅ ጉዞ ነው።

## ሜሪ ዲያመንድ

በተለየ እውነታ፣ በተለየ ህይወት ትኖራለህ። ሰዎች ሲያዩህ «ስለኔ የተለየ ምን አደረክ?» ይሉሃል። ከነሱ የተለየ ያደረከው ነገር ከምስጢሩ ጋር መስራትህ ብቻ ነው።

## ሞሪስ ጉድማን

እናም በአንድ ወቅት ሰዎች ሊያደርገውምና ሊናገረውም ያለቱን ሁሉ ታደርገዋለህ። ይናገርሃልም።

t.me/OLDBOOKSPDF

## ዶ/ር ፍሬድ አላን ወልፍ

*እኛ አሁን ወደ አዲስ ዘመን እየተሸጋገርን ነው:: «ስታር ትሬክ» እንዳለው ቦታ የመጨረሻው ጠርዝ የሆነበት ዘመን ሳይሆን አይምሮ ነው የሚሆነው ዘመኑ::*

## ዶ/ር ጆን ሃጌሊን

*ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የማያዳግትበት መካ.-ዘመን ይታየኛል:: እስከአሁን ድረስ ከጥቅም ላይ የዋለው የሰው ልጅ አይምሮ 5 ከመቶ ብቻ መሆኑን አስታውስ:: የሰውን አይምሮ መቶ በመቶ ለመጠቀም ትክክለኛ ትምህርት ሊኖር ይገባል:: ሰዎች አቅማቸውንና አይምሯቸውን በመቶ እየተጠቀሙበት ያለች አለም በምናብህ ተመልከት:: ወደፈለግነው ስንሄድ፣ የፈለግነውን ስናደርግና የተመኘ ነውን ሁሉ ስናገኝ ታያለህ::*

የአሁኑ የአለማችን ጊዜ እጅግ የሚያጓጓ ጊዜ ነው:: አይሆንም የተባለውን ነገር የምናይበት ወቅት ነው:: «የተወሰነ ነው» የሚል እምነታችንን ስናስወግድና እኛም ወሰን-አልባ መሆናችንን ስንገነዘብ የሰውን መጠን-አልባነት እናውቃለን:: ይህ መጠን-አልባነትም በስፖርት፣ ጤና፣ ኪነ-ጥበብ፣ ቴክኖሎጂ፣ ሳይንስና በእያንዳንዱ ጥቃቅን ፈጠራ ይገለፃል::

# ኃያልነትክን ውደድ

## ቦብ ፕሮክቶር

*ከምትፈልገው ጥሩ ነገር ጋር እራስህን አብረህ እየው:: ታዋቂ መጻሕፍት፣ መሪዎችና የጥንት ተመራማሪዎች የሚነግሩን ይህን ነው:: ተመልሰህ ሂድና ጥበበኞቹን አጥና:: ብዙዎቹ በዚህ መጻሕፍ ቀርበውልሃል:: ሁሉም አንድ ነገር ገብቷቸዋል::*

ምስጢሩ ገብቷቸዋል:: አሁን አንተም ተረድተሃል:: የበለጠ ስትጠቀምበት የበለጠ ይገባሃል:: ምስጢሩ በውስጥህ ነው:: የውስጥህን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስጥር የበለጠ ስትጠቀምበት የበለጠ ወደአንተ እንዲመጣ ታደርገዋለህ። የበለጠ መከራ ማድረግ ከምትፈልግበት ጊዜ ትደርሳለህ። ምክንያቱም ኃያል፣ ትክክል፣ ጥበበኛ፣ አዋቂ፣ ፍቅርና ደስተኛ ስለምትሆን ነው።

## ሊዛ ኒኮልስ

*ልትደሰት ይገባሃል። አያለህ ያለ የሆነ ነገር በመኖሩ እዚህ ደርሰሃል። የተወለድከው ትንሽ ነገር ለመጨመር ነው። ለዚች አለም እሴት ለመጨመር ነው። በቀላሉ ትላንት ከነበርከው የበለጠ ትልቅና የተሻልክ ለመሆን ነው እዚህ የደረስከው።*

*ያለፍክበት ማንኛውም ነገርና እያንዳንዷ ያለፍከት ወቅት ለዚህ ላለህበት ጊዜ አዘጋጅተውሃል። አሁን ባለህ እውቀት ከአሁን ጀምሮ ምን ለማድረግ እንደምትችል ገምት። አሁን የራስህ እድል ፈጣሪ አንተው መሆንክን አውቀሃል። ስለዚህ የቱን ያህል መስራት እንዳለብህ ታውቃለህ? ምን ያህል እንደምትሆንስ? ስንት ሰዎች መባረክ ይኖርብሃል? ወቅቱን እንዴት ትጠቀምበታለህ? ማንም የንተን ዘፈን አይዘፍንም። መዝሙርህንም አይዘምርም። ማንም የንተን ታሪክ አይፅፍልህም። ማንነትህ ፤ ምን እንደምታደርግ አሁኑኑ ይጀምራል።*

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

*ትልቅ እንደሆንክ አምናለሁ። ስለአንተ አንድ ክቡር ነገር መኖሩንም አምናለሁ። ከህይወትህ ያጋጠመህን፣ የቱን ያህል ወጣትና ሽማግሌ ነኝ ብለህ የምታስበውን ከግምት ሳላስገባ ማለቴ ነው። በትክክል ማሰብ ስትጀምር በውስጥህ ያለው ይህ የሆነ ነገር፣ ይህ ከአለም የሚበልጥ አቅም ብቅ ማለት ይጀምራል። ጭልጥ አድርጎ ይወስድሃል። ይመግብሃል። ይመራሃል። ይጠብቅሃል። ያኖርሃል። እንዲሆን ከደረከው በእርግጠኝነት ውጤቱን አሁን አውቀዋለሁ። አለም ከምህዋሯ ትዞርልሃለች። ውቅያኖሶች ይሸሹና ጅረት ይሆኑልሃል። ወፎች ይዘምሩልሃል። ፀሐይ ትወጣና*

t.me/OLDBOOKSPDF

ትጠልቅልሃለች:: ከዋክብት ይመጡልሃል:: የምታየው ቆንጆ ነገር ሁሉ! የሚያጋጥምህ አስገራሚ ነገር ሁሉ ያንተ ነው:: ዘር ዘር ብለህ ተመልከት ካለአንተ ምንም ነገር የለም:: እንዲህ ነበር የምትለውን ትተህ የአሁኑ ማንነትህን ታውቃለህ:: የአለም ንጉስ ነህ:: የመንግስቱ ወራሽ ነህ:: የህይወት ቁንጮ ነህ:: እናም አሁን ምስጢሩን አወቅህ::

ደስታ ካንተ ጋር ይሁን !

«ምስጢሩ የነበረው፣ ያለውና የሚኖረው ሁሉ መልስ ነው»
ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን

# የምስጢሩ ማጠቃለያዎች

- የህይወትክን ጥቁር ሰሌዳ በምትፈልገው መሙላት አስብበህ::
- ማድረግ ያለብህ አሁን ደስ እንዲልህ ነው:::
- የውስጥህን አቅም የበለጠ ስትጠቀመበት የበለጠ አቅም ይመጣልሃል::
- የራስህን ትልቅነት የምታቅፍበት ጊዜ አሁን ነው:::
- የምንገኘው በሚወደስ ዘመን ውስጥ ነው:::
- የሚገድቡ ነገሮችን ሁሉ ስናስወግድ የሰውነትን ታላቅነት በማንኛ ውም ፈጠራ እንገነዘባለን::
- የምትወደውን ነገር አድርግ:: የሚያስደስትህን ነገር ካላወቅክ «የሚያስደስተኝ ምንድን ነው» ብለህ ጠይቅ:: ደስታህን ስትሻ የደስታ ጉርፍ ያጥለቀልቅሃል:: ምክንያቱም ደስታን እያመነጨህ ነውና::
- አሁን የምስጢሩን እውቀት ተምረሃል:: ይህን እውቀት ምን እንደምታደርገው የራስህ ፋንታ ነው::: የመረጥከው ነገር ሁሉ ትክክል ነው:: ኃይሉ የራስህ ነው:::

t.me/OLDBOOKSPDF

# የህይወት ታሪኮች

## ጆን አሣራፍ

የጎዳና ህፃን ነበር:: አሁን ግን የታወቀ ደራሲ፣ መምህርና የቢዝነስ አማካሪና ባሃብቶች የበለጠ ሃብት እንዲያገኙና የተለየ ህይወት እንዲኖሩ የሚጥር ነው:: ለአለፉት 25 አመታት በሰው አይምሮ፣ ኳንተም ፊዚክስና የቢዝነስ ስትራቴጂ ተመራምሯል:: የተማረውን በተግባር በማዋሉ ጆን አራፍ የብዙ ሚሊዮን ዶላር ኩባንያዎች ከምንም ተነስቶ አቋቁሟል:: አሁን ይህን የቢዝነስ ጥበብና ገንዘብ ማፍራት የመቻል ክህሎት ለሌሎች እያካፈለ ይገኛል:: ስለጆን የበለጠ መረጃ ካስፈለገ ድረ-ገጽ www.onccoach.com ይመልከቱ::

## ሚካኤል በርናርድ ቤክዊዝ

ገለልተኛውና የሁሉም ኃይማኖት ሰው የነበረው ዶ/ር ቤክዊዝ በ1986 የአጋፔ አለም አቀፍ መንፈሳዊ ተቋምን መሰረተ::ተቋሙ 10000 የአገር ውስጥ አባላትና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ አለማቀፋዊ ጓደኞች አሉት::

ቅዱስ ዳላይ ላማ፣ ዶ/ር ኤ. ቲ. አሪያራትኔና አሩን ጋንዲን ከመሳሰሉት ብርሃን ሰጪዎች ጋር ሆኖ በአለም አቀፍ ስብሰባዎች አገልግሏል:: በአመታዊ ስብሰባዎቹ አያሌ ሳይንቲስቶችን፣ የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎችንና የእምነት መሪዎችን የሚያሰባስበው የአለም አቀፍ አዲስ አስተሳሰብ ማህበር ተባባሪ መሥራች ነው::

ዶ/ር ቤክዊዝ ስለተመስጦና ሳይንሳዊ ፀሎት ያስተምራል:: ወጣ ያሉ ስብሰባዎችን ያካሂዳል:: በኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች ላይ ንግግር ያቀርባል:: ስለ ህይወት ራዕይ ሂደትን የፈለሰፈ ነው:: የልብ መነሳሳት፣ የአርባ ቀን አይምሮ፣ ፈጣን የነብስ ጭብጥና የሰላም ማስታወቂያ የተባሉት ፅሑፎች ደራሲም ነው:: ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.agapelive.com ይሂዱ::



t.me/OLDBOOKSPDF

## ደኔቪየቭ በህሬንድ(1881 - 1960)

ደኔቪየቭ በህሬንድ የተማረችው ከታላቁ ዳኛ ከቶማስ ትሮዋርድ ጋር ነው:: ቶማስ ትሮዋርድ ከቀደምት የመንፈሳዊ ሜታፊዚክስ መምህራን መካከልም አንዱ ነው:: የአይምሮ ሳይንስ የሚባለው ፅሑፍ ደራሲም ነበር:: ቶማስ ትሮዋርድ በህሬንድ ተማሪው አድርጎ ስለመረጣት በሰሜን አሜሪካ ውስጥ የአይምሮ ሳይንስ ለ35 አመታት አስተምራለች:: በተጨማሪም የራሷ የሆኑትን «የማይታየው ኃይልህ» እና «ልብ የተመኘውን ማግኘት» የሚሉ ጽሑፎችን ደርሳለች::

## ሊ ብሮወር

ሊ ብሮወር አለም አቀፍ የምክር አገልግሎት ሰጪ የሆነው «የተጠናከረ ሃብት» የሚባለው ድርጅት መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው:: ድርጅቱ ለንግድ ተቋማት፣ ፋውንዴሽኖች፣ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ተምክሯቸውን፣ አስተዋጽኦቻቸውንና የገንዘብ ሃብታቸውን ለማጠናከር የሚረዱ መፍትሔዎችን ይሰጣል:: ሊ ብሮወር ኳድራንት ሊቪንግ ኤክስፔሪያንስ የሚባል ተቋም መሥራችም ነው::

የተቋሙ አላማ የቡቲክ ድርጅት ሲሆን የአለም አቀፍ የኳድራንትሊቪንግ አማካሪዎችን የንግድ ፈቃድ መስጠትና ማሰልጠን ነው:: የ «ሃብት አነሳስና አጠባበቅ» የሚለው ጽሑፍ ተባባሪ ደራሲም ነው:: «ብሮወር ኳድራንት» የሚለውንም የፃፈው እርሱ ነው:: ሁለቱ ድረ-ገፆቹ www.empwoeredwealth.com እና www.quadrantliving.com የሚባሉት ናቸው::

## ጃክ ካንፊልድ

«የግብ መምጣት መርሆች» የሚለውን ጽፏል ጃክ:: «የዶሮ መረቅ ለነብስ» የሚል ተከታታይ ጽሁፍ በኒወርክ ታይምስ ላይ ተባባሪ አቅራቢ ነው:: ጋዜጣው በአሁኑ ወቅት በአንድ ጊዜ ከ100 የበለጠ ቅጂዎች አሉት:: ለአሜሪካ ባለሃብቶችና ለንግድ ተቋማት መረጃዎች አሉት:: ለማናጀሮች፣ የሽያጭ ሰራተኞች፣ ተቀጣሪዎችና አስተማሪዎች በጥሶ የመውጣት ዘዴን በማሳየት የመጀመሪያው ባለሙያ ነው:: በመቶ ሺህ

t.me/OLDBOOKSPDF

የማቆጠሩ ግለሰቦችንም ህልሞቻቸውን እውን የሚያደርጉበትን መንገድ በማመላከት ረድቷቸዋል:: ጃክ ካንፊልድን የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በ «www.jackcanfield.com » ያገኛሉ::

## ሮበርት ኮሊየር (1885 - 1950)

ሮበርት ኮሊየር የተዋጣለትና ግቡን የመታ አሜሪካዊ ዐሐፊት ነበር:: «የዘመናቶቹ ሚስጥር» እና «የትርብህ ሃብታሞች» የሚሉትን ጨምሮ ሁሉም መጽሐፎቹ ኮሊየር በሚታፊዚክስና ግብ መምታት፣ ደስታና ብልፅግና እያንዳንዱ ሰው ሊያገኛቸው የሚችሉ መብቶቹ ናቸው በሚለው የግል እምነት ላይ ባደረጋቸው ምርምሮች ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጽሑፎች ከባለ ሰባት ቅፁ «ሴት ዘሴክሬት ኦፍ ዘ ኤጅስ» ከሚለው መጽሐፉ በሮበርት ኮሊየር እታሚዎች ስምምነት የተወሰዱ ናቸው::

## ሜሪ ዲያመንድ

ሜሪ በአለም የታወቀች የፌንግ ሹዊ ንግስት ናት:: ይህን ከሃያ አመታት በላይ ተለማምዳዋለች:: በመሆኑም በልጅነቷ ያገኘችውን እውቀት በእጅጉ አበልፅጋዋለች:: አያሌ የሆሊውድ ተደናቂዎችን፣ ዋና የፊልም ዳይሬክተሮችንና በህዝብ ታዋቂ የሆኑ ብዙ ሰዎችን በሁሉም የህይወት መስኮቻቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ መንገዱን በማሳየት ረድታቸዋለች:: «ሜሪ ዲያመንድ ፌንግ ሹይ፣ ዲያመንድ ደውሲንግና ውስጣዊ ዲያመንድ ፌንግ ሹይ » የስበት ህገን በግለሰብ ሁኔታ ድልድይ ለማድረግ በሚል ፈጥራለች:: በድረ-ገፅ www.mariediamond.com ተጨማሪ መረጃ ያግኙ::

## ማይክ ዱሌይ

ዱሌይ ባለሙያ ሳይሆን, የህይወት ደፋር ነው:: ሁለቱን የተቋምና የዘለሃብት መስኮችን በተዋጣለት መልኩ ቀዝፎባቸዋል:: ፕራይስ ዋተርሃውስ ለሚባል ድርጅት በአለም ዙሪያ የኖረና የሰራ ነው:: በ1989 «ቶታሊ ዩኒክ ቶውትስ»ን በተባባሪነት መሰረተ:: የተቋሙ አላማ አስደሳች የስጦታ እቃዎችን ማከፋፈል ነበር:: ከመሬት ተነስቶ ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቋም እድግ በመስፋፋት በተለያዩ አገሮች ቅርንጫፎቹን እንደ አሸን በትኗል:: በ2000 ይህን ተቋም በድረ-ገጽ ላይ የተመሰረተ የእንሳሽነትና የፍልስፍናዊ ደፋሮች ክበብ አደረገው:: በአሁኑ ወቅት የ169 አገሮች ተወላጅ የሆኑ 60000 አባላት አሉት ተቋሙ:: «ከዩኒቨርስ የተላኩ ማስታወሻዎች» የሚለው ባለሶስት ቅጽ ጽሁፍና «ማስቲያ የሌላቸው እጋባሚዎች» የሚለው በአለም ታዋቂውን የኦዲዮ ፕሮግራም ጨምሮ የብዙ መጻህፍት ደራሲ ነው:: ስለማይክ በ www.tut.com ብዙ መማር ይቻላል::

## ቦብ ዶይል

ቦብ ዶይል " Wealth Beyond Reason" የሚለው ፕሮግራም ፈጣሪ ነው:: ይህ ፕሮግራም ኃይለኛ የመልቲ ሚዲያ ስርአት ትምህርት ሲሆን የሚያጠነጥነው በስበት ህግ አተገባበር ላይ ነው:: ቦብ ያተኮረው በስበት ህግ ሳይንስ ላይ ነው:: አላማውም ህጉን ለሚጠቅምህ ጉዳይ እንድታውለውና ሀብት፣ እርካታ፣ የተመቻቸ ግንኙነት ሌላም የፈለከውን ነገር እንድታገኝ ለመርዳት ነው:: ለተጨማሪ መረጃ www.wealthbeyondreason.com ን ይጎብኙ::

## ሃሌ ደወስኪን

የኒወርክ ታይምስ ደራሲና የሴደና ሜተድ ዋና ሻጭ ነው:: ሃሌ ደወስኪን ሰዎች የፈለጉትን ለማግኘት ያለባቸውን ውስንነት የሚያቃልል ጥረትን ያደርጋል:: የሴደና ሜትድ ገዳቢና አስቸጋሪ ስሜቶችን፣ እምነቶችንና አዝማሚያዎችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል የሚያሳየን የተለየ ዘዴ ነው:: ሃሌ እነዚህን መርሆች ላለፉት ሰላሳ አመታት ለአለም አስተምሯል:: ድረ-ገፁ www.sedona.com ነው::

## ሞሪስ ጉድማን

«ዘ ሚራክል ማን» የሚለውን አክሎ ሞሪስ ጉድማን በ1981 ርዕስ ዜናዎችን አዘጋጅቷል:: ያን ጊዜ አውሮፕላኑን አጋጭቶ ከደረሰበት

አደጋ አጋጥሞ ነበር። አደጋ እንደደረሰበት መራመድ፣ መናገር ወይም ጤናማ ሆኖ መስራት እንደማይችል ተነግሮት ነበር። ነገር ግን ጥሩ ጤናማ ሆኖ ጤናማ ሆኖ በማስተሰብ... አስደናቂ እየዘረ በሚናገረው የራሱ ታሪክ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አነቃቅቷል። የጥሬስ ሚስት ካቲ ጉድማን በሚሰጥሩ ውስጥ ተጥንቷን ሆናለች። የተሳተፊችውም እራሷን የማዳንን ነገር እየተናገረች ነው። የበለጠ ለማወቅ www.themiracleman.org ን ጉብኙ።

## ጆን ግሬይ (ዶክተር)

ወንዶች ከማርስ ሴቶች ደግሞ ከቬነስ የመጡ ናቸው የሚለው ጽሑፍ ደራሲ ነው። ያለፈው አስርት አመት ግሩም ሽያጭ የነበረው ነበር ይህ ጽሑፍ። ከ30 ሚሊዮን ቅጂዎች በላይ ተሸጧል። ሌሎች 14 በደንብ የተሸጡ መጽሀፍትን ደርሷል። በሺህ ለሚቆጠሩ ተሳታፊዎች ሴሚናሮችን አዘጋጅቷል። ዋናው ትኩረቱ ወንዶችና ሴቶች ልዩነታቸውን እንዲረዱ፣ እንዲያከብሩና እንዲያደንቁ መርዳት ነው። አዲሱ መጽሐፍ «ዘ ማርስ ኤንድ ቬነስ ዳይት ኤንድ ኤክስርሳይስ ሶሊሽን» የሚለው ነው። www.marsvenus.com በሚለው ድረ-ገጽ የበለጠ ማወቅ ይቻላል።

## ቻርለስ ሃኔል *(1866 - 1949)*

ቻርለስ ሃኔል የተዋጣለት አሜሪካዊ የቢዝነስ ሰው ነበር። የአያሌ መጽሀፍት ደራሲም ነው። ሁሉም መጽሀፍቱ በህይወቱ ታላቅነትን ለማግኘት የተጠቀመባቸውን ሃሳቦችና ዘዴዎች ይዘዋል። የታወቀው ሥራው «ዘ ማስተር ኪ ሲስተም» የሚለው ነው። ይህ

መጽሐፍ 24 ሳምንታዊ ትምህርትን በትልቅነት ላይ በመስጠት ባሬም መጀመሪያ በ1912 ሲገፍ እንደነበረው ታዋቂ መጽሐፍ ነው።

## ጆን ሃጌሊን (ዶክተር)

ጆን ሃጌሊን የአለማችን የታወቀ የኳንተም ፊዚክስ ሊቅ መምህርና የፐብሊክ ፖሊሲ ባለሙያ ነው። «ማኑዋል ፎር ኤ ፐርፌክት ገቨርንመንት» የሚለው መጽሐፉ ዋና ዋና የህብረተሰብና አካባቢ

ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል ያብራራል:: ጆን ሃጊሊን የተዘበረውን የኒ.ሊቢ. ሽልማት አግኝቷል:: ይህ ሽልማት የሚሰጠው ለህብረተሰብ ወሳኝ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሳይንቲስቶች ነው:: በ2000 የተፈጥሮ ህግ የሚባለው ፓርቲው ለፕሬዚዳንትነት እጭርዕት የነበረ እጩም ነበር:: ጆን ከአለማችን ጥቂት ሳይንቲስቶች አንዱ እንደሆነ ዛሬ ብዙ ሰዎች ይናገሩለታል:: ድረ-ገፁ www.hagelin.com ነው::

## ቢል ሃሪስ

ቢል ሃሪስ ባለሙያ ተናጋሪ፣ አስተማሪና የንግድ ባለቤት ነው:: ቢል በአይምሮ ተፈጥሮና በመለዋወጫው መንገዶች ላይ ዘመናዊ ጥናትን ከተማረ በኋላ ጥልቀት ካለው ተመስጦ ጥቅሞች የሚገኝ ሆሎሲንክ የሚባል የኦዲዮ ቴክኖሎጂን ፈጠረ:: ሴንተር ፖይንት የምርምር ተቋም የተባለው ኩባንያው በአለም ዙሪያ የሚገኙ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በደስታና ከጭንቀት ነፃ ሆነው ለመኖር አስችሏቸዋል:: የበለጠ ለማግኘት www.centrepointe.com ን ይጎብኙ::

## ዶ/ር ቤን ጆንሰን (በተለያዩ መስኮች ዶክተር)

ቤን ጆንሰን መጀመሪያ የተማረው የምዕራቡን ህክምና ነበር:: ህይወቱን ለአደጋ ያጋለጠ በሽታ ከያዘው በኋላ ኃይል ተጠቅሞ በማዳን ላይ ፍላጎት አሳደረ:: እጅግ ፍላጎት የነበረው ዶ/ር አሌክስሲዮድ ባገኙት የሂሊንግ ኮድስ ላይ ነበር:: ዶ/ር አሌክሳሲዮዲ የኩባንያ ባለቤት ናቸው:: ኩባንያው የሁለቱን አስተምህሮቶች ያሰራጫል:: የበለጠ ለመማር www.healingcodes.com ይግቡ::

## ሎራል ላንግማየር

ሎራል ላንግማየር የ «ሊቭ አውት ላውድ» መስራች ናት:: ይህ ተቋም ሰዎች የሚፈልጉትን ገዘብ ለማግኘት የሚያስችል ትምህርት ይሰጣል:: የአይምሮ ሁኔታ ሃብት ለማፍራት ቁልፍ መሆኑን ታምናለች:: ብዙ ሰዎች ሚሊዬነሮች እንዲሆኑ አግዛለች:: ድረ-ገጿ www.liveoutloud.com የሚል ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

## ፕሬንቲስ ሙልፎርድ (1834 - 1891)

ፕሬንቲስ ሙልፎርድ ከቀዳሚዎቹ ጸሀፊዎችና የአዲሱ አስተሳሰብ ንቅናቄ መሥራቾች አንዱ ነው፡፡ በሥራው በአያሌ ደራሲያንና መምህራን ላይ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ በሥራው ውስጥ አስተሳሰቦች ነገሮች ናቸው እና የነጠሉ መስተል ቤተመጽሐፍት ድርሰቶች ይካተታሉ፡፡

## ሊዛ ኒኮልስ

ሊዛ ኒኮልስ ኃይለኛ የሰባዊ ሹመት ጠበቃ ናት፡፡ «ብዙሃኑንና ትናንሾቹን መተስተስ» የሚባለው ተቋም መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናት፡፡ እነዚህ ሰፊ ክህሎቶች በወጣት ልጆች፣ ሴቶችና ባለሃብቶች ጥልቅ ለውጥ የሚያመጡ ናቸው፡፡ እንዲሁም ለትምህርት ሥርአቱ፣ ለደንበኞች፣ ተቋማትና እምነትን መሰረት ላደረገ ፕሮግራሞች ግልጋሎት ይሰጣለች፡፡ ሊዛ «የዶሮ መረቅ ለአሜሪካና ለአፍሪካ ነብስ» የሚለው ጽሑፍ ተባባሪ ደራሲ ናት፡፡ ድረ-ገጿ www.lisanichols.com ነው፡፡

## ቦብ ፕሮክቶር

የቦብ ፕሮክተር ጥበብ የመጣው ከታላላቅ አስተማሪዎች ሲወርድ ሲዋረድ ነው፡፡ የጀመረው በአንድሩ ካርኔጂ ሲሆን ከዚህ ወደ ናፖሊዮን ሂል ከናፖሊዮን ሂል ደግሞ ወደ እርል ላይቲንጋል የተወራረደ ነው፡፡ ላይቲንጋል የጥበቡን ችቦ ለቦብ ፕሮክተር አወረሰ፡፡ ቦብ ለአርባ አመታት በአይምሮ እምቅ ኃይል ዙሪያ ሠርቷል፡፡

በስበት ህግ አማካይነት የበለፀገ ህይወት ከባንያዎችና ግለሰቦች ማግኘት እንዲችሉ ቦብ አለምን እያዞረ ስለሚስጥሩ ያስተምራል፡፡ ቦብ በአለም እጅግ በመሸጥ ላይ የሚገኘው «ሃብታም ሆነህ ነበር የተወለድከው » የሚለው መጽሐፍ ደራሲ ነው፡፡ ስለቦብ የበለጠ ለማወቅ www.bobproctor.com ን ይጎብኙ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

## ጀምስ አርተር ሬይ

ጀምስ ህይወቱን ሙሉ የእውነተኛ ሃብትና ብልፅግና መርሆች ተማሪ ነው። ጀምስ የተዋጣለትና ሀብር የተጉናፀፈ ሃብቱ ሳይንስን የፈጠረ ነው። ይህ ሳይንስ ሰዎችን እንዴት ያልተወሰነ ገንዘብ፣ ዝምድና፣ ትምህርት፣ አካልና መንፈሳዊነት ሊያገኙ እንደሚችሉ ያስተምራል። የግላዊ አሰራሩ ሥርአት፣ የድርጅቶች የስልጠና ፕሮግራሞችና የምክር አገልግሎቶች በአለም ሙሉ ከፍተኛ ላይ ውለዋል። እውነተኛ ሃብት፣ ግብ መምታትና የሰው ልጅ እምቅ ኃይል በሚሉ ርዕሶች ላይ አዘውትሮ ይናገራል። ጀምስ በምስራቃውያን መሰረታዊና እምነታዊ ባህሎችም ባለሙያ ነው። ድረ-ገፁን www.jamesray.comን ይመልከቱ።

## ዳቪድ ሺርመር

ዳቪድ ሺርመር የተዋጣለት የአክሲዮን ነጋዴ፣ ኢንቨስተርና የኢንቨስትመንት አሰልጣኝ ነው። ወርክሾፖችን፣ ሴሚናሮችንና ኮርሶችን ያዘጋጃል። ትሬዲንግ ኤድጅ የሚባለው ኩባኒያው ሃብት ለማግኘት በሚችልበት ሁኔታ አይምሮን በማዘጋጀት እንዴት ገደብ የሌለው ገቢ ማግኘት እንደሚቻል ያስተምራል። የሺርመር የአውስትራሊያና የባህር ማዶ አክሲዮኖች ትንታኔ ዘወትር ትክክለኛነት ስላለው ይደነቃል። በድረ-ገጽ www.tradingedge.com.au የበለጠ ይገኛል።

## ማርሲ ሺሞፍ

(በቢዝነስ የማስትሬት ዲግሪ ያላት)

«የዶሮ መረቅ ለሴቶች ነብስና የዶሮ መረቅ ለእናቶች ነብስ» የሚለው ጽሑፍ ተባባሪ ደራሲ ናት ማርሲ። ስለግለሰባዊ እድገትና ደስታ ደስተኛ ሆና የምትናገር የለውጥ መሪ ናት። ሥራዋ የሴቶችን ህይወት በተለይ ለማራመድ የተቀየሰ ነው። «የኢስቲም ግሩፕ ኩባንያ» ተባባሪ መስራችና ፕሬዚዳንት ስትሆን ኩባንያው ለሴቶች እራስን የመንከባከብና የማነቃቃት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል። ድረ-ገጿ www.marcishimoff.com ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

## ዶ/ር ጆ ቫይታል (የሳይንስ ዶክተር)

ከሃያ አመት በፊት መኖሪያ ቤት አልነበረውም:: በአሁኑ ወቅት ከአለም ታዋቂ የንብያ ባለሙያዎች አንደ አንዱ ይቆጠራል:: በውጤታማነትና ባለፀጋነት መርሆዎች ላይ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል:: «ላይፍ ማ.ሲንግ ኢንስትራክሽን ማኑዋል፣ ሂፕኖቲክ ራይቲንግና ll አትራክተር ፋክተር» የሚባሉትን ጨምሮ ማለት ነው:: ሁሉም በጣም የሚሸጡ ናቸው:: ጆ ቫይታል በሚታፊዚካል ሳይንስ የዶክተር ዲግሪ አለው:: የታወቀ ሂፕኖቴራፒስት፣ የሚታፊዚክስ ተግባሪ፣ የተመረጠ ሚኒስትርና የቺ ኩንግ ፈዋሽ ነው:: በእርሱ ላይ ተጨማሪ ለማወቅ ድረ-ገጽ www.mrfire.com ን ይጎብኙ

## ዶ/ር ዴኒስ ዌትሌይ

ዶ/ር ዌትሌይ ከታወቁት አሜሪካዊ ደራሲዎች፣ አስተማሪዎችና አማካሪዎች አንዱ ነው:: የናዛ አስተሮናዊቶችን ለማሰልጠን ተቀጥሮ ነበር:: ቆይቶም ተመሳሳይ ፕሮግራምን ለኦሎምፒክ ሯጮች ተጠቅሞ ነበር:: «የአሸናፊነት ስነ-ልቦና» የሚለው የኦዲዮ አልበሙ አሁንም ከፍተኛ ሽያጭ ያለው ነው:: አስራ አምስት ልብ-ወለድ ያልሆኑ መጻሕፍትን ጽፏል:: ድገ-ገፁ www.waitley.com ነው::

## ኒል ዶናልድ ዋልሺ

ኒል የዘመናችን መንፈሳዊ መሢህና እጅግ ተሻጭ የሆነው የምድር አንቀጥቃጩ ባለሶስት ተከታታይ የሆነው «ንግግር ከእግዚአብሔር ጋር» የሚለው መጽሐፍ ደራሲ ነው:: ኒል ሃያ ሁለት መጻሕፍትን ደርሷል:: የቪዲዮና አዲዮ ፕሮግራሞችም አዘጋጅቷል:: የአዲስ መንፈሳዊነትን መልዕክት ይዞ አለምን ይዞራል:: በ www.nealedonaldwalsch.com ሊገኝ ይችላል::

## ዋላሥ ዋትልስ (1860 -1911)

በአሜሪካ የተወለደው ዋላሥ ዋትልሥ በ«አዲስ አሳብ» ትግበራ ላይ ከመጻፉ አስቀድሞ የተለያዩ ሃይማኖቶችንና ፍልስፍናዎችን በመማር አያሌ አመታት አሳልፏል:: የዋትልስ ብዙ መጻሕፍት በዘመናችን

t.me/OLDBOOKSPDF

የብልፅግናና የተዋጣለት የመሆን ትምህርት ላይ በአያሌው ተጽንኦ አድርገዋል። እጅግ ታዋቂው ሥራው «ሃብታም የመሆን ሳይንስ» የሚለው ነው። የታተመውም በ1910 ነው።

## ፍሬድ አላን ወልፍ (ዶክተር)

ወልፍ የፊዚክስ ሊቅ፣ ፀሐፊና አስተማሪ ነው። በንድፈ ሃሳባዊ ፊዚክስ የዶክተር ዲግሪ አለው። ዶ/ር ወልፍ በመላ አለም በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች አስተምሯል። የኳንተም ፊዚክስና የንቃተ ህሊና ነክ ሥራው በሚጽፋቸው ጽሁፎች አማካይነት በደንብ ይታወቃል። «የኳንተም እምርታ መውሰድ» የሚለውን ጨምሮ የ12 መጻሕፍት ደራሲ ነው። የብሔራዊ መጽሐፍ ሽልማትን አግኝቷል። ዛሬ ዶ/ር ወልፍ በአለም ዙሪያ ማስተማሩንና መጻፉን ቀጥሏል። በኳንተም ፊዚክስና በንቃተ - ህሊና መካከል ስለአለው ግንኙነት የሚያደርገውን አስደናቂ ምርምር እያስኬደው ነው። ድረ-ገፁን www.fredalanwolf.com ን ይጉብኙ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ታላቁ ምስጢር . . .



ምስጢሩ ከአንድ መቶ አመት ከሞላው መፅሐፍ ነበር የተገኘው:: መፅሐፉንም የሰጠችኝ ሃይሊይ ብዬ የምጠራት ልጄ ነበረች:: ታሪኩን መሠረት አድርጌ ምስጢሩን ወደኋላ ተመልሼ መመርመር ጀምርኩ:: ይህን የሚያውቁትን ሁሉንም ሰዎች ስረዳ ማመን አቃተኝ:: ለካስ በታሪክ የላቁት( ካርኒጌ፣ ፕላቶ፣ ጋሊሊዮ፣ ሼክስፒር ፣ ኒውተን፣ ቤቶቨን፣ አንስታይን፣ ኤዲሰን) ኖረዋል::

ገፆችን እያለፍክ በሄድክና ምስጢሩን በተማርክ ቁጥር እንዴት አንድ የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት፣ ለመሆን፣ ወይም ለማድረግ እንደምትችል ለማወቅ ትችላለህ:: ከፊትለፊትህ ያለውን እውነተኛ ታላቅነትሕን ትገነዘባለህ::

በመፅሐፉ ውስጥ የሚያስተምሩን ዘመናዊ መምህራን (ሴትም ወንድም) ምስጢሩን በመጠቀም ጤንነታቸውን፣ ሐብታቸውንና ደስታቸውን ያገኙ ሲሆን ብዙዎችም ከመፀሐፉ የተገኘውን እውቀት በተግባር ላይ በማዋል በሽታን ማጥፋት፣ ዳጎስ ያለ ሐብትን ማፍራት፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማለፍ እና ብዙዎች «አይቻልም» ያሉትን እውን ማድረግ ችለዋል::

ዋጋው: 24.00 ብር

Far-East Trading(P.P)

Cover and Layout design Girum Y.

t.me/OLDBOOKSPDF